

## ሽግግር፤ ከጋዜጠኝነት ወደ ፖለቲካ ፓርቲ አባልነት



በገፅ 6-7


# ሰንደቅ


እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በሰላም አደረሳችሁ






ሰንደቅ 10ኛ ዓመት ቁጥር 487 ረቡዕ ታህሳስ 29 2007 ዋጋ 7 ብር

# “በመጪው ምርጫ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ቢፈጠር ተጠያቂው ገዥው ፓርቲ ነው”

አቶ ተክሌ በቀለ /የአንድነት ፓርቲ ተ/ም/ሊቀመንበር/

# “የጥፋት መንገድ ‘ለሕዝባዊ እምቢተኝነት’ ሽፋን አይሆንም”

አቶ ረዳኢ ሃለፎም /የኢህአዴግ ፅ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ/

በጋዜጣው ሪፖርተር

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ባሳለፍነው ሳምንት በጽ/ቤቱ ምርጫውን ተከትሎ ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ላይ መምከሩን ምንጮች ገለጹ፡፡

በምክረ ሃሳቡ ስብሰባ ሁለት የተለያዩ አቋሞች ተራምደዋል፡፡ በአመራሩ ወገን ምንም አይነት ሕዝባዊ ዕቢተኝነት ቢፈጠር በበላይነት እኛ መምራት አለብን ሲሉ በሌላ ወገን ደግሞ የምርጫ ፓርቲዎች በመሆናችን ሊነሱ የሚችሉ ማናቸውም ሕዝባዊ እምቢተኝነትን በእኛ መመራት የለባቸውም ማለታቸውን ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡

የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝደንት አቶ ተክሌ በቀለ በበኩላቸው “ሕዝባዊ እምቢተኝነት” በሚል አጀንዳ አልተወያየንም ካሉ በኋላ “ኢሕአዴግ ግን አብዮት እንዲቀሰቀስ ሌት ተቀን እየሰራ መሆኑን እናውቃለን፣ እናምናለን” ሲሉ ወንጅለዋል፡፡

“ሕዝቡን እያገለለ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እያገለለ፣ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችን እያሸ ነው ያለው፡፡ ስለዚህ እኛ እንኳን ባንፈልገው፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት አይቀርም፡፡ ስለዚህ ይህ ምርጫ ሰላማዊና ፍትሃዊ ካልሆነ ተጠያቂው ገዢው ፓርቲ ነው” ብለዋል፡፡

ገዢው ፓርቲ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እንዲፈጠር እየሰራ ነው ለሚሉት ውንጀላችሁ ማሳያዎቹ ምንድን ናቸው ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ “ነፃ ሚዲያ ሞቶ ተቀብሯል፡፡ ብሎገሮች ታስረው ነው የሚገኙት፡፡ የመሬት ፖሊሲ ቀውስ ያስከተለው ችግር የሚታወቅ ነው፡፡ ለሃይማኖት ተቋማት ጥያቄ ምላሽ አልተሰጠም፡፡ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውሶች ሕብረተሰቡን ወደ አላስፈላጊ ሁኔታዎች እየመሩት ነው፡፡ ባለፉት አራት ምርጫዎች የይስሙላ ምርጫ ነበሩ፡፡ አሁን ግን ህዝቡ የመንግስት ለውጥ ፈልጓል፡፡ ስለዚህም በመጪው ምርጫ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ቢፈጠር ተጠያቂው ገዢው ፓርቲ ነው” ሲሉ አቶ ተክሌ ገልፀዋል፡፡

‘ሕዝባዊ እምቢተኝነት’ የምትሉት ቢከሰት እንዴት ለማስተናገድ ተዘጋጅታችኋል ለሚለው ጥያቄም ሲመልሱ፤ “ጊዜው ሲደረስ የሚታይ እንጂ አሁን ላይ ሆነን የምንለው ነገር የለም” ብለዋል፡፡

የኢህአዴግ ፅ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ረዳኢ ሃለፎም ለተሰነዘረው ክስ በሰጡት ምላሽ፣ “መጀመር ለሚፈልጉት የጥፋት መንገድ ‘ሕዝባዊ እቢተኝነት’ ሽፋን አይሆንም፡፡ ከወዲሁ ሕገወጥነት የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎችን ለመጀመር መታሰቡ በኋላ ላይ የሚያስከፍለው ዋጋ ከባድ ነው የሚሆነው” ብለዋል፡፡ አያይዘውም ፣ኢህአዴግ ከሕዝቡ ውስጥ የበቀለ ድርጅት እንጂ ከየትም የመጣ አይደለም፡፡ ሕዝብ ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ ይረዳል፡፡ ሕዝብን የሚያርቅበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ከሰላማዊና ሕጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋርም የጋራ የስምምነት

በገፅ 17

## ምርጫ ቦርድ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስታረቅ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ

በፋኑኤል ክንፉ

በምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ በፕሮፌሰር መርጋ በቃና አወያይነት በአዲሱ የአንድነት አመራር እና መርህ ይከበር በሚል ጥያቄ ባነሱ ወገኖች መካከል ሰኞ ታህሳስ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የተካሄደው ስብሰባ ያለውጤት ተበተነ፡፡ ምርጫ ቦርድ ማክሰኞ ታህሳስ 28 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲሱ የአንድነት ፓርቲ ሕጋዊነት ላይ ውሳኔ ያሳልፋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአንድነት አዲሱን አመራር እና መርህ ይከበር በማለት ጥያቄ እያቀረቡ ያሉ ወገኖችን ሰኞ ዕለት ስብሰባ ጠርቶ ችግሮቹ እንዲፈቱ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም ስብሰባው ያለውጤት ተበትኗል፡፡

መርህ ይከበር ከሚለው ወገን በውይይቱ የተሳተፉት የአንድነት ፓርቲ የምስራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ኃላፊ መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ አየለ ደስታ ለሰንደቅ ጋዜጣ እንደገለጹት፣ በሕገወጥ መንገድ ስልጣን የያዘው አመራር ከበፊቱ የበለጠ ሕገወጥ ሆኖ በመቅረቡ “እናንተ

በገፅ 16

## የጋዜጠኞቹና ጦማሪያኑ ክስ እንዲሻሻል ፍ/ቤት በድጋሚ ትዕዛዝ ሰጠ



በገፅ 16

## የቤተ ክርስቲያኒቱ የገቢ ማስገኛ ተቋማት ኪራይ የግለሰቦች መጠቀሚያ መኾናቸው ተጠቆመ



ሀብትና ጥቅሟን የሚያስጠብቅ የኪራይ ተመን ፖሊሲ የሚወጣበት ጥናት ተጀምሯል

የጥቂት አድባራት ሓላፊዎችና ጥቅመኞች እንቅስቃሴ ጥናቱን እንዳያኮላሸው ተሰግቷል


የአለቆች የመኪና ሽልማት የሙሰኞች ከለላና ስብልሹነት በር የሚከፍት ነው ተብሏል

በገፅ 17


ሕግ...13
ኢኮኖሚ...8
መዝናኛ...10
የኔ ሃሳብ...18

# ለቀጣዩ ምርጫ ሠላማዊነት ሁሉም ወገን የድርሻውን ይወጣ

በግንቦት ወር የሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫን የአውሮፓ ህብረት እንደማይታዘብ ይፋ ማድረጉ የሚታወቅ ነው:: ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ይህንን በተመለከተ በቅርቡ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተጠይቀው ጉዳዩን የፓርቲዎቹ መሆኑን በመጠቆም መተማመኑ ካለ ብዙም አሳሳቢ እንደማይሆን ተናግረዋል:: በአሁኑ ወቅት በምርጫ ሒደት እየታየ ያለው ሁኔታ ግን መተማመንና መግባባትና የተከተለ አይመስልም::



መድረክ በቅርቡ የተካሄደው የሕዝብ ታዛቢ ምርጫ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን በመጥቀስ በድጋሚ እንዲካሄድ ሰሞኑን ጠይቋል:: አንድነት ፣ሰማያዊ እና መኢአድ የተባሉ ፓርቲዎች በተናጠል የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ በትክክል አልተካሄደም በሚል ቅሬታቸውን በተለያዩ መንገዶች ገልጸዋል::

በተጨማሪም የፖለቲካ ፓርቲዎች የፋይናንስ ክፍፍል ቀመርን አስመልክቶ ምርጫ ቦርድ የጠራው ስብሰባ ብዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ቅሬታን አስከትሏል:: እነዚህ ሁኔታዎች በምርጫው ሒደትና ተአማኒነት ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ድርሻ እንዳያበረክቱ ሁሉም ወገን የራሱን ኃላፊነት ጥንቃቄና ኃላፊነት በተሞላው መንገድ ሊወጣ ይገባል::

ምርጫ ቦርድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድጋፍ የሚከፋፈልበትን ቀመር የማውጣት ሥልጣን በእጁ ስለሆነ ክፍፍሉ ፍትሐዊና ከአድልኦ የጸዳ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል:: ቦርዱ የሀገሪቱን ወቅታዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደርግ መልክ ረቂቅ ቀመሩን ያሻሽለዋል ተብሎም ይጠበቃል:: ፓርቲዎች በሕዝብ ታዛቢዎች ዕጩዎች ምርጫ ጋር ተያይዞ የሚያነሱትን ቅሬታ በአግባቡ መርምሮ ከፓርቲዎቹ ጋር መግባባት ላይ መድረስ የሚችልበትን መንገድም ሊፈልግ ይገባል::

ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግም የሥነምግባር ሕጉ አዋጅ ሆኖ ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለ መሆኑን ሳይዘነጋ ይህን ሕግ የማክበር ጉዳይ የሥነምግባር ደንቡን ከመፈረምና ያለመፈረም ጋር የማይገናኝና ሕግን ማክበር የሁሉም ወገን ግዴታ መሆኑን ተረድቶ ለውይይትና ለድርድር በሩን ሊከፍትና የአናሳ ቡድን ድምጾችን ሊሰማ ይገባል::

ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ችግሮች በሠላማዊ አግባብ ለመፍታት በሰከነና በሰለጠነ መንገድ መንቀሳቀስ ከቻሉ አለመግባባቶች፣ አለመተማመኖች እየጠበቡና እየተፈቱ የሚመጡበት ዕድል ይኖራል::■

## ቁጥሮች

**200ሺ ሀ ሜትሪክ ቶን**

በ2007 ዓ.ም ግገር የተፈፀመበት ስንዴ መጠን፣

**80ሺ ሀ ሜትሪክ ቶን**

ከተገዛው ስንዴ እስከ አሁን ወደ ሀገር ውስጥ የገባው መጠን

**267 ዶላር**

በአሁኑ ወቅት ያለው የአንድ ሜትሪክ ቶን ስንዴ ዋጋ፣

ምንጭ
የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ

## መልዕክቶች

### የስብሰባ እና የስልጠና ሀገር

የመንግሥት ሠራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ክልል ከተሞች ጭምር በማምራት በስልጠና ተወጥረው ነው የከረሙት:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በየመስሪያ ቤቱ ሲኬድ በቢሮው ውስጥ የሚገኙት ፀሐፊዎች ብቻ ናቸው:: እነዚህ ፀሐፊዎች ልክ በኮምፒውተር እንደተገጠመ ድምፅ ስብሰባ ላይ ናቸው እያሉ የመጣውን ሁሉ ገና ከበር ይመልሳሉ:: የአለቆች እና ኃላፊዎች ስብሰባ ሲገርመን ደግሞ ሰሞኑን ሰራተኞች በአጠቃላይ ስብሰባ ላይ ናቸው እየተባልን ነው:: መሰብሰቡ ባልከፋ ነገር ግን ሰራተኛው ሁሉ ሳምንቱን ሙሉ ሲሰበሰብ የቢሮውን ስራ ማን ይሰረዋል? እያንዳዳችን በየመስሪያ ቤታችን አንድ ቀን ላልሞላ ጊዜ ስብሰባ ላይ ቆይተን ስንመልስ ስንት ነገር ነው የሚስተጓጎልብን? ስንት ለነገ ሲነጋ ይጠብቀናል? ለነገሩ እነዚህ ሰዎች ስራ ተሰራ አልተሰራ የሚያስጨንቃቸው አይመስለኝም:: በየሴክተሩ አፈፃፀማቸውን ሪፖርት ሲያደርጉ 34 በመቶ፣ 45 በመቶ፣ ከ50 በመቶ በላይ እንደሆነ ይነግሩናል:: እኛም እንሰማቸዋለን:: በየጊዜው እናሻሽላለን ይሉናል፤ እኛም እንጠብቃቸዋለን:: አሁን ግን ተስፋ ቆርጠን መቀመጥ ሳይኖርብን አይቀርም:: ሀገር በስብሰባ እና በስልጠና አይገነባም:: በስብሰባም ሀገር አይመራም:: ጎበዝ ስብሰባ ለመፍትሄ ሲሆን እንጂ ትርፉ ስራ መፍታት ብቻ ነው::

በስልክ የተሰጠ አስተያየት

### ጉዳዩ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም

ከዚህ ቀደም ጀሞ ኮንዶሚኒየም ህንጻው ዘመመብን እያሉ በርካቶች ጩኸታቸውን ሲያሰሙ ጉድ ብለን ነበር:: አሁን ደግሞ ገርጂ ቁጥር አንድ ኮንዶሚኒየም በነዋሪዎች ግድግዳው በላያቸው ላይ እንደወረቀት እየተሰነጣጠቀ መሆኑን በጋዜጣችሁ አስነበባችሁን:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ የችግሩ ተጠያቂ እከሌ ነው እያሉ አንዱ ወደ ሌላው ከማንከባለል ውጭ የነዋሪዎችን ችግር ከቁም ነገርም አልቆጠሩትም:: አርባ አባወራ ማለት በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ ምን ያህሉ ሰው እንዳለ መገመት ይቻላል:: እነዚህ ሰዎች መሽቶ እስከሚነጋ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አያውቁም:: ለሰዎቹ ፈጣን መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ሁሉም እራሱን ነፃ ለማውጣት ሲሯሯጥ ነው እየተመለከትን ያለነው:: ነገር ግን ጉዳዩ የመወንጀያ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም:: ነዋሪዎቹም ቢሆኑ አደጋ ከመድረሱ በፊት ህንፃወን ለቀው ወጥተው በድንኳንም ቢሆን መጠለል አለባቸው:: ከመሞት መሰንበት ይሻላልና እንደአብዛኞቹ ሰዎች ያው ሽራ ወጥረው መቀመጥ እና የሚሆነውን መጠባበቅ ነው ያለባቸው:: ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ እነዚህን ሰዎች ሊታደጋቸው ይገባል:: ከጀሞ ኮንዶሚኒየም ትምህርት ያልወሰደው መንግሥት አሁን ግን ለስራው ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ባይ ነን::

አስቴር - ከገርጂ

"ሰንደቅ" ጋዜጣ በሰንደቅ የሕትመትና የማስታወቂያ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በንግድ ሚኒስቴር በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር 14/673/7498/2004፣
በብሮድካስት ባለሥልጣን የምዝገባ ቁጥር 38/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው

**ዋና አዘጋጅ**
ፍሬው አበበ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 12/201
0911 61 79 35
abebeferew@gmail.com

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ፋኑኤል ክንፉ
0911 865119
Kinfu2006@yahoo.com

**አዘጋጅ**
ፀጋው መላኩ

**ከፍተኛ ሪፖርተሮች**
አሸናፊ ደምሴ
መስከረም አያሌው

**ግራፊክ ኤዲተር**
ነብዩ መሥፍን
0911 18 09 33
nebiyou1st@yahoo.com

**ኮምፒዩተር ጽሁፍ**
አለምነሽ ታከለ
ሰብለወንጌል ንጉሴ
ምናለሽዋ ተ/አረጋይ

**ህትመት ክትትልና ስርጭት**
በዛብህ ተክሉ
0911 41 68 00

**ማስታወቂያ ሽያጭ**
ባይለየኝ ወርቁ
bayleyworku@gmail.com
0921 56 95 03
0912 95 67 95

አታሚ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አድራሻ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 984

የአሳታሚው አድራሻ:- ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/03 የቤት ቁጥር 027 ከአትላስ ሆቴል በስተጀርባ 011-6-62 81 90/ 011-6-18 40 34/ 0911 95 58 16 ፖ.ሣ.ቁ. 80964
www.sendeknewspaper.com

# በፋይናንስ ክፍፍል ረቂቅ ቀመር ተቃዋሚዎች ቅሬታ አላቸው

በጋዜጣው ሪፖርተር




የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የፋይናንስ ድጋፍን አስመልክቶ በተዘጋጀዉ ረቂቅ የክፍፍል ቀመር ላይ ከሀገር አቀፍና ክልላዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ታህሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም በግዮን ሆቴል ያካሄደው የጋራ ምክክር መድረክ ተቃውሞ ገጥሞታል። ቦርዱ አስተያየቱን እንደሚያየው ቃል ገብቷል።

በስብሰባው ላይ የተገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የተቃወሙት የገንዘብ ክፍፍል ቀመሩ ገዥውን ፓርቲ ኢህአዴግን ይበልጥ ተጠቃሚ ለማድረግ ያለመ ነው በሚል ነው። ቦርዱ ባቀረበው ረቂቅ ቀመር መሰረት ከጠቅላላ በጀቱ ለዕጩዎች 25 በመቶ፣ ለሁሉም 10 በመቶ፣ ለሴቶች 10 በመቶ፣ ለፓርላማ ወንበር 55 በመቶ እንዲከፋፈል የተያዘ ነው። ይህ ቀመር የ2002 ምርጫ ኢህአዴግና አጋሮቹ የፓርላማውን ወንበር 99 ነጥብ 6 በመቶ የያዙበት ሁኔታ በመኖሩ፣ በክልሎችም መቶ በመቶ በኢህአዴግ በመያዙ እንዲሁም ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በ547ቱም መቀመጫዎች እጩዎችን ማቅረብ ስለሚችል ቀሪውንም ገንዘብ ጠቅልሎ ይወስደዋል ከሚል ሥጋት ጀምሮ ረቂቁ ኢህአዴግን ለመጥቀም የተቀመጠ ነው እስከሚሉ የቅሬታ አስተያየቶች ተስተናግደዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ2007 ዓ.ም ለሚካሔደዉ አምስተኛ ዙር ጠቅላላ ምርጫ ላይ ለመወዳደር የመወዳዳሪያ ምልክቶቻቸውን የወሰዱ ፓርቲዎች ብቻ የተሳተፉበት ይኸዉ የምክክር መድረክ ላይ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የክፍፍል ቀመሩ እንዲስተካከል በግልጽ ጥያቄ አቅርበዋል።

ለፓለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድጋፍ የሚከፋፈልበትን አሰራር ለመደንገግ የወጣው ደንብ ቁጥር 5/2001 መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበትን መስፈርት ወይም ቀመር እንዲሁም ጥቅም ላይ ስለሚውልበትና ስለሚተዳደርበት ሁኔታ ግልፅ አሠራር በመዘርጋት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል እንደሆነ ይጠቅሳል።

በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ በግልጽ እንደተደነገገው መንግስት ለፖለቱካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ማንኛውም ድጋፍ በፍትሐዊነትና ያለአድልኦ መፈጸም እንዳለበት ቢደነግግም ይህ ግን በተግባር ሊፈጸም እንዳልቻለ ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ይገልጻሉ።

በመመሪያው አንቀጽ 15 ለምርጫ ተግባር የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚሰጥበት መስፈርት ይናገራል። በምርጫ ወቅት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውድድር ባቀረቡት የዕጩ እና የሴት ዕጩ ብዛት የሚሰላ መሆኑን አመልክቷል። ይህም ቀመር ቦርዱ እያዘጋጀ እንደሚቀርብና ለፖለቲካ ፓርቲዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኂላ ወደተግባር እንደሚገባ መመሪያ ላይ ተመልክቷል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጥላሁን እንደሻው ስለጉዳዩ ከሰንደቅ ጋዜጣ ተጠይቀው በስብሰባው ላይ በአካል ያልተገኙ መሆኑን ነገርግን መድረክን ወክሎ ከተገኙ ሰዎች ባገኙት መረጃ መሠረት ቀመሩ አድሎአዊና ሕገወጥ መሆኑን አስረድተዋል። በደንብ ቁጥር 5/2001 መሠረት ያልተከናወነና ሆን ተብሎ ገዥውን ፓርቲ ለመጥቀም የተቀመረ በመሆኑ መድረክ እንደማይቀበለው አስታውቀዋል። ቀመሩ በየዓመቱ ለፓርቲዎች የሥራ ማስኬጃ ከሚደረገው ቀመር ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መቅረቡን ነገርግን በደንቡ መሠረት በዕጩዎችና በሴት ዕጩዎች ብዛት ብቻ መከናወን እንደነበረበት አስረድተዋል።

አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከስብሰባው በኃላ በድረገጹ በለቀቀው መረጃ መሰረት በቦርዱ ቀመር አለመስማማቱን ገልጿል።

አንድነትን በመወከል ስብሰባው ላይ የተሳተፉት የአንድነት ተወካይ አቶ ዳንኤል ተፈራ፣ በበኩላቸው በተለይም ፓርላማና የክልል ም/ቤት ባለ መቀመጫ በሚል የተመደበውን ገንዘብ በኢህአዴግ ለማስረከብ መዘጋጀቱ ተቀባይነት እንደሌለውና እንደገና ራሱን እንዲፈትሽ መጠየቁን ገልፀዋል።

ቦርዱ ቀመሩን የሰራሁት ከ111 ሀገሮች ተሞክሮ ወስጄ ነው ቢልም፣ ተሳታፊዎቹ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እና የኢትዮጵያ ተሞክሮ የሚለያይ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ገዥ ፓርቲ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የማይጨነቅ፣ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት የሚሰራና የይስሙላ ምርጫ የሚያደርግ በመሆኑ ለንፅፅር የሚቀርብ አይደለም። ስለዚህ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ቀመሩን እናውጣ በማለት ምርጫ ቦርድ ያቀረበው የፋይናንስ ክፍፍል ቀመር ውድቅ መደረጉን አስታውሰዋል።

በምርጫ ቦርድ የቀረበውን የፋይናንስ ድጋፍ ክፍፍል ተገቢ ነው የሚል ድጋፍ የሰጠው የኢህአዴግ ተወካይ ብቻ ሲሆን ሌሎች ተሳታፊዎች ተቃውሞ በማሰማትና ቀመሩን ባለመቀበል ኢህአዴግ ብቻውን የቆመበት ስብሰባ ነበር ሲል የአንድነት ፓርቲ ተወካይ አቶ ዳንኤል ተፈራ መናገራቸውን አክሏል።

ሰማያዊ ፓርቲ በበኩሉ በክፍፍል ቀመሩ ኢፍትሐዊነት በመበሳጨት ተወካዩ ስብሰባውን ጥለው እስከመውጣት መድረሳቸውን ይፋ አድርጓል።

ምርጫ ቦርድ ለቀጣዩ ምርጫ የገንዘብ ክፍፍል ቀመር ላይ ለመወያየት በጠራው ስብሰባ ሰማያዊ ፓርቲ ከገንዘብ ክፍፍል ቀመሩ በፊት ምርጫው ፍትሓዊና ነጻ ለማድረግ መወያየት እንደሚቀድም ማሳሰቡን ፓርቲውን ወክሎ በስብሰባው የተገኘው አቶ ጌታነህ ባልቻ ለፓርቲው ልሳን ተናግረዋል።

ሰማያዊ ፓርቲን ጨምሮ ትብብሩን የመሠረቱት ፓርቲዎች ምርጫው ፍትሓዊ እንዲሆን የበኩላቸውን ትግል እያደረጉ እንደሆነ ያስታወሰው አቶ ጌታነህ፤ ታህሳስ 12/2007 ዓ.ም የህዝብ ታዛቢዎችን ለመምረጥ በተደረገው ሂደት የተመረጡት የኢህአዴግ አባላት መሆናቸው፣ ከተመረጡት መካከል የሞቱ ሰዎች ስምም መካተቱ፤ እንዲሁም በህመምና በተለያዩ ምክንያቶች ለመታዘብ የማይችሉ የሚገኙበት መሆኑ፣ የአውሮፓ ህብረትና ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመታዘብ ልምድ ያላቸው ተቋማት ራሳቸውን ማግለላቸው ምርጫው ከአሁኑ ፍትሓዊ እንዳልሆነ እንደሚያሳይና ከገንዘብ ክፍፍሉ በፊት ምርጫውን ፍትሓዊ ለማድረግ መወያየት እንደሚገባ አሳስቧል።

ምርጫ ቦርድ ባቀረበው የገንዘብ ክፍፍል ቀመር መሰረት 10 በመቶ ለሴቶች፣ 10 በመቶ ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል፣ 25 በመቶ ፓርቲዎች በሚያቀርቡት እጩ፣ 55 በፓርላማና በክልል ምክርት ቤት ባላቸው መቀመጫ እንደሚያከፋፍል የተቀመጠ ሲሆን ይህም 99.6 በመቶ ፓርላማ እንዲሁም የክልል ምክርቤትን የተቆጣጠረው፣ ከዚህም በተጨማሪ 547 ተወዳዳሪዎችን ለሚያቀርበው ኢህአዴግ የሚጠቅም ነው በሚል ተቃውሞ ገጥሞታል።

የቅንጅት ሊቀመንበር አቶ አየለ ጫሚሶ በበኩላቸው ቦርዱ ጊዜውን ጠብቆ የፋይናንስ ድልድል የሚከናወንበትን ቀመር ማቅረቡና ማወያየቱ የሚደገፍ መሆኑን በመጥቀስ በረቂቁ ውስጥ አለ ያሉትን ጉድለቶች አስቀምጠዋል። ፓርቲያቸው በፓርላማ ወንበር 55 በመቶ እንዲከፋፈል የተቀመጠው ቀመር ይበዛል ብሎ እንደሚያስብና ይህ ቀመር ወደ 45 በመቶ ዝቅ ብሎ ለሴቶች የተያዘው 10 በመቶ ወደ 15 በመቶ፣ ለዕጩዎች የተያዘው 25 በመቶ ወደ 30 በመቶ ከፍ እንዲል አስተያየት ማቅረቡን ተናግረዋል። ምርጫ ቦርድ ይህንን ቀመር ሲሰራ የደቡብ አፍሪካን ልምድ መመልከቱንና በደቡብ አፍሪካ ለፓርላማ ወንበር 90 በመቶ ቀመር መኖሩን መናገሩን ያስታወሱት አቶ አየለ ነገርግን በደቡብ አፍሪካ ተመጣጣኝ ውክልና በፓርላማ ውስጥ በመኖሩ ብዙ ተቃዋሚዎች ወንበር እንደሚያገኙ፤ በአንጻሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚተገበረው የአብላጫ ድምጽ አሠራር በመሆኑ 99 በመቶ በላይ የፓርላማ ወንበር በገዥው ፓርቲ መያዙን በማስታወስ ንጽጽሩ ተገቢ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

ምርጫ ቦርድ በድረገጹ እንዳሰፈረው ምንም እንኳዋ ቀመሩን እንዲወስን ሥልጣን የተሰጠዉ ቢሆንም ፓርቲዎቹ እንዲወያዩበት እያደረግን ያለነዉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ እንዲጎለብትና አሳታፊ እንዲሆን ነዉ ያሉት በሚኒስትር ማዕረግ የቦርዱ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና ቦርዱ ከፓርቲዎቹ ያገኛቸዉን ሃሳቦች በመጠቀም በቅርቡ ዉሳኔዉን እንደሚያሳዉቅ ገልጸዋል።■

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን ድጋፍ የሚከፋፈልበትን አሠራር ለመደንገግ የወጣ ደንብ ቁጥር 5/2001 የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጥበት መስፈርትን በግልጽ ደንግጓል። አንቀጽ 15 ለምርጫ ተግባር የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚሰጥበት መስፈርት**

1. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት በምርጫ ወቅት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ፣
ሀ. ለፌዴራል ምክርቤት ምርጫ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲው ቀደም ሲል በተካሄደ ምርጫ በፌዴራል ምክርቤት ባለው መቀመጫ ብዛት ወይም
ለ. ለክልል ምክርቤት ምርጫ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲው ቀደም ሲል በተካሄደ ምርጫ በክልል ምክርቤት ባለው መቀመጫ ብዛት መሠረት ይሆናል።

2. የንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም በምርጫ ወቅት የሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ በሚከተሉት መስፈርቶች የሚከፋፈል ይሆናል።
ሀ. የፖለቲካ ፓርቲው ለውድድር ባቀረበው የእጩ ብዛት እና
ለ. የፖለቲካ ፓርቲው ለውድድር ባቀረበው የሴት ዕጩ ብዛት

3. መንግሥት ለምርጫ ተግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ በየጊዜው ቦርዱ እያዘጋጀ በሚያቀርበው ቀመር መሠረት ይመራል። ቦርዱ ያዘጋጀው ቀመር ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያሳውቃል፣ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል።


ቅዱስ ጊዮርጊስ ድራፍት
St. George Beer
መልካም
የገና በዓል
ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ
St. George Beer
PREMIUM
LAGER
BEER
ከሥራ
በኋላ...
18+ ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ የተከለከለ



ዳሽን ባንክ
Dashen Bank

የዳሽን ባንክ አ.ማ ለመላው የክርስትና እምነት
ተከታዮች መልካም የገና በዓል እንዲሆንላችሁ ከወዲሁ
እየተመኘ በዓሉን ምክንያት በማድረግ
ከየትኛውም የዓለም ክፍል

Dahabshiil | EzRemit | MoneyGram | TRANSFAST | XPRESS MONEY | WESTERN UNION

ዓለም አቀፍ ገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች በኩል ከወዳጅ
ዘመድ የተላከን ገንዘብ በአደራ ተቀብሎ በሁሉም አካባቢ ባንኮቹ
እና የውጭ ምንዛሬ ቢሮዎቹ ከልዩ መስተንግዶ ጋር ይጠብቅዎታል፡፡
ፈጥነው ይምጡ . . .
በእርግጥም በአገልግሎታችን ረክተው ፈጥነው ይመለሳሉ!

## መልካም የገና በዓል!

ስልክ (+251) 011 466 1380 ፋክስ (+251) 011 465 3037 dashen.bank@ethionet.et
www.dashenbanksc.com

# ሽግግር፦ ከጋዜጠኝነት ወደ

በፋኑኤል ክንፉ



**አቶ አናኒያ ሶሪ በዓለም ዓቀፍ ግንኙነትና በግሎባል ጥናት የመጀመሪያ ዲግሪ አለው። በጋዜጠኝነት ከሦስት ዓመታት ያላነሰ አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ፓርቲን በደፋ በመቀላቀል እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።**

# “የመንግሥት ጫና ወደ ፖለቲካው እንድገባ ግፊት ፈጥሮብኛል”

**አቶ አናኒያ ሶሪ**

<u>ሰንደቅ</u>፡- ከጋዜጠኝነት ሙያ ወደ ሙሉ ሰዓት ፖለቲከኛነት ያደረከው ሽግግር መነሻው ምንድን ነው?

<u>አቶ አናኒያ</u>፡- በጋዜጠኝነት ውስጥ በቆየንበት ወቅት ከመንግስት ብዙ ጫናዎች ይደርሱብን ነበር። በርካታ ጋዜጠኞችም ከሙያው እንዲወጡ ተደርገዋል። እንዲሁም ተሰደዋል። እኔም ላይ የደረሰው ከዚህ የተለየ አይደለም። ስለዚህ እኔም በግሌ ካጋጠመኝ ተነስቼ ለምን የጋዜጠኛው መብት ይነካል? የጋዜጠኛው መብት ሊከበር ይገባል፣ ወደሚል አተካራ ውስጥ መግባቱ ቀጣይ ሂደት ነው የሚሆነው። የጋዜጠኛውን መብት ለማስከበር በምታደርገው እንቅስቃሴ አውቶማቲካሊ መብት ወደማስከበር እንቅስቃሴ ትገባለህ። ይህ ሲሆን ከጋዜጠኝነትም ከፍ ያለ የአክቲቪስት እንቅስቃሴ ውስጥ ትገባለህ። በዚህም ሳትገደብ ለሌላው መብት ትቆማለህ። በአጭሩ የጋዜጠኛው መብት አለመከበር እና የመንግስት ጫና መበርታቱን ተከትሎ ወደ ፖለቲካው ዓለም እንድቀላቀል ግፊት ፈጥሮብኛል።

<u>ሰንደቅ</u>፡- ፖለቲካና ጋዜጠኝነትን ቀላቅለዋል፤ ድሮም ቢሆን የፖለቲካ ዓላማ ነበራቸው የሚሉ ወገኖች አሉ። በዚህ ነጥብ ላይ ምን አስተያየት አለህ?

<u>አቶ አናኒያ</u>፡- እዚህ ላይ ላጠራ የምፈለገው መሰረታዊ ነጥብ ፖለቲካ በየትኛውም ቦታና ስፍራ ይገኛል። ማንም ሰው ፖለቲካዊ ፍጡር ነው። ይህ ዕውቀት በጣም የቆየ፣ እነአርስቶትልም ያረጋገጡት ነው። ስለዚህም አዲስ ነገር አይደለም፣ ፖለቲካ የትም ስፍራ አለ። ዋናው ነገር መሆን ያለበት ያነገብከው ግብ አብዛኛውን ሕዝብ ሊጠቅም እና ሊያሳትፍ የሚችል ነው? ወይንስ ጥቂቶችን የሚጠቅም ነው? የሚለው ነው መታየት ያለበት የሚመስለኝ።

<u>ሰንደቅ</u>፡- ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉ ይታወቃል። አሁን አጥቼዋለሁ የምትለውን መብት ለማሳካት፣ ከሌሎች ፓርቲዎች አንድነት ለምን ምርጫህ አደረክ?

<u>አቶ አናኒያ</u>፡- አንድነት ልመርጥ የቻልኩበት ምክንያት ወጣት እና ብሩህ ተስፋን የሰነቁ ራዕይ ያላቸው አዳዲስ መሪዎች በመምጣታቸው ነው። በእነሱ ላይ እምነትም እንድጥል ስላደረጉኝም ነው። በአንድነት የበፊት አሰላለፍ ቢሆን ኖሮ ወደ አንድነት የማልመጣበት ሰፊ አጋጣሚዎች ነበሩ። ነገር ግን በአንድነት ውስጥ በተደረገ የአመራር ሽግሽግ አዲስ ኃይሎች መምጣታቸውን ተከትሎ ተስፋ እንዲታየኝ ሆኗል። ሙሉ እምነትም ጥያለሁ። እኔም የበኩሌን አስተዋፆ አደርጋለሁ።

<u>ሰንደቅ</u>፡- የዓለም ዓቀፍ ግንኙነትና የግሎባል ጥናት ባለሙያ ከመሆንህ አንፃር፣ አንድነት የሚከተለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ አንተ ያነሳሃቸውን ችግሮች ይቀርፋል የሚል እምነት አለዎት?

<u>አቶ አናኒያ</u>፡- በዋናነት የዚህች ሀገር ችግር የሚመነጨው ከአፈናና ከአምባገነንነት ነው። ድህነትም፣ ስራ አጥነትም፣ የዕምነት ነፃነት መታጣትም፣ የተለያዩ የሙያ ማሕበራት መዳከም፣ የተቋማት ህልውና አለመኖር፣ እያንዳንዱ የሚመነጨው ከአፈና ነው። ስለዚህም አብዮታዊ ዲሞክራሲ መሰረታዊ ፍልስፍናው የአፈና ፍልስፍና ነው። ጥቂቶች በሕዝብ ስም የሚነግዱበት ነው። ጥቂት አፈቀላጢዎችን በተደላደለ ሁኔታ የሚያስቀምጥ ስርዓት ነው። ስለዚህም ይህን ሂደት መቀልበስ ነው ዋናው ነጥብ ያለው። በተራቀቁ ርዕዮተዓለሞች ልባስ ሳናላብሰው በተራቀቁ የሙያ ቃላቶች ሳናጅበው፣ ኢሕአዴግ አፈናን ይወክላል። አንድነት ነፃነትን ይወክላል። በአፈናና በነፃነት መካከል የሚደርግ ግብግብ ነው።


<u>ሰንደቅ</u>፡- አንድነት በተግባር ያልተፈተሸ፣ በመንግስታዊ መዋቅር ደረጃ ያልታየ፣ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ እየተወዳደረ ያለ ፖለቲካ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንፃር አንድነት ነፃነትን ይወክላል የሚለውን አገላለጽዎን ሰፋ አድርገው ቢያስረዱን?

<u>አቶ አናኒያ</u>፡- አንድነት ሊብራሊዝምን ነው የሚያራምደው። ይህ ርዕዮተዓለም የሚቆምባቸው እሴቶች ደግሞ ነፃነት እና የግለሰብ መብቶች ናቸው። እስካሁን በገዢው ፓርቲ ያየነው አካሄድ ግን የቡድን መብትን አከበራለሁ ይላል፣ ሲያከብር ግን አላየንም። የሙስሊሞች የመብት ጥያቄ አልተመለሰም። የኦሮሞ ብሄር ላይ ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር ተያይዞ በተነሳው ጥያቄ ውይይት ሳይሆን ጥይት በምላሽነት ተሰጥቷል። ስለዚህ በእነዚህ ተጨባጭ ምክንያቶች ስርዓቱ የአፈና መሆኑን አሳይቷል። በተቃራኒው አንድነት የቆመው ለግለሰብ እና ለቡድን መብቶች ጭምር ነው። ይህ ለጊዜው በወረቀት ላይ የሰፈረ ቢሆንም ስልጣን ሲይዝ ተግባራዊ

በገፅ 19

# ፖለቲካ ፓርቲ አባልነት

ከኮተቤ መምራን ኮሌጅ በሥነ-ፅሁፍ ዲፕሎማ፣ ከአ.አ.ዩ. በቲያትር ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪ ወስዷል። በሕትመት ሚዲያ ውስጥ በቼንጅ መጽሄት፣ በሃብል መጽሄት፣ በአዲስ ከተማ ጋዜጣ እንዲሁም አሁን ‘የሚሊዮን ድምፃች’ ጋዜጣ ላይ እየሰራ ነው። በኤፍ.ኤም ሬዲዮ ላይም ለረጅም ዓመታት በሙያው ሰርቷል። የዛሬው እንግዳችን አቶ ስለሺ ሐጎስ በአሁኑ ወቅት በእስር ላይ የምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ እጮኛም መሆኑ ይታወቃል። በቅርቡ ከጋዜጠኝነት ወደ አንድነት ፓርቲ አባልነት ተቀላቅሏል።



## “አትናገር፣ አትፃፍ ማለት ሰው የመሆን ጥያቄን ያስነሳል”

### አቶ ስለሺ ሃጎስ

ሰንደቅ፡- ከጋዜጠኝነት ወደ ፖለቲካ ፓርቲ አባልነትና ተሳትፎ ተሸጋግረሃል። ወደዚህ ውሳኔ እንዴት ደረስክ?

አቶ ስለሺ፡- ከጋዜጠኝነት በይፋ ወደ አንድነት ፓርቲ ተቀላቅያለሁ። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። በሌሎች ሙያም ውስጥ ያሉ ባለሙያዎችም ፖለቲከኛ ይሆናሉ። ዋናው ነገር ወደ ፖለቲካ ውስጥ የሚገቡበት ምክንያቶች ናቸው የሚለያዩት። እኔ በሶስት ምክንያቶች ነው ወደ ፖለቲካ ውስጥ የገባሁት።

ሰንደቅ፡- ምክንያቶችህ ምንድን ናቸው?

አቶ ስለሺ፡- የመጀመሪያው የሃገር ጉዳይ ነው። አሁን ካለሁ ተጨባጭ ሁኔታ ገዢው ፓርቲ የዚህችን ሀገር ሰላምና ደህንነት አረጋግጦ ህልውናዋን ያስቀጥላል የሚል እምነት የለኝም። በተለያዩ ዘርፎች የምታየው ነገር ከግምት ካስገባህ ይህች ሀገር ትቀጥላለች ወይስ አትቀጥልም የሚል ጥያቄ ማንሳትህ አይቀርም።

ሁለተኛው፣ ለጋዜጠኝነት ሙያ ስል ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ የተዘረጋ ስርዓት በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ በቀጥታ ተፅዕኖ የሚያደርግበት ሁኔታ አለው። ከሌሎች ሙያዎች የሚለይበትም ይህ ነው። ወደ ትግልም ያስገባኝ፣ ይህች ሀገር ፍትህ አልባ ከሆነች ፍትህ የለም ብለ ትፅፋለህ። የመልካም አስተዳደር ከጠፋ፣ ጠፋ ብለህ ትጽፋለህ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትፅፋለህ። የተመቸ ሁኔታ ግን የለም። ይህ ሁኔታ ቢመቻችልን ኖሮ ወደትግል ውስጥ አንገባም። ይህች ሀገር ፍትህ አልባ፣ ምግብ አልባ፣ ወደብ አልባ ሆና ታውቃለች። አሁን ደግሞ ፕሬስ አልባ ሆናለች። የመናገር ነፃነት በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ጋዜጠኝነት የለም። በርካታ ጋዜጠኞች በእስር ቤት አሉ። የተሰደዱም የሞቱም አሉ። ይህን የመናገር የመፃፍ ነፃነትን ለመታገል ሌላኛው አማራጭ መደራጀት ነው። የጋዜጠኞች መድረክ ብለን ተደራጅነት ለመታገል ሞክረን ነበር፣ አልቻልንም። ሕገመንግስቱ ቢፈቅድልንም አንድ ኦፊሰር ይህ መብታችንን ይንደዋል። ስለዚህም ለጋዜጠኝነት መብት ብቻ ሳይሆን ሕገመንግስታዊ ስርዓትንም ለማስፈን ወደ ትግሉ ጎራ ገብቻለሁ።

ሶስተኛው፣ ለእራሴ ነው። በጋዜጠኝነት ብቻ አይደለም፣ ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ያላጣሁት የለም። ከከባቢ አየር በስተቀር ያላጣሁት ነገር የለም። ሲፈልግ በንፅህናዋ መቶ በመቶ የምትተማመንባትህን እጮኛህን እስር ቤት አስቀምጦ፣ ሕገመንግስቱ ልታያት ልትጠይቃት ያረጋገጠውን መብት ትነፈጋለህ። እጮኛዬ ርዕዮትን አንድ ዓመት ከስድስት ወር አይቻት አላውቅም። ሚዲያ ተዘግቷል። ስራ እየሰራሁም አይደለም። ስለዚህ እኔ እራሴ ነፃነት ያስፈልገኛል። በእነዚህ ሶስት ምክንያቶች ወደ ፖለቲካው ገብቶ ለመታገል ወስኜ እየተንቀሳቀስኩኝ ነው።

ሰንደቅ፡- በሀገር ውስጥ ካሉት የተለያዩ ፓርቲዎች መካከል ከላይ የዘረዘርካቸው ፍላጎቶችህን ሊያሟላ የሚችለው አንድነት ፓርቲ ነው፣ ከሚል ውሳኔ ላይ እንዴት ደረስክ?

አቶ ስለሺ፡- መጀመሪያ ለመታገል ስትነሳ የምትታገለው ለምንድን ነው የሚል ጥያቄ ታነሳለህ። እኔ የምታገለው የነፃነት ትግል፣ ሀገር የማዳን ትግል ነው። እነዚህን እሴቶች ለመታገል በሚያስችል ቁመና ውስጥ የሚገኙት ምርጫ ቦርድ እንደሚለው ስልሳ ፓርቲዎች የሉም። ሁለት ሶስት ፓርቲዎች ብቻ ናቸው ያሉት። ከዚህ በተጨማሪ የፕሮግራም ጥያቄ ታነሳለህ፣ በእኔ መለኪያ በተለይ ሀገርን የማዳን ትግል የሚለውን አስምሮ እየታገለ ያለው አንድነት ፓርቲ ነው። ለዚህም ነው ምርጫዬ ያደረኩት።

ሰንደቅ፡- “ሀገር የማዳን ትግል” ምን ማለት ነው?

አቶ ስለሺ፡- ሀገር የማዳን ትግል ሲባል በአንድ ሀገር ውስጥ የዜጎች መብት ከታፈነ በሀገር ውስጥ ደህንነት የለም። ከየት እንደሚፈነዳ የማይታወቅ አንድ አደጋ አለ ማለት ነው። ስለዚህም በአንድ ወቅት ሊፈነዳ የሚችልን የዜጎች መሰረታዊ መብትን ለማስቀረት የሚታገል ፓርቲ ነው። ይህ ማለት ለወንበር ብቻ የሚታገል ፓርቲ አይደለም። ጦርነት አልገጠምን ይሆናል፣ መሣሪያም አልያዝን ይሆናል፣ ሆኖም ግን በአንድ ወቅት ሊፈነዳ የሚችል የታፈነ የዜጎች የመብት ጥያቄ እንዳለ ግን ይታየኛል። ታፍኖም እንደማይዘልቅ ጥርጥር የለኝም። አትናገር አትፃፍ ማለት፣ ሰው የመሆን ጥያቄን ያስነሳል።

ሰንደቅ፡- ጋዜጠኛው ታፍኗል አልታፈነም በሚለው የመከራከሪያ ነጥብ ላይ በምክንያትነት የሚጠቀስ አንድ ጉዳይ አለ። ይሄውም በጋዜጠኝነት እና በአክቲቪስት መካከል ያለው የድንበር ልዩነት ባለመሰመሩ አሁን ተፈጥሯል ለሚባለው ውዝግብ በር መክፈቱን የሚያነሱ ወገኖች አሉ። በዚህ ላይ አንተ

በገፅ 19




# የነዋሪዎቹን ህይወት
# አደጋ ላይ የጣለው የኮንደሚኒየም ህንፃ

በቦሌ ክፍለ ከተማ ገርጂ ቁጥር አንድ የኮንደሚኒየም ሳይት በብሎክ ሃያ አንድ ህንፃ ላይ በደረሰው መሰነጣጠቅ ከአርባ በላይ አባወራዎች ህይወት አደጋ ላይ መውደቁን ባለፈው ሳምንት እትማችን በስፋት መዘገባችን ይታወሳል። በወቅቱ የነዋሪዎቹን አስተያየትና የሳይቱን ማህበር ኃላፊ ሃሳብ ያካተትን ሲሆን፤ ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታቸዋል የተባሉትን የመንግስት አካላትም በማነጋገር ሃሳባቸውን ለማካተት ሙከራ አድርገናል። በዚህ ዙሪያ ካነጋገርናቸው የመንግስት ኃላፊዎች መካከል በከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የቤቶች ህንፃ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ መምሪያ ኃላፊ ወይዘሪት ደስታ ሸዋሞላ አንዷ ናቸው። በወቅቱ እሳቸው በስብሰባ ላይ ስለነበሩ ቀደም ብለን አግኝተናቸው ሙሉ ሃሳባቸውን ማካተት የቻልንበት ሁኔታ አልነበረም። መገናኘት የቻልነው ህትመት ልንገባ ሰዓታት በቀሩበት ወቅት ስለነበር የነበረንን ቆይታ በዚህ ዕትም ሙሉ በሙሉ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

በህንፃው ላይ ለተፈጠረው ችግር ነዋሪዎቹም ሆኑ ወይዘሪት ደስታ በምክንያትነት ካስቀመጧቸው ነጥቦች መካከል አንዱ በአካባቢው ያለው መንገድ በአግባቡ እንዲገነባ አለመደረጉ ሲሆን፤ በመንገዱ የሚያልፉ ከባድ መኪኖች በህፃው ላይ ከፍተኛ ንቅናቄ እየፈጠሩ መሆኑ ታውቋል። ነዋሪዎቹ መንገዱ በቂ ክብደት ሊሸከም በሚችል መልኩ እንዲገነባ ለአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በተደጋጋሚ ደብዳቤ መፃፋቸውንም ባለፈው እትማችን መግለፃችን ይታወሳል። በዚህ ጉዳይ ባለፈው ሳምንት የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ስራ አሰኪያጅ ኢንጂነር ፈቃደ ኃይሌን ምላሽ ለማካተት ሙከራ አድርገን የተሳካበት ሁኔታ ባይኖርም፤ በዚህ ሳምንት በሰጡን ምላሽ ከመንገዱ ጋር በተያያዘ ለተፈጠረው ችግር የቦሌ ክፍለ ከተማን ተጠያቂ አድርገዋል።

ኃላፊው የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን መንገዱን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመገንባት በየጊዜው በጀት እየያዘ ለአራት አመታት ያህል ሙከራ ቢያደርግም ክፍለ ከተማው በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በአካባቢው የወሰን ማስከበር ስራን መስራት ባለመቻሉ ግንባታውን ማከናወን አልተቻለም። እንደ ኢንጂነር ፈቃደ ገለፃ፤ መንገዱ የመኪኖቹን ክብደት ሊሸከም በሚችል መልኩ መገንባት ቢችል ኖሮ በቤቶቹ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ንቅናቄ መቀነስ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖር ነበር። አሁንም ቢሆን የአካባቢውን መሰረተ ልማት በወሰን ማስከበር ማንሳት ከተቻለ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን መንገዱን ለመገንባት ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን ገልፀዋል። ከኢንጂነር ፈቃደ ጋር ያደረግነው ቆይታ አጠር ያለ በመሆኑ ወይዘሪት ደስታ የሰጡንን ሀሳብ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

በፀጋው መላኩ



ወ/ሪት ደስታ ሽዋሞላ

ሰንደቅ፡- በህፃው ላይ ችግር እንደተፈጠረ ሪፖርት የደረሳችሁ መቼ ነበር?


ወ/ሪት ደስታ፡- በመስከረም 2007 ነዋሪዎቹ ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ችግሩን አስመልክተው የማመልከቻ ደብዳቤ ጽፈዋል። ደብዳቤውን ያስገቡት ችግሩ በተፈጠረበት ብሎክ ወስጥ ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች ናቸው። ነዋሪዎቹ አንድ ላይ ተፈራርመው ነው ማመልከቻውን ያስገቡት። ደብዳቤው ሚኒስትሩ ጋር ከደረሰ በኋላ በህዳር ወር ነው ወደእኛ የተመራው። በጊዜው ተከታታይ ስልጠናዎች ስለነበሩ ክቡር ሚኒስትሩ ሥራ በዝቶባቸው ነበር። ጉዳዩ አስቸኳይ መሆኑ ስለተገለፀልን እኛ ሐሙስ ዕለት ደብደቤው እንደደረሰን በማግስቱ ችግሩ ተፈጠረ ወደተባለበት ቦታ ሄደናል። ወዲያውኑ ነው ሪፖርታችንን ጽፈን ለክቡር ሚኒስትሩ እንዲቀርብ ያደረግነው።

ሰንደቅ፡- ከእናንተ ክፍል የሄደው ምን አይነት የባለሙያዎች ስብስብ ወይም ስብጥር ነው?

ወ/ሪት ደስታ፡- ደብዳቤው የተመራው በሚነስትሩ ስር ላለው የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ ነው። የእኔ ቢሮ የዲዛይን መምሪያ ቢሮ ነው። የእኛ ቢሮ የተመረጠው ምንአልባት ችግሩን የፈጠረው የዲዛይን ችግር ሊሆን ይችላል በሚል እሳቤ ነው። ከፕሮጀክቶች ግንባታ ጋር በተያያዘ የፕሮጀክቶች ግንባታ ክትትል መምሪያ ነው እንዲያየው የተደረገው። በወቅቱም በተሰጠው ኃላፊነት ከሁለቱ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በስብጥር እንዲያዩት ተደርጓል።

ሰንደቅ፡- በቦታው ከተገኛችሁ በኋላ በምን መልኩ ነበር መረጃዎችን የሰበሰባችሁት?

ወ/ሪት ደስታ፡- በአንድ መልኩ እኛም በቦታው ተገኝተን በዓይናችን የተመለከትነው መረጃ አለ። በሌላ መልኩ ነዋሪዎቹንም በመጠየቅ መረጃ ሰብስበናል። እንደባለሙያም የተደረጉ ሙያዊ ፍተሻዎች አሉ። እኛም የሰበሰብነውን መረጃ አጠናቅረን አቀረብን። ክቡር ሚኒስትሩም ወዲያውኑ ነው ጉዳዩ ለአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ደብዳቤ እንዲፃፍ ያደረጉት።




<u>ሰንደቅ</u>፡- ባለሙያዎቹ በቦታው ደርሳችሁ የራሳችሁን ምርመራ ስታደርጉ ለችግሩ መንስኤ ነው ብላችሁ የለያችኋቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ወ/ሪት ደስታ፡- ችግሩ አንደኛ የአፈር ችግር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ህንፃው ሲገነባ ከመሰረቱ ችግሮች ይኖሩበታል ተብሎ ይታሰባል። ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው ያለው መንገድ ከባድ መኪኖችና ዳም ትራኮች የሚመላለሱበት ስለሆነ በህንፃዎቹ ላይ ከባድ ንቅናቄ የሚፈጥሩበት ሁኔታ አለ።

ከዚህም በተጨማሪ ነዋሪዎች ራሳቸው በኮንደሚኒየም ቤቶቹ ላይ የተለያዩ ማስተካከያዎችን በማድረግ መሠረታዊ የመናጋት ችግር እንዲፈጠር የሚያደርጉበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ ጀሞ ሳይት ላይ ያጋጠመን የህንፃውን ተሸካሚ ምሰሶ የሚቆርጡበት ሁኔታ መኖሩን ነው። አሁን ችግሩ በተፈጠረበት የገርጂ ህንፃ ይሄንን ሁኔታ ባንመለከትም አንድ ቤት ግን ነዋሪዎቹ ግድግዳን አፍርሶ የመቀላቀል ነገርን ተመልክተናል።

በግራውንዱ ባለ አንድ ክፍል የውጪኛውን ግድግዳ በማንሳት ክፍል የመቀላቀል ድርጊትን ታዝበናል። የውጪ ግድግዳንና የውስጥ ግድግዳ ሲነካኩ፤ ሁለቱም በቤቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ቢሆኑም በተለይ የውጪ ግድግዳ ደግሞ የቤቱን ተሸካሚ ምሰሶዎች በማገዝ ክብደቱን ተጋርቶ የሚሸከም የግንባታ ክፍል መሆኑ መታወቅ መቻል አለበት።

የውጪኛውን ግድግዳ ማንሳት ማለት በህንፃው ላይ መሰረታዊ መናጋትን መፍጠር ማለት ነው። የውስጠኛውና የውጪኛው የህንፃው ግድግዳዎች በተለያየ የብሎኬት አይነት እንዲገነቡ የሚደረገውም ለዚህ ነው። የውስጠኛው የክፍሎች መለያያ ግድግዳ እንዲገነባ የሚደረገው በባለአስር ብሎኬት ሲሆን፤ የውጪኛው የህንፃው ግድግዳ ግን በባለሀያ ብሎኬት ነው የሚገነባው። የውስጥ ክፍሎቹ በባለአስር ብሎኬት እንዲከፋፈሉ የሚደረገው ብሎኬቶቹ ከመከለል ባለፈ የህንፃውን ምሶሶ የክብደት ተሸካሚነት ብዙም ስለማይጋሩ ነው። ሆኖም የውጪኛው ግድግዳ በባለሀያ ብሎኬት እንዲገነባ የሚደረገው የህንፃውን ምሰሶ ክብደት በተወሰነ ደረጃ ስለሚጋራ ነው። ይህንን ግድግዳ ማንሳት ማለት ደግሞ በህንፃው ላይ መሰረታዊ መናጋትን መፍጠር ማለት ነው።

<u>ሰንደቅ</u>፡- ደብዳቤው ለአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከተፃፈ በኋላ የእናንተ ቢሮ በቀጣይ የሚያደርገው ክትትል ይኖራል?

ወ/ሪት ደስታ፡- ደብዳቤው ተፃፈ ማለት እኛ ዝም ብለን ቁጭ እንላለን ማለት አይደለም። በቀጣይ ጉዳዩ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰም እንከታተላለን። ደብዳቤው የተፃፈለት አካል የሚያደርገውን ክትትልና የሚወስደውንም እርምጃ በተመለከተ ከራሳቸው ከነዋሪዎቹ ጭምር መረጃ እየወሰድን ክትትል እናደርጋለን። የዚህ ቢሮ ኃላፊነት ሁኔታው የደረሰበትን ውጤት በየደረጃው እየተከታተሉ ሪፖርት ማድረግ ነው።

የእኛ ሥራ ክትትል ማድረግ እንጂ ዞሮ ዞሮ ግን ቴክኒካል የሆነውን ሥራ የሚሰራው የአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ነው። በህንፃው ላይ ከሚታየው መሰነጣጠቅ አንፃር ያለምንም መፍትሄ እስከመጪው ክረምት የሚሄድ ከሆነ ችግሩ እየተባባሰ ነው የሚሄደው። ችግሩም ወደ አደጋ ሊያመራ ይችላል። አደጋው ከደረሰ በኋላ አንዱ አካል ሌላውን ጥፋተኛ አድረጎ ጣት ከመጠቋቆም ችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ እንደሚያስፈልገው አውቆ በአፋጣኝ እርምጃ መውሰዱ የተሻለ ነው የሚሆነው።

<u>ሰንደቅ</u>፡- ህንፃውን በተመለከተ በቀጣይ ሊወሰድ የሚችለው እርምጃ ምንድን ነው ተብሎ ይታሰባል?

ወ/ሪት ደስታ፡- ችግሩ መሰረታዊ ነው። መፍትሄም የሚያስፈልገው በዚያው በችግሩ ስፋት መጠን ነው። ነዋሪዎቹ ህንፃው መሰነጣጠቅ ሲጀምር ችግሩ ቀለል ያለ መስሏቸው ክፍተቶቹን በአሸዋ የመሙላትና በሲሚንቶ የመቀባባት ስራ ሲሰሩ ነበር። ይህ ግን መሰረታዊ መፍትሄ አይደለም። ለህንፃው መሰረታዊ መፍትሄ ሊሰጠው ነው የሚገባው። ለምሳሌ በጀሞ ሳይት አንድ ያዘመመ የኮንደሚኒየም ህንፃ ነበር። በወቅቱም በህንፃው ውስጥ የነበሩት ሰላሳ ቤተሰቦች እንዲወጡ ተደርጎ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመነጋገር፤ ጥናቱ ተሰርቶ በአሁኑ ሰአት ምን መደረግ አለበት ወደሚለው መደምደሚያ ላይ እየደረስን ነው። በዚህም መሰረት ለገርጂው ህንፃ የሚያስፈለገው መሰረታዊ መፍትሄ በዚህ መልኩ የሚታይ ነው የሚሆነው።



<u>ሰንደቅ</u>፡- ከአፈር ጋር በተያያዘ እንደ አንድ ችግር ሲነሳ በአካባቢው በርካታ የኮንደሚኒየም ቤቶች የተገነቡ ከመሆኑ አንፃር በሌሎቹ የኮንደሚኒየም ህንፃዎች ላይ ተመሳሳይ ችግር ላለመፈጠሩ ዋስትናው ምንድነው?

ወ/ሪት ደስታ፡- የአፈር አይነት በመቶ ሜትር ራዲየስ ስፋት ውስጥ ስለሚለያይ ከአፈር ጋር በተያያዘ አንድ ህንፃ ላይ ችግር ተፈጠረ ማለት ሌሎቹ ህንፃዎች ተመሳሳይ ችግር ይገጥማቸዋል ማለት አይደለም። አሁን ከተሰነጣጠቀው ህንፃ ጎን ያለ ብሎክ ሃያ ሁለት ከብሎክ ሃያ አንድ ይልቅ ለመንገዱ የቀረበ ነው። ሆኖም በዚያ ህንፃ ላይ ያየነው ምንም አይነት የመሰንጠቅ ምልክት የለም። ከዚህ በመነሳት ነው ብሎክ ሃያ አንድ፤ የራሱ የሆነ ቴክኒካል ችግሮች ጭምር ይኖሩበታል የሚል ግምትን ለመውሰድ የቻልነው።

<u>ሰንደቅ</u>፡- ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ችግሮች ተከስተው ለእናንተ ሪፖርቶች የቀረቡበት ሁኔታ አለ?

ወ/ሪት ደስታ፡- እስካሁን የቀረበው በጀሞ ሳይት የዘመመው የኮንደሚኒየም ህንፃ ነው። ከዚህ ውጪ ግን እስከአሁን የቀረበ መሰል ሪፖርት የለም።

<u>ሰንደቅ</u>፡- በቤቶቹ አሰራር ወይንም በሌሎች ውጫዊ ምክንያቶች በቤቶቹ ሳይ የሚፈጠሩ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ውጪ ግን ነዋሪዎች ክፍሎችን በመቀላቀልና አንዳንድ የውስጥ ለውስጥ የማስተካከያ ስራዎችን በመስራት ህፃዎቹ ሳይ ጉዳት እንዳያደርሱ ምን አይነት የክትትልና የቁጥጥር ዘዴ አለ?

ወ/ሪት ደስታ፡- በዚህ በኩል እያንዳንዱን ሳይትና ብሎክ በመንግስት ደረጃ መቆጣጠር አይቻልም። አስተዳደሩን አስመልክቶ በዋነኝነት ይመለከታቻቸዋል ተብሎ የሚታሰበው በየሳይቱ ያሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማህበራት ናቸው። የአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትም ሆነ የቤቶች ማስተላለፍ ኃላፊነት ቤቶቹን መስራትና ማስተላለፍ ነው የሚሉት። መሆን ያለበት ግን እነዚህ አካላት ቤቶቹን ከመስራትና ከማስተላለፍ ባለፈ ከማህበራቱ ጋር በጋራ በመሆን መሰል ችግሮች እንዳይፈጠሩ መከላከል የሚቻልበትን የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ነው። ከእኛ መምሪያ ውጪ ወደ ቦታው የተንቀሳቃሽ የከተማ ቤቶች መረጃ የሚባል ክፍል ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ በዚያ መምሪያ በኩል ሰፊ ሥራ መሥራት ያለበት እንደሆነ ነው የተረዳነው።

ገና በወሬ ደረጃ ቢሆንም ከማህበሩ አመራሮች ያገኘናቸው መረጃዎች የሚያመለክቱት ቤቶች ውስጥ ለውስጥ የሚቀላቀሉበት ሁኔታ መኖሩን ነው። አንድ ሰው ዕጣ ሲደርሰው፣ ሲከራይ ወይም ሲገዛ ከጎኑ ባዶ ቤት ካለ ሁለቱን ቤት ውስጥ ለውስጥ የመቀላቀል ስራ እንዳለ ነው የነገሩን። ይሄንን ጉዳይ በተጨባጭ መረጃ ለማስደገፍ በቀጣይ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ይኖራሉ።

<u>ሰንደቅ</u>፡- የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ እንዲህ እንደአሁኑ ከመስፋፋቱ በፊት በቀጣይ ለሚገነቡት ቤቶች በሞዴልነት የሚያገለግሉ ቤቶች ተገንብተው ነበር። ሌሎቹ ቤቶች እነዚህን ሞዴል ቤቶች ተከትለው መገንባት ሲገባቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚገነቡት ቤቶች ግን የመጥበብ ሁኔታ ይታይባቸዋል የሚሉ ሰዎች አሉ። በእርግጥ እነዚህ መኖሪያ ቤቶች ለመኖሪያነት በሚበቃ የስፋት ደረጃ ባለመገንባታቸው፤ ነዋሪዎች ተጨማሪ ቦታን በመፈለግ የመቀላቀል ድርጊት ውስጥ እንዲገቡ አያደርጋቸውም?

ወ/ሪት ደስታ፡- ይሄ ሊታሰብ አይቻልም። መሰረታዊው ችግር ቤቶቹን በተመለከተ መረጃን በተገቢው መልኩ የመያዝና የመቆጣጠሩ ጉዳይ ነው።


በእውነቱ ለመናገር ቤቶቹን ሰርቶ ከሚያስተላልፈው አካል ምን ያህል ቤት ተሰራ፣ ምን ያህሉ ቤት ተላልፏል፣ ምን ያህሉ ቤትስ ክፍት ነው የሚለው መረጃ በአብዛኛው አይታወቅም። መሰረታዊው ችግር እዚህ ጋር ነው። ብዙውን ጊዜ የቤቶቹን መረጃ በተመለከተ ለሌሎች ግብአትነት የሚያገለግሉ መረጃዎችን ስንጠይቅ መረጃው በትክክል እንደማይታወቅ ነው የሚነግሩን።

እነዚህ መረጃዎች በትክክል አለመኖራቸው ሰዎች ቤቶቹን እየቀላቀሉ እንዲጠቀሙ ፍላጎት ሊያሳድርባቸው ይችል ይሆናል እንጂ፤ ከሚጠቀሙባቸው ቤቶች ስፋት በቂ አለመሆን ጋር የሚያያዝ ነው ሊባል አይችልም። ቤቶቹ የሚሰሩት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናቶች ከተደረጉ በኋላ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ነዋሪዎች ቤቶቹ በዕጣ እንዲደርሷቸው የሚደረገው በተመዘገቡባቸው የቤት ዓይነቶች በመሆኑ የስፋትና የጥበት ጉዳይ እንደ አንድ የችግር መንስኤ ተደርጎ ሊነሳ የሚችል አይደለም። በዚህ ላይ ነዋሪዎች የሚወስዷቸው ቤቶች የከፈሉባቸው ሆኖ ሳለ፤ ያልከፈሉባቸውን ቤቶች መውሰድ ለእኔ ወንጀል ነው።

<u>ሰንደቅ</u>፡- የቤቶቹ ግንባታ ከመከናወኑ በፊት የሳይት መረጣ ላይ የሚሰራው ስራ ምን ያህል ጥንቃቄ የተሞላበት ነው። ቤቶቹ ተገነቡ፤ ይሁንና በአካባቢው ደግሞ ፋብሪካዎችና ሌሎች ግንባታዎች ይታያሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአካባቢው የሚያልፉ ከባድ ተሽከርካሪዎች ችግር እየፈጠሩ መሆኑን ከነዋሪዎቹ ተረድተናል። በዚህ ረገድ ይህ ሳይት ማሳያ ሲሆን ይችላል። በሌሎች የኮንደሚኒየም ሳይቶች ሳይስ መሰል ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመኖሪያ አካባቢ የግንባታ ሳይት ሲመረጥ ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች የሉም?

ወ/ሪት ደስታ፡- ቤቶቹ የተሰሩት በሞዴል ደረጃ ነው። በአሁኑ ሰዓት በዚያ ቦታ የከባድ መኪኖች ምልልስ ሊበዛ የቻለው በአካባቢው የአርባ ስልሳ ቤቶች ግንባታ በመጀመሩ ነው። ይህ ደግሞ ሁልጊዜም የሚቀጥል አይደለም። የፕሮጀክቱ ግንባታ ሲያልቅ አብሮ ሊቆም የሚችል በመሆኑ እንደዘላቂ ስጋት ሊታይ የሚችል አይደለም። ፋብሪካዎቹን በተመለከተ ብዙም መረጃ የለኝም። እኛ ለምርመራ በሄድንበት ወቅት ከባድ መኪኖቹ በአካባቢው ሲያልፉ ሴፕቲክ ታንክ ላይ ቆመን የነበረውን ንቅናቄ በሚገባ ተረድተናል። የቤቶቹን የግንባታ ሳይት መረጣ በተመለከተ ግን ያለ ጥናት የሚሰራ ነገር የለም።

*የፕሮጀክቱ ግንባታ ሲያልቅ አብሮ ሊቆም የሚችል በመሆኑ እንደዘላቂ ስጋት ሊታይ የሚችል አይደለም። ፋብሪካዎቹን በተመለከተ ብዙም መረጃ የለኝም። እኛ ለምርመራ በሄድንበት ወቅት ከባድ መኪኖቹ በአካባቢው ሲያልፉ ሴፕቲክ ታንክ ላይ ቆመን የነበረውን ንቅናቄ በሚገባ ተረድተናል*



# ትልቁ “ብላቴና”

በአሸናፊ ደምሴ

“ብላቴና” ፊልም ባሳለፍነው ሳምንት በይፋ የተመረቀ የቤተሰብ ፊልም ነው:: ገና በብላቴናነቱ የተቸገሩ ቤተሰቦቹን ለመርዳት የሚታትርን ህፃን፤ በተማረበትና በተመረቀበት ትምህርት መስክ (የተመረቀበት ትምህርት ምን እንደሆነ በግልፅ ባይታወቅም) ስራ አጥቶ የሚንከራተትን ወጣት ህይወትና ልጆቿን ለማሳደግ ጉሊት የምትቸረችርን እናት ታሪክ የሚተርክ ፊልም ነው::

ቤተሰቡ ችግር ያልፈታው፣ ማጣት ያልበገረው፣ ፍቅር ያልነጠፈው፣ ተስፋን የሰነቀ ተደርጎ ተስሏል:: ተመርቆ በስራ ፍለጋና ዕጦት ሲንከራተት የሚታየው ዘላለም (ታሪኩ ብርሃኑ) ፈገግ በሚያስብሉ አጋጣሚዎች መካከል ሁሉ ሸንቆጥ የሚያደርጉ ማህበራዊ ሂሶችን በፊልሙ ውስጥ ያሳየናል:: ለዚህም በልምድ ጥየቃ የተሰላቹ ጀማሪ ስራ ፈላጊዎች የሚገጥማቸውን አበሳ ፊልሙ ፍንትው አድርጎ ያሳያል::

ብላቴናው አቢ (እዮብ ዳዊት) ከትምህርቱ በምትተርፈው ጊዜ ሁሉ ሊስትሮ ሰርቶ፣ ማስቲካ አዙሮ፣ ዕቁብ ገብቶ የቤተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ሲታትር ማየት በፊልሙ የታየ አዲስ መንገድ ነው:: የእናታቸው ደግነሽ (ፍቅርተ ደሳለኝ) ድንገት በተፈጠረ እና ስሩን የጉበት በሽታ ምክንያት መሞት የሁለቱን ወንድማማቾች ህይወት የበለጠ ሲያመሰቃቅለው እናያለን:: ዳሩ ግን “ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች” እንዲሉ፤ የእናታቸውን የደም ምርመራ ውጤት ተከትሎ በተሰራ ሌላ ምርመራ በተለይም ብላቴናው ሄፒታይትስ “B” በተሰኘው የጉበት በሽታ የተጠቃ መሆኑና ለህክምና ከ20 ሺህ ብር በላይ እንደሚያስፈልግ መታወቁ የታሪኩ ጡዘት መጀመሪያ ይሆናል::

“በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” ይሉት ነገር ወንድማማቹ ከእናታቸው ሞት በኋላ የህክምናው ነገር ሲያምሳቸው ይታያል:: በዚህም በዘርፉ በህክምናው ሊደረግ የሚገባውን የተሻለ ህክምና ሁኔታ እንዲመቻች በመጠቆም፤ የችግረኛ ቤተሰቦችን እንግልት የት ይደርስ እንደሆነ “ብላቴና” ፊልም ያሳየናል::

ለዓመታት ተምሮ እንጀራውን በየመስሪያ ቤቱ የሚያድነው ዘላለም፤ በታዋቂ ቡና ቤቶች ውስጥ በዘውግ ዳንስ የምትታወቅን ቲና (ብርክት ሃይማኖት) ወጣት መተዋወቁ ጋሬጣ የበዛበትን መንገድ ሲደላድልለት እናያለን:: ለወንድሙ (ለብላቴናው) የበሽታውን አይነትና ደረጃ ያልተናገረው ዘላለም ዕረፍት የሚያስፈልገውንና ታታሪውን ህፃን ከቤት እንዲውል በማድረግ በሊስትሮና በማስቲካ ንግድ ለውጥ ለማምጣት ሲጣጣር ማየቱ

**አቅራቢው - በሸገር ፊልም ፕሮዳክሽን**

**ኤዲተር -ይታየው አምላክ ዘርጋው**

**መብራትና ረዳት ካሜራ - መብራቱ ዮሐንስ**

**ድምፅ - ብዙአየሁ አበራ**


**ዳይሬክተር ኦፍ ፎቶግራፊ - ሲዳኪያል አየለ**

**ዲዛይነርና ማናጀር - መታሰቢ ሸንቁጤ**

**ማጀቢያ ሙዚቃ - ሱልጣን ኑሪ**

**ተዋንያን - ታሪኩ ብርሃኑ፣ እዮብ ዳዊት፣ ፍቅርተ ደሳለኝ፣ ብርክት ሃይማኖት፣ ኤፍሬም ሙላቱ፣ መቅደስ መልካሙ፣ አመኑ ሚጀና እና ሌሎችም**

**ደራሲ እና ዳይሬክተር - ክንፈ ባንቡ**




*ለቤተሰቡ ኑሮ ከአቅሙ በላይ ሲለፋ የሚታየው “ብላቴና” በስተመጨረሻም በተለያዩ ሰዎች መካከል ፍቅርን፣ አንድነትን፣ መተሳሰብን፣ ተስፋን በሚገባ እንዲታይ አድርጓል። የሀብቱን ሽራፊ በመስጠት የጉበት ህክምናውን ተከታትሎ መድሃኒቱን እንዲያገኝ ያደረገው ባለሀብት ለወንድሙም የእንጀራ መንገድ ሲቀጥልም እናያለን።*

የተመልካችን ሀሳብ የሚፈታተን ትዕይንት ነው:: ለክብሩ ብዙ ሲጨነቅ የምናየው ይህ ገፀ-ባህሪይ ከወንድሙ ህይወት የሚበልጥ ነገር የለምና ራሱን ዝቅ አድርጎ ሲሰራ ማየቱ የወንድማማቾቹ ፍቅር ያሳየናል::

ድህነት የቱንም ያህል ቢከብድ ጠንካራ ስብዕና ያለው ሰው ፀንቶ እንደሚቆይ ያሳየው “ብላቴና” ፊልም፤ በተለይም ለመድሃኒት መግዣ የቸገረው ወጣት በምሽት ማጅራት መቺነት ተሰማርቶ ገንዘብ ለማግኘት ሲሞክር የሚገባበትን የህሊና ፈተና ፍንትው አድርጎ ያሳያል::

በ“ብላተናው” የጉበት ህመም ምክንያት ቤተሰቡ አለኝ የሚለውን ንብረት ሁሉ በሰጥም መድሃኒቱ በቅርበት ለማግኘት ያለውን ፈተናና ስለበሽታው አፅንኦት ሰጥቶ መጠቆም የቻለ ፊልም ነው:: በዚህም ኪነ-ጥበብ (በተለይም ፊልም) ሊጫወተው የሚችለውን (የሚገባውን) ማህበራዊ ፋይዳ በማጉላት አሳይቶናል:: ከበሽታው በተጨማሪ በማህበረሰባችን ውስጥ የእዝን ስነ -ሥርዓት በሚገባ አመላክቷል::

ለቤተሰቡ ኑሮ ከአቅሙ በላይ ሲለፋ የሚታየው “ብላቴና” በስተመጨረሻም በተለያዩ ሰዎች መካከል ፍቅርን፣ አንድነትን፣ መተሳሰብን፣ ተስፋን በሚገባ እንዲታይ አድርጓል:: የሀብቱን ሽራፊ በመስጠት የጉበት ህክምናውን ተከታትሎ መድሃኒቱን እንዲያገኝ ያደረገው ባለሀብት ለወንድሙም የእንጀራ መንገድ ሲቀጥልም እናያለን::

“ብላቴናው” ፊልም የወንድማቾችን ፍቅር፣ የተስፋ ማጣትን ስቃይ፣ የማህበረሰባችንን አስተዋይነትና ቁስል በመጎንጎን የሚያሳይ ፊልም ነው::

ያም ሆኖ ግን በተመልካቹ ዘንድ ጥያቄን የሚያጭሩ ሃሳቦች መከሰታቸው አይቀርም:: አንድ ሁለቱን ለመጥቀስ ያክል፤ የትንሽ ትልቁ “ብላቴና” ይህን መሰል ሃይል ከየት የመጣ እንደሆነ ጥቂትም ቢሆን በገፀ- ባህሪው ግንባታ ወቅት ሥነ-ልቦናዊ ጥቆማ ቢኖረው መልካም ነው:: በሌላ በኩል ፊልሙ የሥራ አጥነትን ምን የማሳየቱን ያህል፤ ስራ ለማግኘት ሰው እንደሚያስፈልግ ማሳየቱ ደግሞ በብዙዎች ልብ ውስጥ ተስፋ መቁረጥ መፍጠሩ ፊልሙን ጎርባጭ ያደርጉታል:: ይህም ሲባል በአንዲት ሴት አማካኝነት ያሳየውን ታሪክ ደግሞ በዚህም ማሳየቱ ብቸኛ የስራ ማግኛ መንገዱ “ዘመድ/ሰው” ነው የሚያስብል ይሆናል:: ነገር ግን ባለታሪኩ ዘላለም በራሱ ጥረት ተወዳድሮ ስራ ሲያገኝ ብናይ መልካም ይሆን ነበር::

በተረፈ ግን ድህነት በሚያንከራትተው ማህበረሰብ ስር ጥቂት የማይባሉ ባለሀብቶች ብራቸውን የትም ሲረጩ የሚያሳየን፤ የተማረ የሰው ሃይል ያስፈልጋታል በምትባል ሀገር የተማረው ወጣት በልምድ ዕጦት የሚታመስባት ሀገር፤ በችግርም መካከል ቢሆን ቅን መንፈስ ያልሞተ መሆኑን የሚያሳይ ፊልም ነው ብላቴና::

በኪዳኔ መካሻ
Kidane1983@yahoo.com

# ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት

## - ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር እና ሕጋዊ ውጤቱ፣

## -ጋብቻ ፈፅሞ ባልና ሚስት ከመሆን ጋር ያለው ልዩነ፣ት

## - በልጆች እና በንብረት ሳይ ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር የሚፈጥረው ውጤት ምን ይመስላል?

እንዴት ናችሁ ሰላም ነው? እንኳን ለክርስትና እምነት ተከታዮች በሰላም አደረሰን። የዛሬው የሕግ ወጋችን የሚያጠነጥነው በቤተሰባዊ ጉዳይ ላይ ነው። በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ሕጋዊ እውቅና ከተሰማቸው ቤተሰባዊ ግንኙነቶች ውስጥ ጋብቻ አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ነው። ለመሆኑ ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር ከጋብቻ ፈፅሞ አብሮ ከመኖር የሚለየው ምንድን ነው? ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር የሚያስከትላቸው ውጤቶች ምን ይመስላሉ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራን። ለማሳያነትም እስከ ፌሬል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሱ ሁለት ጋብቻ ሳይፈፅሙ አብሮ መኖር የሚመለከቱ ክርክሮችን እናነሳለን።

1. ሚስት ወይም የቤት ሰራተኛ

ወ/ሮ የዝና እና መምህር ጥሩ አየሁ ወደ ኋላ ላይ የጋብቻ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ክርክር ቢያስነሳም ግንኙነታቸው የተጀመረው በ1972 መምህር ጥሩአየሁ ወ/ሮ የዝናን በቤት ሰራተኛነት በመቅጠራቸው ነበር። ቀስ በቀስ አንድ ቤት አብሮ ለመኖሩ መላመዱ መጣና 5 ልጆችን ወለዱ። ለ25 ዓመታት እስከ 1997 ዓ.ም አብረው ኖሩ። መምህር የት ያገባሁሽን ነው" በሚል ወ/ሮ የዝና የሚስትነትን ወጉንም ግዴታቸውንም ነፈጓቸው።

በዚህ ቅር የተሰኙት ወ/ሮ የዝና ለደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት ለ25 ዓመታት 5 ልጆች ወልጄለት አንድ ላይ ኖረን እንደ ሚስት አልቆጠረኝምና ቀርቦ ይጠየቅልኝና ሚስትነቴ ወይም የቤት ሠራተኝነቴ ይለይልኝ ሲሉ ክስ አቀረቡ።

መምህር ጥሩአየሁ 25 ዓመት አብረን ኖረናል፣ 5 ልጆችም ወልደናል። ነገር ግን የቀጠርኳት የቤት ሰረተኛዬ እንጂ ያገባኋት ሚስቴ አይደለችም። ስለዚህ ሚስት ነኝ ስትል ያቀረበችው ክስ ውድቅ ይደረግ ብለው ተከራከሩ። ፍ/ቤቱ በሁለቱም በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ሰማ። ከወ/ሮ የዝና ምስክሮች አንዱ የተከሳሹና የከሳሿ የበኩር ልጅ ነበር። "አባትና እናቴ ባልና ሚስት ናቸው ብዬ አምናለሁ" ሲል መሰከረ።

የደብረ ማርቆሱ ፍ/ቤት በመምህር ጥሩአየሁና በወ/ሮ የዝና መካከል የተመሰረተ ጋብቻ የለም። ስለዚህ ሚስት አይደሉም ሲል ወሰነ። ወ/ሮ የዝና በውሳኔው ቅር ተሰኝተው በየደረጃው እስከ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ጋብቻ ያላችሁም ሚስት አይደለሽም የሚለው ውሳኔ ፀናባቸው።

መስከረም 12/2000 ዓ.ም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታው ጋብቻ የለም ቢባልም ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት አብረን መኖራችንን እንዲረጋገጥልኝ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ በመደረጉ የሕግ ስህተትን በስር ፍ/ቤቶች ተፈፅሟል። ስለዚህ ይሻርልኝ የሚል ነው። ሰበር ክርክሩን መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ ከማየታችን በፊት አንድ ሌላ ክርክር እንጨምር።

2.በድግስ ላይ የታወጀው ጋብቻ

ጥር 15/1976 የባህል ሀኪሙ ሀኪም ኪዳነወርቅ በቤታቸው ባዘጋጁት ድግስ ላይ በተጠራው እንግዳ አንድ ነገር አሳወቁ። ከዛሬ ጀምሮ ወ/ሮ መሠረት ሚስቴ ናት ሲሉ አሳወቁ። ከዚያ በፊት ወ/ሮ መሠረት በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቁት በሀኪም ኪዳነወርቅ ጋር በረዳት የባህል ሀኪምነት ተቀጥረው ሲሰሩ ነበር። ከዚያን ቀን በኋላ አብረው ኖሩ፣ ልጅም ወለዱ ሀኪም ኪዳነወርቅ በ1994 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

ወ/ሮ መሠረት በፌ/የመ/ፍ/ቤት ቀርበው ሚስትነታቸውን አስወስነው እያለ ወ/ሮ የሻረግ መቃወሚያ አቀረቡ። የሀኪም ኪዳነወርቅ ሚስት እኔ ነኝ። ወ/ሮ መሠረት የሚች ሠራተኛ እንጂ ሚስት አልነበሩም። ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ አሉ።

ፍ/ቤቱ የወ/ሮ መሠረትንና የወ/ሮ የሻረግን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሚች ሀኪም ኪዳነወርቅ ወ/ሮ መሠረት ሚስቴ ናት ብለው በድግስ ላይ ለተሰበሰበው ሰው ተናግረዋል። ከዚያም አብረው ኖረው ልጅ ወልደዋል። ወ/ሮ የሻረግ ያቀረቡት ማስረጃ ይሄን የሚያስተባብል ባለመሆኑ አልተቀበልኩትም ሲል ወሰነ።

ወ/ሮ የሻረግ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቀረቡ። ይግባኙ ሚች ድግስ ደግሰው ወ/ሮ መሠረት ሚስቴ ናት ቢሉም በፅሑፍና በሽማግሌዎች ፊት ስላልተረጋገጠ የተባለው ጋብቻ ባህላዊ የጋብቻ ሥርት የተፈፀመ አይደለም አለ። ፍ/ቤቱም የወ/ሮ መሠረት ሚስትነት በጋብቻ ምስክር ወረቀት ወይም በትዳር ሁኔታ አልተረጋገጠም በሚሉት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሻረው።

ወ/ሮ መሠረት በተራቸው ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቀረቡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሐኪም ኪዳነ ወርቅ ድግስ ደግሰው ወ/ሮ መሰረትን ሚስቴ ነች ማለታቸው አብረው ኖረው ልጆች መውለዳቸውን ወ/ሮ መሠረት ስላስረዱ ጋብቻው መኖሩ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 97(2) መሠረት ተረጋግጧል። የስር ፍ/ቤት ለባህላዊ ጋብቻ የሰጠው ትርጉም ስህተት ነው በሚል የከ/ፍ/ቤትን ውሳኔ ሻረው።

ወ/ሮ የሻረግ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ለመሻር የሰበር አቤቱታ አቀረቡ። በ1976 ሊያውም አዲስ አበባ በሽማግሌ ፊት ፊርማ ሳይፈረም ባህላዊ ጋብቻ ተፈፀመ ሊባል አይችልም። ወ/ሮ መሰረት የሀኪም ኪዳነወርቅ ሰራተኛ ሆነው ደመወዝ ይቀበሉ ነበር። በ1980 ከሀኪም ኪዳነወርቅ ተለይተው አቶ ሽፈራውን አግብተው 2 ልጆች ወልደዋል ስለዚህ ሚስት መባላቸው ስህተት ነው ይታረምልኝ አሉ። ወ/ሮ መሰረት በበኩላቸው የፌ/ጠ/ፍ/ቤትን ውሳኔ የሚያጠናክር ክርክር አቀረቡ። ሰበር ክርክሩን መርምሮ ለሰጠው ውሳኔ በፊት የቤተሰብ ሕጉን ድንጋጌዎች እናስቀድም

### ሳይጋቡ በትዳር መኖር

የፌዴራሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀፅ 94 ላይ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለ መኖር በሰጠው ትርጓሜ "አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈፅሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው" ይላል።

በአንቀጽ 99 ላይ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልናሚስት ኖሩ ለማለት የሚያስፈልገው "በትዳር መልክ መኖር" በሕግ የተጋቡ ሰዎች አይነት ሁኔታ ወንድና ሴቷ ማሳየት እንዳለባቸውና ይህ ሁኔታ ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው ኖረዋል ለማለት አስፈላጊና በቂ መሆኑን ይገልፃል። ለሌሎች ሰዎችም ሳይጋቡ ባልና ሚስት ሆነው ግንኙነታቸውን እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አለመሆኑንም ያሰምርበታል።

በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች አይነት ሁኔታ ማሳየት ወይም በትዳር መልክ አብሮ መኖሩ እንጂ በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈፀማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ባይጋቡም የባልና የሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አለመሆነና በአንቀጽ 99 (3) ላይ ተደንግጓል።

ይህ ግንኙነት ከጋብቻ ከሚለይባቸው ነገሮች አንዱ የጋብቻ ዝምድናን ባለመፈጠሩ ሲሆን ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ወንድና ሴት በዘመዶቻቸው መካከል ግንኙነታቸው አንዳችም ዝምድና እንደማይፈጥር የተ/የቤ/ሕ/አ 100 (1) ይደነግጋል። ይሁን እንጂ በተጋቡ ሰዎች መካከል ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች (የሚስትን እህት እናት ልጅ ማግባት) ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከልም አብረው እስከመኖሩ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል።

የጋራ ንብረት፡- በጋብቻ ላይ ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ የሚያፈሯቸው ንብረቶች ገቢዎቻቸው የጋራ ሀብት ሲሆኑ ጋብቻ ባይፈፅሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ግን ከሶስት አመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ የሚያፈሩት ንብረት የጋራ ተደርጎ እንደሚገመት በአንቀፅ 1021 ይደነግጋል።

ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ እያንዳንዳቸው እንደ አቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በአንቀፅ 101 ላይ የሚገደዱ ሲሆን፤ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖራች ንብረቶች በግንኙነት ውስጥ እንደተፈሩ የሚቆጠሩትም ንብረቶች የግል ወይም ከግንኙነቱ በፊት የተፈሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበባቸው ነው።

በጋብቻ ላይ በግል የሚመጣ እዳ ከግል ሀብት የሚከፈል ሲሆን በዚ ካልተሸፈነ ወደባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ማስከፈል ይቻላል። ብድርም ሆነ እዳ ስጦታ ሲደረግ ሁለቱም ከተወሰነ ገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ መስማማት አለባቸው። ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው እዳዎች ለጋራ ኑሮአቸው ለልጆቻቸው መሠረታዊ ፍላጎቶች የተገቡ ሲሆኑ ለእዳው አከፋፈል ሁሉም በአንድነት በነጠላ ተጠያቂነት አለባቸው።

ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት የሚኖሩ ወንድና ሴት የጋራ ሀብት ካፈሩ የንብረቱን አስተዳደር የ3ኛ ወገን እዳ አከፋፈልና የንብረት ማጣራት ከጋብቻ ውስጥ ከሚፈጠር የጋራ ንብረት ጋር ተመሳሳይ ነው።

### የልጆች ጉዳይ

ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱ ልጆች በጋብቻ ውስጥ እደተወለዱት የባልየውን አባትነት በሕግ በመገመት የሚወስን ሳይሆን ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት ከእናትየው ጋር ይኖር የነበረው ሰው ልጁን ልጄ ብሎ መቀበሉን የሚያሳዩ ማስረጃዎች በማቅረብ መሆኑ በአንቀፅ 104 ላይ ተደንግጓል።

### ግንኙነቱን ማቋረጥ

የተጋቡ ሰዎች 6 ወር ሳይሞላቸው በስምምነት ጋብቻቸውን ማፍረስ አይችሉም። ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት የሚኖሩት ግን በፈለጉት ጊዜ ግንኙነታቸውን ማቋረጥ የሚችሉ ሲሆን ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈፀመ ካሳ ለመክፈል እንደማይገደድ የተ/ቤ/ሕ/ አንቀጽ 105 (2) ላይ ተቀምጧል።

> በድግስ ሳይ የታወጀውን የወ/ሮ መሠረትና የሀኪም ኪዳነወርቅ ጋብቻን በተመለከተ ጥር 15ቀን 1970 በድግስ ሳይ ሚች ሀኪም ወርቅነህ ወ/ሮ መሰረት ሚስቴ ናት ብለው ለታዳሚው ይፋ ማድረጋቸው ስለተረጋገጠ ከዚያም በኋላ ባልና ሚት ሆነው አብረው መኖራቸውን ምስክሮች አስረድተዋል

### ግንኙነቱን ማስረዳት

ጋብቻ ባለመፈፀሙ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ሊቀርብበት አይችልም ወይም ከ3ቱ የጋብቻ አይነቶች ባዱ መፈፀሙንም ማስረዳት አይችልም። ሆኖም ጋብቻው ባይኖም እንደ ባልና ሚስት ግንኑነት እንደነበር በአንቀፅ 106(1) መሠረት የግንኙነቱ ሁኔተ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላ። ይህን ግንኑነት አለ ለማት ወንዱና ሴቷ ባይጋቡም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውን ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ አድርገው የሚገምቷቸው መሆኑን ወንዱ ወይ ሴቷ ካስረዱ ፍ/ቤቱ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናች ሲል የሕግ ግምት እንደሚወሰድ አንቀጽ 106(3) ይደነግጋል።

ሆኖም እንደባልና ሚስት ግንኑነት በወንዱና በሴቷ መካከል የለም የሚል ግንኙነቱ አለመኖሩን የሚያሳይ አስተማማኝ ማስረጃ ማቅረብ የሕጉን ግምት በማፍረስ ማስተካከል ተፈቅዶለታል።

### ሴሎች ያስጋብቻ ግንኙነቶች

ጋብቻ ወይም ካለጋብቻ እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጭ በአንድ ወንድና ሴት መካል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት እንደማይኖራቸው በአንቀጽ 107 ላይ የተመለከተ ሲሆን ጉዲፈቻ ወይም ልጅነትን መቀበል በወንድየው በኩል ከሌለ በዚህ አይነት ግንኙነት የተወለዱ ልጆ ከእናታቸው በቀር ከሌላ ሰው ጋር ምንም ህጋዊ ግንኑነት አይኖራቸውም።

### ሰበር ምን አለ?

የወ/ሮ የዝናንና የወ/ሮ ጥሩአየሁን ክርክር በሰ/ወ/ቀ 33/26 ሚያዝያ 28/2000 በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቶበት በቅፅ 5 ላይ ታትሟል። ወ/ሮ የዝና ለ25 ዓመት ከመ/ር ጥሩአየሁ ጋር ኖረው 5 ልጆች ወልደዋል። ልጃቸውም እንደተጋቡ እንደሚያምን መስክሯል። መ/ር ጥሩአየሁ የቤት ሰራተኛ ነች ቢሉም የሚኖሩት ግን ከዚህ የተለየ በሆነ ሁኔታ ነበር። ስለዚህ በፌዴራሉም ሆነ በአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ ጋብቻ ባይፈፀሙም ለ25 ዓመታት እንደ ባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን ስለካዱ የሰር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል። ወ/ሮ የዝና መ/ር ጥሩአየሁ ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው ስለኖሩ አብረው ሲኖሩ ያፈሩት ንብረት ላይ እኩል ድርሻ አላቸው ሲል ወስኗል።

በድግስ ላይ የታወጀውን የወ/ሮ መሠረትና የሀኪም ኪዳነወርቅ ጋብቻን በተመለከተ ጥር 15ቀን 1970 በድግስ ላይ ሚች ሀኪም ወርቅነህ ወ/ሮ መሰረት ሚስቴ ናት ብለው ለታዳሚው ይፋ ማድረጋቸው ስለተረጋገጠ ከዚያም በኋላ ባልና ሚት ሆነው አብረው መኖራቸውን ምስክሮች አስረድተዋል። በአዲስ አበባ የባህል ጋብቻ ሥርዓት በሽማግሌ ፊት በፅሁፍ ካልተደረገ በስተቀር ብሎ የሚከለክል ሕግ የለም። ከፈለጉ በፅሁፍ ከፈለጉ በቃል ተጋቢዎች ለህብረተሰቡ እወቁልን ብለው ሊመሰርቱት ስለሚችሉ ሀኪም ኪዳነወርቅና ወ/ሮ መሰረት በባህላዊ ስነሥርዓት ተጋብተዋል ሲል የፌ/ጠ.ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ 33875 ላይ ውሳኔ ሰጥቷል።■



ደርባ
Derba®
"Ready for Tomorrow!!"
የደርባ ሚድሮክ ማኔጅመንትና ሠራተኞች
መልካም የመውሊድ በዓል እንዲሆንላችሁ
ልባዊ ምኞታቸውን ይገልፃሉ።
DERBA CEMENT
DT
DERBA TRANSPORT
DLC
Derba
Drilling


ደርባ
Derba®
"Ready for Tomorrow!"
የደርባ ሚድሮክ ማኔጅመንትና ሠራተኞች
መልካም የገና በዓል እንዲሆንላችሁ
ልባዊ ምኞታቸውን ይገልፃሉ።
DLC
Derba
Drilling
DT
DERBA TRANSPORT
ደርባ ሲሚንቶ
DERBA CEMENT

## ኪነ-ጥበብ እና ባህል

# ሐይማኖት እና ያ ትውልድ

በጥበቡ በለጠ

መቼም ቀኑ የገና ዋዜማ ነውና ዛሬ ደግሞ እስኪ ስለ "መንፈሣዊ ፖለቲካ" እናውጋ ብዬ ተነስቻለሁ። "መንፈሣዊ ፖለቲካ" ምን አይነት ፅንሠ ሃሳብ ነው? ብላችሁም መጠየቃችሁ አይቀርም። ለነገሩ "መንፈሣዊ ፖለቲካ" ከተባለ "ስጋዊ ፖለቲካ"ም መኖሩ አይቀርም፤ ብላችሁ ልትገምቱ ትችላላችሁ። ግድ የለም ሁለቱም ፅንሰ ሃሳቦች ይኑሩ። ዛሬ ግን "መንፈሣዊ ፖለቲካ" የሚለውን ሃሳብ እንጨዋወት። በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ ይባል የለ? ተቆጪ ስለሌለን ወደ ወጋችን እንግባ።

ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት በቀደምትነት ከተቀበሉት ጥቂት የዓለማችን ሀገራት መካከል አንዷ ነች። ይህች ኢትዮጵያ፣ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥም ተደጋግማ ስሟ በበጐ ጐኑ የተፃፈላት ሀገር ናት። አባቶች "መንፈሣዊት ሀገር" ይሏታል። ጉዳዩን ሲያብራሩም፣ ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው ወይም ወደ ሀገሪቱ ምድር ያስገባችው እየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ በአራተኛው ዓመት ነው ይላሉ። ይህ ማለት በ34 ዓ.ም ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ማብራሪያ የሚጠቀሙበት፣ መጽሐፍ ቅዱስን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም የሐዋርያት ሥራ ተብሎ በተጠቀሰው ምዕራፍ ውስጥ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ እስራኤል ሔዶ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁ ይገለፃል። ይሄ ደግሞ በ30 ዓ.ም ልክ እየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ወቅት ነው። ጃንደረባው በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ የገንዘቧ አዛዥ መሆኑ ተገልጿል። ያ ማለት በአሁኑ አጠራር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስትሯ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ ይህ ጃንደረባ (ባኮስ) ትልቅ የመንግሥት መልዕክተኛ ነበር። በመሆኑም ጃንደረባው በእየሱስ ጥምቀት ላይ ተገኝቶ እሱም ተጠምቆ ወደ ኢትዮጵያ እስኪመለስ ድረስ ወደ አራት ዓመት ፈጅቶበታል። ከዚያም በ34 ዓ.ም ሀገሩ ኢትዮጵያ ገባ። ክርስትናም በኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ ዓመት ጀምሮ የመንግስት ሃይማኖት ሆነ ብለው መረጃ የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ።

ይህን ከላይ የሰፈረውን ሃሳብ በመከራከሪያነት የሚያቀርቡት አካላት በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና የገባው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉስ ኢዛና ዘመነ-መንግሥት ነው የሚሉትን ምሁራን የመልስ ምት ለመስጠት ነው። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ክርስትና ገባ የሚሉት ምሁራን የእነሱ ማስረጃ አክሱም ከተማ ውስጥ በንጉስ ኢዛና ዘመነ-መንግሥት የተሰሩ የድንጋይ ሐውልቶች ላይ "እኔ ንጉስ ኢዛና ከዛሬ ጀምሮ ክርስቲያን ሆኛለሁ" የሚለውን ጽሁፍ በመመልከት ነው። በዚህ ጽሁፍ ሀገሪቱን የሚመራው ኢዛና ሙሉ በሙሉ ክርስትያን መሆኑን ስላወጀ፣ ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት የሆነው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ባዮች ናቸው ምሁራኑ።

ከቤተ-ክርስቲያን በኩል ሆነው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም ነው ብለው በሚከራከሩት እና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ክርስትና የመንግስት ሃይማኖት የሆነው በሚሉት መካከል የ300 ዓመታት ልዩነቶች አሉ። የቤተክርስቲያኖቹ ተከራካሪዎች ማስረጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፤ የዩኒቨርሲቲ ምሁራኖቹ ማስረጃ ደግሞ አክሱም ውስጥ ያለው የድንጋይ ጽሁፍ ነው።

በነገራችን ላይ ከእነዚህ ከላይ ከሰፈሩት ሁለት ተከራካሪዎች ሌላ አንድ መረጃም አለ። ይህም፣ እየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የአክሱም ኢምፓየር ነበር። በዚያን ወቅት ኢትዮጵያን ይመራ የነበረው ደግሞ ንጉስ ባዜን ይባላል። ንጉስ ባዜን

> *ያ ትውልድ ያቀጣጠለውን አብዮት ከ40 ዓመታት በኋላም ሰከን ብለን ስናስበው ኢትዮጵያዊ መሠረቱ የሳሳ ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል። እነ ሆቺ ሚኒ፣ ቼኩ ቬራ፣ ማርክስ፣ ኤንግልስ፣ ሌኒን... የያ ትውልድ መጠምጠሚያ ሆነው አረፋት። የኢትዮጵያን አብዮት ማቀጣጠያ ችቦ ሆነው አገለገሉ። የመቅደላው ሰማዕት አፄ ቴዎድሮስ ተዘነጉ*

እየሱስ ከመወለዱ በፊት ኢትዮጵያን ለስምንት ዓመታት መርቷታል። ከዚያም የእየሱስ ክርስቶስን መወለድ ሲሰማ ወደ እስራኤል ተጉዞ እንደ ሰብዐ ሰገሎች ሁሉ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ እና ሌሎችንም የደስታ ስጦታዎች አበርክቶ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ መመለሱ በአፈ-ታሪክ ውስጥ በሰፊው ይነገራል። ከዚያም፣ ማለትም እየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላም ንጉስ ባዜን ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያን መርቷታል። ከእየሱስ መወለድ በፊት ስምንት ዓመት፣ ከመወለዱ በኋላ ደግሞ ስምንት ዓመት በአጠቃላይ 16 ዓመታት ኢትዮጵያን መርቷታል። ስለዚህ የክርስትና ጽንሰ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ የገባው እየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ በንጉስ ባዜን ዘመነ-መንግስት ነው የሚል ሃሳብ የሚሰነዝሩ የአክሱም መረጃዎችም አሉ።

በአጠቃላይ ግን መናገር የሚቻለው የክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ኢትዮጵያ ላይ መገናኘት የጀመረው እጅግ ረጅም ዓመታት ወደኋላ ተጉዞ ነው። ኢትዮጵያ ላይ የሚነግሱ ንጉሶች እስከ አፄ ኃይለሥላሴ ድረስ ያሉት ማለት ይቻላል ሹመታቸው የሚፀድቅላቸው በቤተ-ክርስቲያኒቱ ይሁንታ ነበር። ስለዚህ የሀገር መሪ ሾማ የምትቀባ ሃይማኖት ሆና እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ተጉዛ ነበር።

ወደኋላ ያሉ የታሪክ መዛግብቶችና መረጃዎች እንደሚያሳዩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የንጉስን ሹመት ከማፅደቅ ባሻገር፣ ኢትዮጵያ ችግር ሲገጥማት፣ በባዕዳን ስትወረር በመመከትና ነፃ በማውጣት ግንባር ቀደም ሚናም ነበራት። በአድዋ ጦርነት እንኳ የካቲት 1888 ዓ.ም ታቦቶቿን እና ቀሳውስቷን ይዛ የዘመተች በኋላም ከኮሎኒያሊዝም አገዛዝ ኢትዮጵያ ነፃ እንድትወጣ ያደረገች ቤተ-ክርስቲያን እንደሆነች ይገለፃል። ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በማቆየቱ ረገድ የቤተ-ክርስቲያኒቱ ሚና በምንም መለኪያ የሚሰፈር እንዳልሆነ የሚናገሩ በርካቶች ናቸው።

ለምሳሌ ያህል ትምህርትን በማስፋፋት፣ ልዩ ልዩ ኪነ-ጥበባዊ ሥራዎችን በመገንባት (ዛሬም ድረስ የፕላኔታችን ምስጢራት የሆኑትን እንደ ቅዱስ ላሊበላ ኪነ-ሕንፃዎች አሠራር)ን በማበርከት፣ በመፃህፍት እና በመዛግብት ሕትመት፣ በቋንቋ ልማትና ብልፅግና ብሎም በሌሎችም ኢትዮጵያዊ መሠረቶች ላይ ዘላለማዊ ካስማና ማገር የሆነች የእምነት ተቋም ነበረች። ድንገት ግን 1966 ዓ.ም ላይ ምን እንደነካት ሳይታወቅ አንድ አስደንጋጭ ጉዳይ ገጠማት።

ከ1950ዎቹ እስከ 1966 ዓ.ም ላይ ብቅ ባሉ ወጣት የኢትዮጵያ የለውጥ አቀንቃኞች አዲስ ሃሳብ መጣ። ይህ ሃሳብ መንግሥት እና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን አፅንኦት ሰጥቶ የሚሰብክ ነው። ያ ትውልድ በነ ማርክስ፣ ኤንግልስና ሌኒን ፍልስፍናዎች የተሞላ ስለነበር ከሀገርኛው መንፈስ፣ እምነት፣ ባሕልና ታሪክ ውጭ የሆኑ አስተሳሰቦች ላይ ትኩረት አደረገ። ኢትዮጵያን ለማዘመን፣ የተሸለች ሀገር ለማድረግ ከሃይማኖታዊ ተፅዕኖ እና አስተሳሰብ መላቀቅ አለበት ተብሎ ትግል ተጀመረ። የትግሎቹ ሒደት በመጨረሻም በ1966 ዓ.ም ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን ፈጥሮ ለሦስት ሺ ዓመት የኖረውን የንግሥና ሥርዓት በመጣልና ከ1500 ዓመት በላይ የቆየውን ሃይማኖታዊ መንግሥትን ማውረዱን አወጀ። ከዚያም በየ ጐዳናው ተጨፈረ።

ፋኖ ተሰማራ
ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆቺ ሚኒ - እንደ ቼኩ ቬራ!
አለ ተቀናቃኙ።
"ተነሣ ተራመድ - ክንድህን አበርታ
ለሀገር ብልፅግና ለወገን መከታ"
እያሉ ሕብረ-ዝማሬ አሰሙ።
"ይህ ነው ምኞቴ
እኔ በሕይወቴ
ከራሴ በፊት ለኢትዮጵያ እናቴ"

እየተባለ ተዘመረ። "ኢትዮጵያ ትቅደም" ብለውም በማታውቀው የሶሻሊዝም የመሮጫ ትራክ ውስጥ ከተዋት ካለ አቅሟ አስሮጧት። አደከሟት።

በኋላም የመፈክር አይነትም ተኸርጐደጐዱ።

- ፊውዳሊዝም ይወድማል!
- ኢምፔሪያሊዝም ይወድማል!
- አናርኪስቶች ይወድማሉ!
- የቢሮ ከበርቴዎች ይወድማሉ!

ብዙ የሚወድሙ ነገሮችም መጡ። ፈተናው እያየለ መጣ።

በወቅቱ በትውልድ ውስጥ ሲብሰለሰል ቆይቶ ድንገት የፈነዳውን ማለትም ሃይማኖትና መንግሥት ከዛሬ ጀምሮ አንዱ በሌላው ጣልቃ አይገባም በሚሉት አስተሳሰቦች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በመቃወም ድምፃቸውን ያሰሙት አለቃ አያሌው ታምሩ ናቸው።

አለቃ አያሌው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ውስጥ የሊቆች ሊቅ የሚል መጠሪያ የነበራቸው ናቸው። ታዲያ 1966 ዓ.ም ላይ፣ አለቃን አስቆጥቶ በተቃውሞ ያስነሳቸው ጉዳይ ቢኖር፣ ሃይማኖትና ሀገር /ፖለቲካ/ አንዱ በሌላው ላይ ጣልቃ አይገቡም የሚለው አዲስ አስተሳሰብ ነው። አለቃ አያሌው ይህን ሃሳብ በመቃወም ያቀረቡት ነገር ቢኖር፣ ይህች ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ከጦርነት ጠብቃ እና ተከላክላ፣ ትውልድን አስተምራና አሳውቃ፣ ነገስታትን እየሾመችና ከጐን ሆና እየመራች፣ እዚህ ያደረሰችው ቤተ-ክርስቲያን ናት። ታዲያ በምን ምክንያት ነው ዛሬ በሀገር አመራር ውስጥ ቤተ-ክርስቲያን ጣልቃ አትገባም የሚባለው? ለመሆኑ ሀገሪቱን ጠብቆ እዚህ ያደረሰው ማን ሆነና ነው። አያገባትም የሚባለው!? በማለት ግንባራቸውን ለጥይት ሰጥተው ከአዳዲሶቹ ትውልዶች ጋር ተፋጠው ነበር።

እየዋለ እያደር የጊዜውና የፖለቲካ ትኩሳቱ፣ ግለቱ እየተፋጀ መጥቶ ግድያውም የትየለሌ እየሆነ ሲመጣ፣ ቤተ-ክርስትያን እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተፋቱ (ተለያዩ)። የአስተሳሰብ ግድግዳ በትልቁ ተገነባባቸው። እየዋለ እያደር ደግሞ "ሃይማኖት የመጨቆኛ መሣሪያ ነው" የሚሉ ፍልስፍናዎች በስፋት ተቀነቀኑ።

ይህ የመጨቆኛ መሣሪያ ነው ተብሎ የተጠራው ሃይማኖት ደግሞ ክፉኛ ችግር ውስጥ መግባት ጀመረ። ታላቋ ቤተ-ክርስቲያን አሉታዊ ተፅዕኖ እየበረታባት በመሄድ ለሕልውናዋ ሁሉ አስጊ ጉዳዮች መታየት ጀመሩ።

ለዚህች ሀገር ክብር፣ ለዚህች ሀገር ሕዝቦች ልዕልና ሲባል ደረታቸውን ለመትረየስ ጥይት ሰጥተው የሚሞቱ የሃይማኖት አባት ማለትም እንደ አቡነ ጴጥሮስ ያሉ ሰማዕት የሰጠች ቤተ-ክርስቲያን በሀገር ጉዳይ አያገባሽም ተባለች። እሷ ጠብቃ ባኖረቻት ሀገር እነ ማርክስ፣ ኤንግልስ እና ሌኒን የሃሳብ መሪዎች ሆኑ። ለኢትዮጵያ የተሰውት የአቡነ ጴጥሮስ የእምነት ፅናትና ፍልስፍና ኢትዮጵያ ላይ ሳይነገር፣ የባዕዳኖቹ የነ ማርክስ ርዕዮተ ዓለም መመሪያዎችን ሆኖ ኖረ።

ያ ትውልድ ያቀጣጠለውን አብዮት ከ40 ዓመታት በኋላም ሰከን ብለን ስናስበው ኢትዮጵያዊ መሠረቱ የላላ ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል። እነ ሆቺ ሜኒ፣ ቼኩ ቬራ፣ ማርክስ፣ ኤንግልስ፣ ሌኒን... የያ ትውልድ መጠምጠሚያ ሆነው አረፉት። የኢትዮጵያን አብዮት ማቀጣጠያ ችቦ ሆነው አገለገሉ። የመቅደላው ሰማዕት አፄ ቴዎድሮስ ተዘነጉ፤ መተማ ላይ አንገታቸውን ለሀገራቸው ክብር የሰጡት አፄ ዮሐንስ ተረሱ፤ አድዋ ላይ የኮሎኒያሊዝምን ወረራ ድባቅ የመቱት አፄ ምኒሊክ ለምሳሌም መብቃት አቆሙ፤ ኢትዮጵያን ከባዕድ ወረራ አውጥተው ወደ ስልጣኔ መንገድ የቀየሷት አፄ ኃይለስላሴን ስማቸውን የጠራ እንደ እርኩስ ይቆጠር ጀመር። በአጠቃላይ ሀገራዊ ምሳሌና መመሪያ የጠፋበት ዘመን ተፈጠረ - 1966 ዓ.ም

የያ ትውልድ አባላት በአብዛኛው ሃይማኖታቸውን ቀይረው አዲስ ሃይማኖት ጀመሩ። አዲሱ ሃይማኖታቸው ደግሞ "ሶሻሊዝም" ሆነ። ርዕዮተ ዓለሙን እስከ ማምለክ ደረሱ። በየፓርቲዎቻቸው ውስጥ ሆነው አቀነቀኑ። ከየ ካምፓቸው ላይ ሆነው የእኔ ፓርቲ አመለካከት የተሻለ ነው በሚለው ተከራከሩ፣ ተጣሉ፣ ተገዳደሉ፣ በመቶ ሺዎች አለቁ፣ ታሰሩ፣ ተሰደዱ። ያ ጦስ ላለፉት 40 ዓመታት ሰንኮፉ አልወጣም።

"በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" ብዬ ሃይማኖትና ያ ትውልድን በጥቂቱ ልዳስሰው ሞከርኩ። መጪው ጊዜም ጥምቀት ነው። ታህሳስ 29 ቀን 2007 ዓ.ም እየሱስ ክርስቶስ ተወለደ ብለን እናከብራለን። ጥር 11 ደግሞ ጥምቀቱን እናከብራለን። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "እኛ እና እግዚአብሔር" የሚል ግሩም ጽሁፍ አላቸው። ያ ትውልድ እና ሃይማኖት ተራርቀው ኖረው ነበር። ይህ ትውልድ እና ሃይማኖትስ የሚል ጥያቄ ማንሳት ትችላላችሁ። ስለዚህ ወጋችን ሳምንትም ይቀጥላል። ወቅቱ ዓውዳመት ስለሆነ ነው። መልካም የገና በዓል ይሁንላችሁ ብዬ ብሰናበትስ።■



# ትዝብትን በጨዋታ

በአሸናፊ ደምሴ ......... demissieashenafi@gmail.com

# “ሁሉ አማረሽ...”

እነሆ በነብዩ መሐመድ እና በእየሱስ ክርስቶ የልደት በዓላት ተከበን ሰንብተናል:: . . . ለእስልምናም ሆነ ለክርስትና አማኑያን እንኳን አደረሳችሁ በማለት ወደትዝብታዊ ጨዋታችን እናዘግማለን::

ከሁሉም ከሁሉም “አስር ያባረረ አንድ አይዝም” ይሉት አነጋገር ይገርመኛል:: እኛ እንደሆነ የምናባርረው አንድ ነገር ነው እርሱም፣ የዕለት እንጀራችንን:: በአንፃሩ ደግሞ እኛን የሚያባርረን ነገር ብዛቱ የትየለሌ ነው::. . . የመብራት መጥፋቱ፣ ውሃ ጥማቱ፣ የኔትዎርክ መቆራረጡ፣ መንገድ መዘጋቱ፣ ቅጣ ያጣው ቢሮክራሲና የኑሮ ውድነቱ ሁሉ እኛን አስር ሆነው የሚያሳድዱን ይመስለኛል::

እኔ የምለው የምኞትና የአምሮት ቁንጣን ቢኖረን ምን ነበረበት?. . . እውነቴን እኮ ነው ከልክ በላይ መመኘት፤ ከአቅም በላይ ፍላጎት እኮ ራሱን የቻለ ድክመት ነው:: ስልጣኑንም መመኘት፣ ገንዘቡንም መመኘት፣ ጉልበቱንም መመኘት፣ አዛኝና ናዛዥነቱንም መመኘት ደግ አይደለም:: (አንዳንድ ወዳጆቼ ፆታ ተኮር ወሬ ሲያወሩ አንድዬ ሲፈጥረን ሽጉጡን አንድ ቦታ ጥይቱን ሌላ ቦታ አድርጎ ነው የፈጠረን ይላሉ:: ቂ-ቂ-ቂ)

ዕውቁ ፈላስፋና ባለአዕምሮ ሸፐንሀወር፤ የታላቅ አእምሮ ህልም ምንድው ቢሉት “ማለቂያ ከሌለው ክፉ ምኞት መውትና ከታላላቆች ግኝትና ጥበብ ጋር ራስን ማቆራኘት ነው” ብሏል:: ይህም ብቻ አይደለም:: ኃይለጊዮርጊስ ማሞ በፃፈው “ጥበብ-ሁለት” መፅሐፍ ውስጥ የዚሁ ፈላስፋ አስተሳሰብ እንደሚከተለው ተቀምጧል::

“አዋቂ ሰው ማለት ፍላጎቱን የመግታት እውቀቱ የሆነ ማለት ነው:: በህይወት ዝቅተኛ ደረጃ ራስን በፍላጎት አጥር ውስጥ ማስቀመጥ መሆኑን የሚናገረው ሾፐንሀወር “አብዛኛው የሰው ልጅ በብዙ ፍላጎትና በጥቂት ዕውቀት የተሞላ ነው፤ አዋቂነት ግን ብዙ እውቀትና ጥቂት ፍላጎት ብቻ ይበቃታል” ይለናል::

ብዙ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ጠቅልለው የያዙ ሰዎችን ማመን ጤነኝነት አይደለም:: ለዚህም ነው ብዙ ምኞትና አምሮት ያላቸውን ሰዎችንም ማህበረሰባችን በስነ-ቃሉ የማያበረታታው:: ለምሳሌ “ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት” ይሉት ብሂል ድንቅ ማሳያ ይመስለኛል::

እኛ ሁሉ አማረሽ በሆን ቁጥር ራሳችንን ለሌላ ፈተና፣ ለሌላ አምሮት፣ ለሌላ ፍላጎት፣ ለሌላ መከራ፣ ለሌላ ድካም ማዘጋጀታችን አይቀሬ ነው:: “ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም” እንዲሉ፤ አንድ ነገር ላይ አተኩረን ያንኑ በተሳካ ውጤት ብንሰራው ምን አለበት? አለበለዚያ ግን የማህበሩም ሰብሳቢ፤ የዕድሩም ሊቀመንበር፤ የዕቁቡም ተቆጣጣሪ፤ የሰራተኛ ማህበሩ ፀሐፊ፤ የቀበሌው ህዝብ አቤቱታ ሰሚ፤ የድርጅት ስራ አስፈፃሚ ወዘተ ሁሉም ላይ እኔ ከሌለው እያሉ መጥለቅ “የእርጎ ዝንብ” ከማስባል ባለፈ፣ “አስር ያባረረ አንድ አይዝም” ሊያስተርትብን ይችላልና ጠንቀቅ ማለት አይከፋም::

የስልጣን አምሮታችንን፣ የገንዘብ አምሮታችን፣ የስም አምሮታችንን፣ የዝና አምሮታችንን፣ የመታየት አምሮታችንን፣ የመደመጥ አምሮታችንን መቆጣጠር ካልቻልን በኋላ “ይሄ እዩኝ እዩኝ ደብቁኝ ያመጣል” ሊሆንብን ይችላል::

ለዛሬ ከመሰነባበታችን በፊት ያንንም - ያንንም ለሚያምራቸውና ፍላጎታቸውን መገደብ የማይችሉ ሰዎች የሚገጥማቸውን ከንቱ ልፋት የምታሳይልኝን ግጥም ከሰለሞን ሞገስ (ፋሲል)፤ “ፅሞና እና ጩኸት” እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ፤

*“አዋቂ ሰው ማለት ፍላጎቱን የመግታት እውቀቱ የሆነ ማለት ነው። በህይወት ዝቅተኛ ደረጃ ራስን በፍላጎት አጥር ውስጥ ማስቀመጥ መሆኑን የሚናገረው ሾፐንሀወር “አብዛኛው የሰው ልጅ በብዙ ፍላጎትና በጥቂት ዕውቀት የተሞላ ነው፤ አዋቂነት ግን ብዙ እውቀትና ጥቂት ፍላጎት ብቻ ይበቃታል” ይለናል።*

ምንገድ

“ከአድማሱ ባሻገር ዘለቅሁ እንደምንም
ሌላ አድማስ አይሁኝ እንደገና አሁንም
በብዙ መታተር በብዙ ፈተና
ይህንንም አድማስ ደርሼ አየሁና
በቃ ፈፀምኩ ስል ጨረስኩ እንደምንም
ይታየኝ ጀምር ሌላ አድማስ አሁንም::”

አንድዬ ለልቅ ምኞታችን ልጓምን አይንፈገን አቦ፤ ቸር እንሰንብት!■

## ኪነጥበብ-ዜና

## “አምስቱ የመከራ ዘመናት” እና “የኢሕአዴግ የማርያም መንገድ” መጽሐፍት ለንባብ በቁ




በደራሲ እርቅ ይሁን በላይነህ የተፃፈውና “አምስቱ የመከራ ዘመናት” የተሰኘ ርዕስ የተሰጠው በሀገራችን ታሪክ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ባሳለፍነው ሳምንት ለንባብ በቃ:: መጽሐፉ በአስራ ሁለት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን፤ በንግስት ዮዲት፣ በኢማም አህመድ፣ በአፄ ሱስኒዮስ፣ በደርቡሾችና በአምስቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ዘመናት ተቃጥለው የወደሙ 44 አብያተ ክርስትያናትን ታሪክ ይዟል:: በዚህም ታሪክ ውስጥ የበርካታ አርበኞች፣ ሊቃውንትና ነገስታት ታሪክ አብሮ ተወስቷል::

“አምስቱ የመከራ ዘመናት” መፅሐፍ ከ94 ያላነሱ ምስሎችን አካቶ በ318 ገጾች የቀረበ ሲሆን፤ ዋጋውም 100 ብር መሆኑ ተጠቅሷል:: ደራሲው እርቅይሁን በላይነህ ይህ አምስተኛ መጽሐፉ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ካቀረባቸው በርካታ የሬዲዮ ድራማዎቹ በተጨማሪ ያልተጠበቡ ጡቶች፣ የግብፅ ቅኝት፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከኢማም አህመድ እስከ አፄ ቴዎድሮስ እና እርቃንሽን ቅሪ የተሰኙ መጽሐፍትን ለንባብ አብቅቷል::

በ ተ ያ ያ ዘ ም በአሸናፊ ደምሴ የተፃፈውና “የኢህአዴግ የማርያም መንገድ” የተሰኘ ርዕስ የተሰጠው የትዝብት አዘል ወጐችን የያዘ መጽሐፍ በዚሁ ሳምንት ለንባብ በቅቷል::

ለደራሲው የበኩር ስራ የሆነው ይህ መጽሐፍ 26 አጫጭር ትዝብት አዘል ወጐች የያዘ ሲሆን፤ በ174 ገጾች ቀርቧል:: ዋጋውም 40 ብር መሆኑ ተገልጿል::




## የጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም የጉዞ ማስታወሻ ታተመ




የቱሪዝምና ባህል ጋዜጠኛ የሆነው የሄኖክ ስዩም የጉዞ ማስታወሻ ለህትመት በቃ:: መጽሐፉ ጋዜጠኛው ለዘገባ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች የተመለከታቸውን ጉዳዮች ሲያካትት በዋናነት ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የሸካ፣ ቤንችና ሸኮ ብሔረሰቦችንና አካባቢያቸውን ሲያትት፣ የራስ ዳሽን የጉዞ ገጠመኙ፣ አንኮበርና ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የአፋር የጉዞ ትዝታዎቹ ተካተውበታል:: በሊትማን ትሬዲንግ የሚከፋፈለው ይህው መጽሐፍ 152 ገጾች ሲኖሩት፣46 ብር የመሸጫ ዋጋ ተቆርጦለታል::

# የጋዜጠኞቹና ጦማሪያኑ ክስ እንዲሻሻል ፍ/ቤት በድጋሚ ትዕዛዝ ሰጠ

በአሸናፊ ደምሴ

የወንጀል አድማ ስምምነት በማድረግ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ ከግንቦት 7 እና ከኦነግ ጋር አብረዋል፤ ማህበራዊ ድረ-ገፆችን በመጠቀም አመፅ ቀስቃሽ ፅሁፎችን በትነዋል፤ ስልጠናዎችን ወስደዋልና ገንዘብ ተቀብለዋል በሚል የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በሽብር ወንጀል ክስ የመሰረተባቸው በእነሶሊያና ሽመልስ መዝገብ ስር የተዘረዘሩት አስር ጦማሪያንና ጋዜጠኞች በድጋሚ ባቀረቡት የክስ መቃወሚያ ላይ ዐቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል ሲል ፍርድ ቤቱ በድጋሚ ትዕዛዝ ሰጠ።

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት በትናንትናው ዕለት ታህሳስ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የቀረቡት ተጠርጣሪዎች በቀረበባቸው ክስ ላይ መቃወሚያ ማቅረባቸውን ተከትሎ፣ ዐቃቤ ሕግ የሰጣቸውን የማሻሻያ ምላሾች ተንተርሶ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ብይን ለማድመጥ የነበረ ቢሆንም፤ የተከሳሽ ጠበቆች ግን በድጋሚ ዐቃቤ ሕግ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት እንዲሻሻሉ የታዘዙትን አላሻሸልም የሚል አቤቱታ አሰምተው የነበረ በመሆኑ በድጋሚ ክሱ እንዲሻሻል የተጠቆሙትን ጉዳዮች አስታውሷል።

በዚህም መሠረት የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው ችሎቱ፤ ዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ክሱን ከፀረ - ሽብር አንቀፅ ሦስት ስር በተዘረዘረው መሠረት አሻሽሎ አቅርቧል ብሏል። በዚህም ተከሳሾቹ ከግንቦት 7 እና ከኦነግ ጋር በመሆን ፈፅመዋቸዋል ያላቸውን ወንጀሎች አሻሽሎ አቅርቧል ተብሏል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን እንዲሻሻሉ ብይን ከተሰጠባቸው ነጥቦች ውስጥ ያልተሻሻሉ አሉ በሚል የተጠርጣሪ ጠበቆች ያቀረቡትን መቃወሚያ ተከትሎ የእያንዳንዱ ተጠርጣሪ የስራ ድርሻ በዝርዝር አልተገለፀም፤ የሽብር ቡድኑ ስምና ስልጠና የትና መቼ ወሰዱ የሚለው አልተገለፀም፣ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ ናትናኤል ፈለቀ ለስራ ማስኬጃ ወስዶታል የተባለው 48ሺ.ህ ብር ከማን እንደተገኘ እና ለምን አገልግሎት እንደዋለ በግልፅ አልሰፈረም የሚሉትን ነቅሶ በማውጣት በቀጣይ ቀጠሮ ተሻሽለው እንዲቀርቡ አዟል። ይህ ካልሆነ ግን ከክሱ መሰረዛቸው አይቀሬ መሆኑንም ፍርድ ቤቱ አሳስቧል።

በዚህም የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ክሱን አሻሽሎ ማቅረብ አለማቅረቡን ተመልክቶ ብይን ለመስጠት ለጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።■

# ካፕተስ፤ ውስኪ እና ቮድካን ማምረት ጀመረ

በመስከረም አያሌው

የአምቦ ማዕድን ውሃ እህት ኩባንያ የሆነው ካፕተስ መጠጦች ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን በኢትዮጵያ ማምረት እና ወደ ገበያ ማስገባት መጀመሩን ገለፀ።

የፋብሪካው ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ግርማ ታደሰ ለሰንደቅ ጋዜጣ እንደገለፁት፣ ፋብሪካው ጂን፣ ቮድካ፣ ትሮየም፣ ኡዞ፣ ውስኪ እና የመሳሰሉትን ስድስት አይነት የአልኮል መጠጦች በማምረት ላይ ይገኛል። የአልኮል መጠጦች ከባለፈው ወር ጀምሮ በመላው ሀገሪቱ በገበያ ላይ መሆናቸውም ተገልጿል። መቀመጫውን በምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ከተማ ያደረገው ኩባንያው የሚያቀርባቸው መጠጦችም ኢትዮጵያዊ እና የተለዩ ምርቶች እንደሆኑ ተገልጿል።

ለረጅም ጊዜ በውስኪነት ተመርተው የተቀመጡ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ በማስገባት እና በመደበላለቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርቶቹን ለገበያ የማቅረብ ሥራ እየተሰራ መሆኑንም አቶ ግርማ ገልጸዋል። ፋብሪካው እያቀረባቸው ያሉት ምርቶች ጎርደን ጂን የመሣሠሉትን ከውጭ የሚገቡ መጠጦች ለመሰባበር እና ለተጠቃሚም በቀላሉ ሊደርሱ የሚችሉ ለማድረግ ታስበው እንደተዘጋጁም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ካፕተስ የመጠጦች ፋብሪካ በተለያዩ የአልኮል መጠጦች ምርት ላይ የተሰማራ እና በአለማችን ሁለተኛው የውስኪ፣ አልኮል፣ ለስላሳ እና ቢራ አምራች የሆነው ሳብ ሚለር (SAB Miller) ኩባያ እህት ፋብሪካ በመሆኑ ምትሮቹ በእነዚህ ኩባንያ ቁጥጥር ስር እንደሆነም አቶ ግርማ ገልጸዋል።

እነዚህን የአልኮል መጠጦች ለማምረት ፋብሪካው አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጉንና መጠጦቹን ለማምረት እና ለማሰራጨት ፈቃድ ተወስዶ ወደ ሥራ መገባቱንም አቶ ግርማ ጨምረው ገልጸዋል።■

# የግብፁ ፕሬዝዳንት አልሲሲ በጥር አጋማሽ በኢትዮጵያ ጉብኝት ያደርጋሉ

በፀጋው መላኩ

የግብፁ ፕሬዝዳንት አብዱል ፈታህ አልሲሲ በጥር ወር 2007 ዓ.ም ኢትዮጵያን ሊጎበኙ እንደሆነ አህራም ኦንላይን በእሁድ ዕለት ዘገባው አመልክቷል። ዘገባው ፕሬዝዳንቱ በዚህ ወር ከተያዘላቸው ዕቅድ አንዱ በኩየት የሚያደርጉት ጉብኝት መሆኑን ገልፆ ከዚህ በመቀጠልም በኢትዮጵያ ጉብኝት የሚያደርጉ መሆኑን ጨምሮ አመልክቷል። እንደዘገባው ፕሬዝዳንቱ ጥር 16 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ የሚጀመረውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔንም የመሳተፍ የጊዜ ሰሌዳ በዚሁ ተካቶ የተያዘ ነው። ፕሬዝዳንቱ የሁለት ቀናት የኩዌት ጉብኝታቸውን ካለፈው ሰኞ ጀምረው ያጠናቀቁ ሲሆን በወሩ ከተያዙት የጉብኝት ፕሮግራሞች መካከል ቀጣይ የጉብኝቱ የጊዜ ሰሌዳ የሚሆነው የኢትዮጵያ ጉብኝት መሆኑ ታውቋል።

በዚሁ ዙሪያ ያነጋገርናቸው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ፕሬዝዳንቱ ጉብኝት የሚያደርጉ መሆናቸውን አረጋግጠው፤ አጠቃላይ ሂደቱን በተመለከተ ዝርዝር ፕሮግራሙ እየተሰራ መሆኑን ገልፀውልናል። የግብፁ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሰሚህ ሹኩሪህ በመስከረም ወር በኢትዮጵያ ኦፊሻል ጉብኝት በማድረግ በህዳሴው ግድብና በሁለቱ አገራት የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዙሪያ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ውይይቶችን ማድረጋቸው ይታወሳል። የሁለቱ አገራት መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያምና ፕሬዝደንት አብዱል ፈታህ አልሲሲ በተለያዩ ጊዜያት ፊት ለፊት ተገናኝተዋል።

ፕ ሬ ዝ ዳ ነ ት አልሲሲ ወደ ስልጣን በመጡ ሰሞን በኢኳቶሪያል ጊኒ ማላቦ በተካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ የተገኛኙ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላም በ69ንኛው ከተባበሩት መንግስታት የመሪዎች መደበኛ ጉባኤ ጎን ለጎንም በአካል ተገኛኝተዋል። በሁለቱ መሪዎች የፊት ለፊት ግንኙነት ጊዜያት ዋነኛ የመወያያ ርዕሰ ጉዳያቸው የነበረው የህዳሴው ግድብ ጉዳይ ሲሆን፤ ፕሬዝደንት አልሲሲም በተለያዩ ጊዜያት ኢትየጵያን የመጎብኘት ፍላጎት እንዳላቸው ሲገልፁ ቆይተዋል።

# ዶ/ር ኢንጂነር ነኝ ባዩ ሳሙኤል ዘሚካኤል ተቀጣ



*ሳሙኤል ዘሚካኤል በዶክተር ኢንጂነርነት ስም ከመጠራት አልፎ በ27 ዩኒቨርሲቲዎች በመገኘት ለተማሪዎችና ለመምህራን የማነቃቂያ ንግግሮች ያደርግ እንደነበር በወቅቱ መዘገቡ የሚታወስ ነው።*

በጋዜጣው ሪፖርተር

በቂ የትምህርት ዝግጅት ሳይኖረው ራሱን "ዶክተር ኢንጂነር" እያለ በመጥራት በማታለል ወንጀል ክስ የተመሰረተበት ሳሙኤል ዘሚካኤል ባመነባቸው ሁለት ክሶች ብቻ 3 ዓመት ከ9 ወር በሚደርስ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ሰሞኑን ወሰነ።

ተከሳሹ ቅጣቱ ሊጣልበት የቻለው ከደረቅ ቼክ እና በሃሰተኛ የንግድ ፈቃድ ሰነድ መገልገል ሁለት ክሶች ወንጀለኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

ሳሙኤል ከነዚህ ክሶች ሌላ ከአንድ ግለሰብ 30 ሺ.ህ ብር አጭበርብሮ ወስዷል በሚልም 4ኛ የማታለል ወንጀል ክስ የተመረተበት ሲሆን በካደው አንድ ክስ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ ይዟል።

3 ዓመት ከ9 ወር በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጡት ሁለት ክሶች ደረቅ ቼክ እና ከንግድ ፍቃድ ጋር ተያይዞ ሃሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀሎች ናቸው።

ከአምባሳደር ልብስ ስፌት ድርጅት ባለቤት በሀሰተኛ መንገድ ድርጅቱንና ባለቤቱን አስተዋውቃለሁ በማለት 58 ሺ.ህ ብር ወስዷል በሚል የተመሰረተበትን ክስ ክዶ በመከራከሩ፤ ዐቃቤ ህግ ክሱን ያስረዱልኛል በማለት ያቀረባቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ የተከታተለው ችሎቱ ተከሳሹ ሊከላከል ይገባዋል ወይስ አይገባም የሚለውን ለመወሰን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

በሐምሌ ወር 2006 ዓ.ም በኬንያ በቁጥጥር ስር ውሎ ክስ የቀረበበት ሳሙኤል ዘሚካኤል በዶክተር ኢንጂነርነት ስም ከመጠራት አልፎ በ27 ዩኒቨርሲቲዎች በመገኘት ለተማሪዎችና ለመምህራን የማነቃቂያ ንግግሮች ያደርግ እንደነበር በወቅቱ መዘገቡ የሚታወስ ነው።

# ምርጫ ቦርድ የአንድነት ፓርቲ ውስጥ…

እነማንናችሁ፣ አላውቃችሁም" የሚል ምላሽ በውይይቱ ወቅት ቢያንጸባርቅም የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች ግን ለአዲሱ አመራር ማን እውቅና ሰጠውና ሌላውን ሕገወጥ ትላላችሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋቸዋል ብለዋል።

አዲሱ አመራር ወክለው የቀረቡት አቶ ግርማ ሰይፉ ለሰንደቅ እንደገለጹት፣ "እኛ ለድርድር አልሄድንም። ምርጫ ቦርድም የተፈጠረውን ልዩነት እንዲፈታ ጥያቄ ቢያቀርብም ልዩነቱ የሚፈታው በፓርቲ ሕገደንብ ብቻ መሆኑን አስረድተናል። የአንድነት ጠቅላላ ጉባኤ የአዲሱን አመራር ሕጋዊነት በውሳኔው አሳልፏል። ይህን ሕገወጥ ነው የሚሉ ወገኖች ፍርድ ቤት ሄደው መክሰስ ይችላሉ። ከዚህ ውጪ እኛን ሕጋዊ መሆን አለመሆናችን ላይ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ለመስጠት ሕጋዊ መሰረት የለውም" ብለዋል።

ከምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በሁለቱ ወገኖች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት መሰረት በማድረግ ቦርዱ በዛሬው ዕለት ተሰብስቦ ውሣኔ እንደሚያሳልፍ ይጠበቃል።



# የቤተ ክርስቲያኒቱ የገቢ ማስገኛ ተቋማት ኪራይ የግለሰቦች መጠቀሚያ መኾናቸው ተጠቆመ

. ሀብትና ጥቅሟን የሚያስጠብቅ የኪራይ ተመን ፖሊሲ የሚወጣበት ጥናት ተጀምሯል

. የጥቂት አድባራት ሓላፊዎችና ጥቅመኞች እንቅስቃሴ ጥናቱን እንዳያኰላሸው ተሰግቷል

. የአለቆች የመኪና ሽልማት የሙሰኞች ከለላና ለብልሹነት በር የሚከፍት ነው ተብሏል

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አንዳንድ ገዳማትና አድባራት፤ የገቢ ማስገኛ ምንጮችና የልማት ተቋማት የኪራይ አገልግሎት ከሰበካ ጉባኤያት ዕውቅናና የወሳኝነት ሥልጣን ውጭ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብትና ጥቅም ለጥቅመኛ የአድባራት ሓላፊዎችና ግለሰቦች ተላልፎ የተሰጠበት መኾኑ ተጠቆመ፡፡

ጥቆማው የተሰጠው፣ ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አድባራትና አንዳንድ ገዳማት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለማስገኘት የተቋቋመው አጥኚ ኮሚቴ ለፓትርያርኩ አቅርቦታል በተባለ የማስታወሻ ጽሑፍ ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ለሀ/ስብከቱ አድባራትና ገዳማት ለማምለኪያ፣ ለመካነ መቃብርና ለልማት መገልገያነት የሰጣቸው መሬቶች፣ “ለገቢ ማስገኛ” በሚል አብያተ ክርስቲያናቱን ተጠቃሚ በማያደርግ የዋጋ ተመንና ሀብቷን ለጥቅመኞች አሳልፎ በሚሰጥ የውል ዘመን ለግለሰቦች እየተከራዩ ስለመኾኑ በጽሑፉ ተመልክቷል፡፡

ተከራይ ግለሰቦች መልሰው በከፍተኛ ገንዘብ እያከራዩ ተጠቃሚ በመኾን ላይ እንዳሉ ጨምሮ የገለጸው ጽሑፉ፣ በአድባራትና ገዳማት ከመሬት፣ ከሕንፃና ከሌሎች ኪራዮች ጋራ ተያይዘው የሚገኙ ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጣቸው አሳስቧል፡፡ በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አጥኚ ኮሚቴው የቀረበው የማስታወሻ ጽሑፍ በቋሚ ሲኖዶስ ቀርቦ ከታየ በኋላ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በኩል ችግሮቹ በዝርዝር እንዲጠኑ በፓትርያርኩ አማካይነት ትእዛዝ መሰጠቱ ታውቋል፡፡

ችግሮቹን በአስተዳደር ጉባኤው የተወያየበት የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ጽ/ቤት ጉዳዩ “አሳሳቢና በሀገረ ስብከቱ አንዳንድ አድባራትና ገዳማት ዘንድ ሰፍኖ የሚታየው የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫ” መኾኑን በመገምገም በጥልቀት አጥንቶ የሚያቀርብ አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ማቋቋሙ ተጠቅሷል፡፡ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ እና የዕቅድና ልማት መምሪያዎች ዋና ሓላፊዎች እንዲኹም የሀገረ ስብከቱና የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ሓላፊዎች የሚገኙበት ኮሚቴው ከታኅሣሥ መባቻ አንሥቶ፣ የጥናቱን ዕቅድና በጥናቱ መካተት የሚገባቸውን ከስድሳ በላይ አብያተ ክርስቲያናት በመለየት ወደ ሥራ መግባቱ ተዘግቧል፡፡

የገዳማትና አድባራት መሬቶች፣ ሕንፃዎች፣ የመቃብር አፈጻጸምና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ቤተ ክርስቲያኒቱ በምትጠቀምበት አግባብ አገልግሎት ላይ የሚውሉበትን ኹኔታ ማመላከት የኮሚቴው ዋነኛ ዓላማ ሲኾን የሚከራዩበትን ዋጋ፣ የተከራዩበትን ጊዜና የውል ዘመን ጨምሮ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዘላቂ ጥቅም የሚሰጡባቸውን መንገዶች ማመቻቸት ጥናቱ የሚያተኩርበት ግብ እንደኾነ በማስፈጸሚያ ስልቱ ተዘርዝሯል፡፡

ጥናቱን በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ በቁርጠኝነትና በሓላፊነት ስሜት እንደሚሠራ ኮሚቴው አስታውቆ፤ የጥናቱ አፈጻጸም ከግኝቶች፣ ተመክሮዎችና ተግዳሮቶች በመነሣት ወቅቱንና የአሠራር ሒደቱን ያማከለ ማሻሻያ እንደሚደረግና ለዚኽም የማስፈጸሚያ መርሐ ድርጊቱን ለሚመለከታቸው አካላት አስቀድሞ በመላክ ግብረ መልስ የመቀበያ ጊዜ ማስቀመጡን ገልጧል፡፡ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ ጸሐፊዎችና ሒሳብ ሹሞች በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ በመገኘት የሚያነጋግራቸው ዋነኛ አካላት ናቸውም ተብሏል፡፡

ጥናቱ በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት ሓላፊዎች ደረጃና በግል ንግድ ላይ የተሠማሩ ጥቅመኞችን የሚያስቆጣ ስለመኾኑ በችግርነት የለየው ኮሚቴው፤ ለሥራ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የልኡካኑን ስም የማጥፋት፣ በተለይም ከመሬትና መሬት ነክ ከኾኑ ጉዳዮች ጋራ ተያያዥነት ባላቸው ግለሰቦች የጥናቱን ዓላማ በአግባቡ ባለመረዳትና በማጣመም ሥራውን የማጥላላት፣ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለማነሣሣት የመሞከር፣ የኪራይ ውልና ሌሎች ሰነዶች ጠፍተዋል በሚል ሰበብ የመደበቅ፣ የተፈላጊ አካላት ተሟልተው ያለመገኘትና መሰል ተግዳሮቶች ሊገጥመው እንደሚችል ታሳቢ አድርጓል፡፡

ኾኖም የጥናቱ ውጤት ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚጠቅምና ሀብቷን የሚያስጠብቅ መኾኑን በመገንዘብ የተጣለበትን ሓላፊነት በብቃት ለመወጣት መወሰኑን ያስታወቀው ኮሚቴው፣ እንቅስቃሴውን በመገምገም ሒደቱን በብዙኃን መገናኛ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ግልጽ የሚያደርግበትን የጊዜ ሰሌዳ ከማስቀመጥ ጀምሮ ተግዳሮቶቹን የሚቋቋምባቸውን ስልቶችና አሠራሮች በዝርዝር መንደፉን አመልክቷል፡፡ አኹን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የተወሰኑ ገዳማትና አድባራት መነሻነት የሚካሔደውና ለቅዱስ ሲኖዶሱ እንደሚቀርብ የሚጠበቀው ጥናት ውጤት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን የመሬት አጠቃቀምና ወጥነት የሚጎድለው የኪራይ ተመን የተመለከተ ፖሊሲ ለማውጣት በግብአትነት የሚያገለግል ነው ተብሏል፡፡

በተያያዘ ዜና፣ በሀገረ ስብከቱ አድባራትና ገዳማት ለአለቆች እየተበረከተ የሚገኘው የመኪና ሽልማት፣ ለአማሳኞች ከለላ የሚሰጥና ለብልሹ አሠራር በር የሚከፍት ነው በሚል በአስቸኳይ እንዲቆም በፓትርያርክ አቡነ ማትያስ መታዘዙ ተሰምቷል፡፡ መረጃው እንደሚጠቁመው፣ ልማታዊ ናቸው በሚል መኪና ለአለቆች የሚሰጥበት የሽልማት ሥነ ሥርዓት፤ የሥራ አፈጻጸማቸው ያልተገመገመበትና በሽልማቱ ጉዳይ ግልጽ መመሪያ በሌለበት ኹኔታ የተፈጸመ ነው፡፡ በልማታዊነት ስም የሕዝበ ክርስቲያኑ ገንዘብ ለሽልማት የሚውልበት አሠራር እንዲቆም በፓትርያርኩ ተሰጥቷል የተባለው ትእዛዝ፣ የጠቅ/ቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለሀ/ስብከቱ በጻፉት ደብዳቤ መመሪያ የተሰጠበት ሲኾን አፈጻጸሙ የሚገኝበትን ኹኔታ መገምገም የአጥኚ ኮሚቴው ተልእኮ አካል እንደኾነ ታውቋል፡፡

## “በመጪው ምርጫ...

ሰነድ ቀርፆ እየሰራ ይገኛል፡፡ አሁንም ቢሆን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ከሚፈልግና የፓርቲዎችን የሥነምግባር ደንብ ለመፈረም ከተዘጋጀ ፓርቲ ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም፣ ከነፃ ፕሬስና ከዕምነት ጋርም የሚያነሱት ክሶች የሕግ የበላይነትን ከማስከበር ውጪ የተለየ ተልዕኮ ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህም የውስጥ የምርጫ ዝግጅት ማነስና ተገቢውን የፖለቲካ ስራዎቻቸውን ካለመስራት የመጣባቸውን በራስ አለመተማመን ሕዝቡን አላስፈላጊ ዋጋ ለማስከፈል የመረጡበት መንገድ ብዙም ርቀት አያስኬዳቸውም፡፡ ሕዝቡ ለውጥ ፈልጓል የሚሉት በምርጫ እንጂ በእነሱ የፖለቲካ ፓርቲ ውሳኔ የሚፈጸም አለመሆኑን በጥንቃቄ ሊገነዘቡት ይገባል” ብለዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም በአዲሱ በአቶ አበባው መሐሪ የሚመራው መኢአድ በጋራ ለመስራት ደብዳቤ ማስገባቱን ገልፀው፣ በሰማያዊ ፓርቲ በኩል የደረሰን ደብዳቤ የለም ሲሉ አስታውቀዋል፡፡ እንዲሁም፣ በአንድነት በኩል በይፋ በተነገረው አቋም መሰረት ተመሳሳይ ፕሮግራም ካላቸውና ሀገር አቀፍ ፓርቲ ከሆኑ ፓርቲዎች ጋር እስከውህደት ድረስ በመዘለቅ አብሮ ለመስራት ይቻላል ብሎ ያምናል፡፡ መሰረታቸውን በክልል ወይም ብሔረሰብ ላይ ካደረጉ ፓርቲዎች ጋር ምርጫውን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን ከምርጫ በኋላ ላሉ ግንኙነቶች በትብብር ወይም በቅንጅት ሰፋ ባለ መሰረትና አደረጃጀት አብሮ መስራት ይፈልጋል፡፡ ይህ አቋም በስራአስፈፃሚ ተወስኖ ሶስት አባላት ያሉት ኮሚቴ አዋቅሮ ወደስራ ገብቷል፡፡ ይህ ኮሚቴ ሁሉንም ወደምርጫ ውስጥ የሚገቡ ሃይሎችን አስተባብሮ ከላይ ባሰፈርኳቸው ነጥቦች ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ እንቅስቃሴ ጀምሯል ብለዋል፡፡

በገዢው ፓርቲ በኩል መረጃ ለማግኘት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡

www.sendeknewspaper.com

## ዕጹብ የገና ስጦታ፡-

# “ሠላም በምድር ይሁን፣ ለሰው ልጆችም በጎ ፈቃድ!”

በዲ/ን ተረፈ ወርቁ



የሠላም ጉዳይ፣ የሠላም ወሬ የፍጥረት ሁሉ ናፍቆት ነው ብል ብዙም ያጋነንኩ አይመስለኝም:: ሠላም ማለት የግጭት፣ የብጥብጥ፣ አሊያም የጦርነት አለመኖር ብቻ አይደለም ይላሉ የሥነ ልቦና ምሁራን:: ሠላም በጦርነት፣ በጫጫታ፣ በኹከት፣ በመናወጥና በማይመች ሁኔታ ውስጥም ሆኖ እርጋታን፣ ውስጣዊ ጸጥታን መላበስም ጭምር ነው ሲሉ መንፈሳዊ አንድምታ ያለው ትርጓሜ ይሰጡታል::

በእርግጥም በነጋ ጠባ፣ የጦርነትና የእልቂት፣ የሥቃይ፣ የጩኸትና የጣር ድምጽ በሚሰማባት ዓለማችን፣ የሽብር ሥጋት ክፉኛ በሚንጣት ምድር ላይ እየኖርን ውስጣዊ የሆነ በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም የማይናወጥና የማይደፈርስ ሰላም ይኖርን ዘንድ የግድ ይላል::

እንዲህ ዓይነቱ ሠላም ምንጩ ከላይ፣ መገኛውም ሰማያዊና መለኮታዊ ነው ሲሉ የሃይማኖት ሊቃውንትና ምሁራን ከቅዱሳት መጽሐፍት ጠቅሰው ያስረዳሉ፣ ይተነትናሉ:: ዓለማውያኑንም ሆኑ በፈጣሪ መኖር የሚያምኑ ምሁራን ስለ ሰላም ምንጭ ያላቸው ትንታኔ ቢለያይም በአንድ ነገር አጥብቀው ይስማማሉ:: እርሱም ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊና መሰረታዊ መሆኑን!!

ሠላም ሰው ልጆች፣ ለፍጥረታት ኹሉ የዕለት ተዕለት ጥያቄ ከመሆኑ የተነሣ ለዓለማችን ሰላም ሲባል የተቋቋመውና ዋና ጽሕፈት ቤቱን በኒው ዮርክ አሜሪካ ያደረገው የመንግሥታቱ ድርጅትም በጽ/ቤቱ ፊት ለፊት ሰላምንና ስለ ሰላምየሚያዘክር አንድ ግዙፍ ሀውልት ቆሞ አለ:: ይህ ሀውልትም አንድ ጎልማሳ፣ ጎበዝ ሰይፉን ወደ ምርት መሣሪያ ለመቀየር በመዶሻ ሲቀጠቅጥ የሚያሳይ ነው:: በዚህ ሀውልትም ስርም የተቀረፀው ጽሑፍም እንዲህ ይነበባል፡-

“They shall beat their swords into ploughshares, and their spears into pruning hooks: nation shall not lift up sword against nation, neither shall they learn war any more.” “ሰይፋቸውን ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፣ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሳም፣ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም::” (ኢሳ. ፪፣፬)::

ግና አሳዛኙ እውነታ ጦርነትን እናውግዛለን የሚሉ የመንግሥታቱ ድርጅቱ ምስራቾችና ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ያላቸው ልእለ ኃያላኑ ሀገራት ሌሎች ሕዝቦች እርስ በርሳቸው የሚተላለቁበትን መሳሪያ በማምረትና በመሸጥ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው መሆናቸው ነው:: እነዚሁ አገራት ከፍተኛ በጀታቸውም የሚውለው ለጦር መሳሪያ ግዢና ምርት ነው:: በአፋቸው ሰላም ሰላም ቢሉም በልባቸው ውስጥ ብርቱ ሰልፍና የጥፋት ሰይፍ እንዳለ በተግባራቸው እየገለጹ ነው::

ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ፡- “. . . የሕዝቤን ስብራት በጥቂቱ ይፈውሳሉ ሰላም ሳይሆን፦ ሰላም ሰላም ይላሉ::” በማለት እንደተነበየው ስለ ዓለምና የሰው ልጆች ኹሉ ሰላም አብዝተው የሚጮኹ፣ አብዝተው የሚሰብኩ እነርሱ ራሳቸው የጦርነትንና የእልቂት ድግስን ደግስው ምድሪቱን የጭንቀትና የጣር ምድር እያደረጓት እንዳለን ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል::

ለአብነትም በኃያላኑ አገራት የኒኩሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤት የመሆን ሕልም ዕውን መሆን በሌሎች እኛስ ከማን እናሳለን በሚሉ አገራት መካከል የፈጠረው ሥጋትና የኒኩሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤት የመሆን ሩጫ ውድድር የሚነግረን ዘግናኝ ሐቅ ቢኖር በዓለማችን ላይ የተጋረጠውን ግዙፍ የሆነ የጦርነት አደጋ ነው:: በየዕለቱ ከመገናኛ ብዙኃን እንደምንሰማውም በአገራት መካከል ያለው የጦር አውርድ ወሬና ዝግጅት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት ኑሮ የሥጋትና ጭንቀት እንዲሆን አድርጎታል::

በዚህ በዛሬው ጽሑፌ ስለ ሰላም ጉዳይ ጥቂት ለማለት የወደድኩት በአንድ ምክንያት ነው:: ይኸውም በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ መንፈሳዊና ባህላዊ ዝግጅቶች የሚከበረው፣ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል/ገና ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም የተሰበከበት ዕለት በመሆኑ ነው:: ሰው ከአምላኩ፣ ሰው ከተፈጥሮ፣ ሰው ከራሱ ጋር ጠብ ውስጥ የነበረበት የጨለማ ዘመን ተሽሮ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ለሰው ልጆች ኹሉ ሰላም የምስራች ተብሎ በመሰበኩ ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት/የገና በዓል ለእኛ ለክርስትና እምነት ተከታዮች ታላቅ የሆነ መንፈሳዊና ባህላዊ አንድምታ ያለው ትልቅ በዓል ነው:: የበዓሉ መንፈሳዊ ምስጢር እንደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን አባቶቻችን አስተምህሮ ከሰው ልጆች በኃጢት መውደቅ በኋላ፣ የልጅነት ክብሩንና ጸጋውን የተገፈፈውን የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ “አምላክ ሰው የሆነበት፣ ሰውም አምላክ የሆነበት” ድንቅና ዕጹብ የሆነ ሰማያዊ ምስጢር የተገለጸበት በዓል እንደሆነ ያትታሉ::

ይህን ሰው አምላክ፣ አምላክም ሰው የሆነበትን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ምስጢር የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አባቶች እንዲህ ሲሉ ያመሰጥሩታል፡- “እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ የሰውን ልጅ ያዳነበት ወይም ሰውን ለማዳን አምላክ ሰው የሆነበት ጥበብ እጅግ ይጠልቃል፣ ይረቃል፣ ይሰፋልም::” ሲሉ በአድናቆትና በመገረም ይተርኩታል:: የአገረ ብሕንሳው የቤተክርስቲያን አባት አባ ሕርያቆስም፣ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቅዳሴው፡-

… ከአባቱ አጠገብ ሳይለይ ቃል ወደ አንቺ መጣ:: ሳይወሰን ፀንሸው በላይ ሳይጎድል በታችም ሳይጨመር በማኅፀንሽ ተወሰነ:: … ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ እሳት፣ ልብሱ እሳት፣ ቀሚሱ እሳት ነው:: እንደምን አላቃጠለሽ፣ ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ፣ ወዴትስ ተጋረደ ከጎንሽ በቀኝ ነውን፣ ወይስ ከጎንሽ በግራ ነውን፣ ትንሽ አካል ስትሆኚ:: የሚያንጸባርቅ ነደ እሳት የሚከበው ኪሩቤል የተሸከሙት ዙፋን በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ፣ ወዴትስ ተተከለ፣ ታናሽ ሙሽራ ስትሆኚ:: በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው የመሆን ምስጢር አድንቋል::

አባ ሕርያቆስ በዚሁ በእመቤታችን ቅዳሴው፡- “ኃያል ወልድን ለሰው ልጆች፣ ለፍጥረቱ ያለው ፍቅር ከዙፋኑ እንደሳበውና እስከሞትም እንዳበቀው፤” ይተርክልናል:: ይህ አባት በዚህ ድርሳኑም፡- “የማይደፈር ግሩም ነው፣ በእኛ ዘንድ ግን ትሑት ነው፣ የማይገኝ ልዑል ነው፣ በእኛ ዘንድ ግን አርዓያ ግብርን ነሣ፣ የማይዳሰስ እሳት ነው፣ እኛ ግን አየነው፣ ዳሰስነውም ከእርሱም ጋር በላን፣ ጠጣን::” ሲል እግዚአብሔር ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ዘመድ እንደሆነን አመስጥሯል::

ለዚህም ነው የአገራችን አዝማሪ በዘለሰኛ ድንቅ ዜማው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆኑ ለእኛ ለሰው ልጆች የቅርብ፣ የሥጋ ዘመድ እንደሆነን በማመስጠር እንዲህ የተቀኘው፡-

አብን ተወውና ንገረው ለወልድ
ፐሎ አይጥልምና የሥጋ ዘመድ።

አስቀድሞም ከክርስቶስ ልደት በፊት ፯፻ ዓ.ዓ. ገደማ የኖረው “ደረቅ አዲስን ተናጋሪ” ተብሎ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ዘንድ የሚጠራው ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም፡-

“እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድም ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም ኢየሱስ/አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች … ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ ሰላም አለቃ ይባላል::” ብሎ እንደተናገረ በይሁዳ ቤተ ልሔም የተወለደው “ኢየሱስ የሰላም አለቃ” መሆኑን ተናግሯል፣ ሰብኳል፣ መስክሯልም:: በይሁዳ ቤተልሔም የክርስቶስ ኢየሱስ መወለድን ተከትሎ መላእክት ከእረኞች ጋር በአንድነት ሆነው ስለ ሰላም መዘመራቸውን ሐኪሙና ታሪክ ጸሐፊው ወንጌላዊው ሉቃስ ደግሞ እንዲህ በወንጌሉ ዘግቦታል፡-

“እነሆም፣ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ፣ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ። ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ። መልአኩም እንዲህ አላቸው፡- እነሆ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፣ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ የሆነ ጌታ ተወልዶላችኋልና። … ድንገትም ብዙ የሰማይ ሰራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፣ ሰላምም በምድር፣ ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።”

ይህ ለሺህ ዘመናት በሱባኤ፣ በታላቅ ናፍቆትና ጉጉት “ይወርዳል፣ ይወለዳል” ተብሎ ይጠበቅ የነበረው የመሢሑ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ፣ አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ መሆኑ ለሰው ልጆች ኹሉ ታላቅ የምስራች ነው:: የአጥቢያ ንጋት ከዋክብትም ከሰማይ መላእክት ሠራዊቶችና ከእረኞች ጋር በአንድነት መዘመራቸውንና ይህን ዕጹብ ድንቅ የሆነ ዘላለማዊ ደስታ ለመካፈል በይሁዳ ቤተልሔም ከትመው እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል::

ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት ሌሊት መንጋቸውን በሜዳ አሰማርተው ለነበሩ የይሁዳ እረኞች መላእክት በታላቅ ደስታ ውስጥ ሆነው “ሰላም በምድር ይሁን፣ ለሰውም በጎ ፈቃድ!!” በሚል ታላቅ ሰማያዊ ዝማሬ ይህን ዘላለማዊና ፍጹም ሠላም ለሰው ልጆች ኹሉ አብስረዋል:: በዚህ ታላቅና ዘላለማዊ እውነት መሠረትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት/ የገና በዓል በአገራችን በኢትዮጵያ በታላቅ ደማቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓትና ባህላዊ ዝግጅቶች በድምቀት የሚከበር በዓል ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ወይም ገና በአገራችን ኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለውን መንፈሳዊና ባህላዊ አካባበሩን በተመለከተ ለዛሬ እምብዛም የምለው ነገር አይኖረኝም:: ግና የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ለሰው ልጆች ኹሉ ሰላምና ፍቅር የተሰበከበት ታላቅ ዕለት መሆኑን በተመለከተ፣ ስለ ሰላም ባነሳሁት ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥቂት አሳቦችን ልጨምር::

ይህን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ከኹለት ዓመት በፊት በአፍሪካ ቀንድ ባሉ አገራት ያሉ ሃይማኖት አባቶች ሰላምን በማስፈን፣ ግጭቶችን በመፍታት፣ በአፍሪካ

በገፅ 20



# “አትናገር፣ አትፃፍ ማለት...

ምን ትላለህ? አሁን በስራ ላይ ያሉ የግል ጋዜጦች ላይ ያለህ መረዳት ምን ይመስላል?

አቶ ስለሺ፡- የግል ብቻ ሳይሆን የመንግስትም መገናኛ ብዙሃን አሉ። እነዚህ ታፍነዋል ሲባል በእነሱ አንደበት የሚናገረው ማነው የሚለው ነው ጥያቄው መሆን ያለበት። ለምሳሌ የኢቲቪ ጋዜጠኞች እየተናገሩ ነው ብዬ አላምንም። ሃሳባቸውን እየገለፁ ነው የሚል እምነትም የለኝም። በአሁን ሰዓት ማንኛውም ሚዲያ በነፃነት ሃሳቡን እየገለጸ ነው ብዬም አልቀበልም። ሌሎች ወገኖች በእነዚህ ሚዲያዎች ተናገሩ ማለት፤ አልታፈኑም እየተናገሩ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ አያደርሰንም።

ሰንደቅ፡- የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ከሚቀረጽለት ኢዲቶሪያል ውጪ እንዴት ሥራዎችን ማስተናገድ ይችላል ተብሎ መውሰድ ይቻላል? አንድነት ካሸነፈ ይህን አሰራር አይከተልም?

አቶ ስለሺ፡- የመንግስትን ስራዎች መናገር ሀጢያትም፣ ወንጀልም አይደለም። እንደተባለው የፕሬስ ነፃነት አለ፤ ኢዲቶሪያል ነፃነትም አለ። የመንግስት ኢዲቶሪያል ምን እንደሚል አላውቅም። የመንግስትን ፖሊሲ ማስፈጸም የሚባለው ግን እነሱ በተረዱበት ሁኔታ ነው እየተተገበረ ያለው። የሙያ ነፃነታቸውን ጠብቀው ኢዲቶሪያሉ በሚለው መሰረት እየሰሩ ነው ወይ? የሚለው ምላሽ የሚፈልግ ጥያቄ ነው። ስለዚህ አለቃ አለህ ወይም በራስህ ላይ አለቃ ትሆናለህ። ከዚህ ውጪ በነፃነት የምትሰራ ከሆነ የእስክንድር የርዕዮት የተመስጌን ዕጣ ፈንታ ይደርስሃል።

ሰንደቅ፡- በነፃው ሚዲያ ላይ ስለሚሰሩት ጋዜጠኞችስ ምን መረዳት አለህ?

አቶ ስለሺ፡- በእኔ ግምገማ በነፃው ሚዲያ እየሰሩ ያሉ ጋዜጠኞች በሙሉ አለቃ አላቸው። አለቃቸው ሰዎች ላይሆኑ ይችላሉ። በርካታ አስፈሪ አዋጆች ግን አሉ። በርካታ አዋጁን ተከትሎ የሚተገበሩ ዕጣፈንታዎች አሉ። የቀደሙ ጓደኞቻቸውን የበላው ጅብ እንዳይበላቸው ሲጠነቀቁ፣ አለቃ በራሳቸው ላይ ያስቀምጣሉ። እጁ ረጅም የሆነ አለቃ አለ። በእኔ ግምት በግሉም በመንግስትም ስር ያሉ ጋዜጠኞች በነፃነት እየሰሩ ነው ብዬ አላምንም።

ሰንደቅ፡- አንድነት ፓርቲ በፕሬስ ነፃነት ላይ ያለው ሰነድ ምን ይላል? ከፕሬስ ጋር ተያይዘው የተቀረጹ ስትራቴጂዎች እና የአፈፃፀም ስልቶቹ ላይ ምን የተለየ ነገር ሰፍሮባቸዋል?

አቶ ስለሺ፡- አንድነት ፓርቲን ከፕሬስ ነፃነት ጋር በተያያዘ እንደገመገምኩት የማያወላውል ቀጥተኛ አቋም ነው ያለው። የሰው ልጅ የመናገር ነፃነት አለገደብ መከበር አለበት ብሎ ነው የሚያስበው። ሊብራሊዝም ስለሚከተልም ሊብራል ሚዲያ ይፈጥራል። ሊብራል ሚዲያ እንደሚታወቀው ለጋዜጠኞች ብዙ እድል ይፈጥራል። የሚዲያ ነፃነትም ይሰጣል። ፓርቲው በራሱ ሚዲያዎችም ላይ የሚዲያ እና የጋዜጠኞችን ነፃነት በተመለከተ እየሰራ ነው። ምክንያቱም የጋዜጠኞች ነፃነት ሁለት እግር ነው ያለው። አንዱ እግር ሕግ ሲሆን ሰዎች እንዲናገሩ መፍቀድ ነው። ሁለተኛው፣ ሰዎች ሲናገሩ በትዕግስት የመስማት ኃላፊነት ነው። የማይጥምህን ነገር እየተናነቀህ ቢሆንም መስማት አለበት። የማዳመጥ ኃላፊነትህን ካልተወጣህ መናገር ብቻውን የፕሬስ ነፃነት አያስከብርም። የአንድነት አመራርን በተጨባጭ መረጃ በፓርቲው ጋዜጦች ላይ መተቸት ትችላለህ። ይህን በማድረግ የሚደርስብህ ነገር የለም።

ሰንደቅ፡- አዲሱ የአንድነት አመራር ‘ከሕግ አግባብ ውጪ ስልጣን ተቆናጧል’ የሚል ልዩነት ያላቸውን ከዚህም በላይ አልፈው ለምርጫ ቦርድ ቅሬታቸውን ያቀረቡ የፓርቲው አመራሮችን አሉ። የእነዚህን አመራሮች ሃሳብ የፓርቲው ጋዜጣ ያስተናግዳቸዋል?

አቶ ስለሺ፡- ከዚህ በፊት መርህ ይከበር ብለው ከወጡት አንዱ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ነበር..

ሰንደቅ፡- ከዚህ በፊት ስለተፈጠረው የመርህ ይከበር ጥያቄ ሳይሆን አሁን ስምርጫ ቦርድ ቅሬታ ያቀረቡትን ማለቴ ነው?

አቶ ስለሺ፡- በአሁን ሰዓት በአንድነት ፓርቲ ውስጥ መርህ ይከበር የሚሉ እንዳሉ አላውቅም። ክፍፍል የሚባል ነገር የለም። እኔ የማውቀው አንድነት እኔ ያለሁበት ነው። ሌላ ስለመኖሩ አላውቅም። ሰሞኑን አመራሮቹ ከምርጫ ቦርድ ጋር ባደረጉት ድርድር ሰኞ ወይም ማክሰኞ የምርጫ ምልክት ውሰዱ ስለመባሉ ብቻ ነው በፓርቲው በኩል የማውቀው።

ሰንደቅ፡- በቀጣይ ምርጫ የመሳተፉ ነገር እንዴት ነው?

አቶ ስለሺ፡- አንድነት ወክዬ ይህን ለመናገር የሚያስችለኝ ሃላፊነት የለኝም። ሆኖም አንድነት በይፋ ምርጫ ላይ እንደሚሳተፍ ያለውን አቋም ግልፅ አድርጓል። ሕብረተሰቡ በምርጫ እንዲሳተፍ እንዲመርጠንም እንንቀሳቀሳለን። ከመረጠን መንግስት እንሆናለን። ከተሸነፍን እንተዋለን። ነገር ግን ገገርው ፓርቲ እንደለመደው አጭበረብራለሁ ካለ የመረጠው ሕዝብ ድምፅን እንዲያስከብር የተቀናጀና ትክክለኛ አመራር እንሰጣለን።

ሰንደቅ፡- ከዚህ በፊት የመሰረታችሁት የጋዜጠኞች መድረክ ከፖለቲካ ሃይሎች ጋር ግንኙነት አለው ይባል ነበር። አሁን የአንተ ወደ ፖለቲካ ፓርቲ ሙሉ ለሙሉ መግባት የነበረውን ግምት ያጠናክረዋል የሚል ስጋት አይፈጥርም?

አቶ ስለሺ፡- በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት እኛን በፖለቲካ ሃይሎች እጠረጥራለሁ የሚል ምክንያት አልሰጠነም። የተሰጠን ኦፊሻል መልስ ማሕበሩን ለመመስረት እያንዳንዳችሁ በጋዜጠኝነት ሙያ መመረቅ ያስፈልጋችኋል የሚል ነበር። በጋዜጠኝነት ያልተመረቀ አይሰራም ከተባለ ማንም አይተርፍም ነበር። ምክንያቱ ግን ለሙያቸው ለሚታገሉ ጋዜጠኞች ማሕበር እንዲያቋቁሙ መንግስት ስለማይፈልግ ብቻ ነው።■

*አንድነት ፓርቲን ከፕሬስ ነፃነት ጋር በተያያዘ እንደገመገምኩት የማያወላውል ቀጥተኛ አቋም ነው ያለው። የሰው ልጅ የመናገር ነፃነት አለገደብ መከበር አለበት ብሎ ነው የሚያስበው።*

# “የመንግሥት ጫና ወደ ፖለቲካው...

ይሆናል።

ሰንደቅ፡- የግለሰብም የቡድን መብትን አጣምሮ አንድነት ይመለሳል ብለሃል። ማሳያዎችን ብታስቀምጥልኝ?

አቶ አናኒያ፡- አንድነት ሊብራሊዝም ነው የሚከተለው። ሊብራሊዝም በሀገረ አሜሪካ እንኳን ብንወስደው ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር (የፌሚኒዝም እንቅስቃሴ) እንደሴት በቡድን ተደራጅተው መብታቸውን ያስከበሩበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው። ከዚህም አልፎ ጥቁር አሜሪካዊያን እነማርቲን ሉተር ኪንግ የጥቁሮች መብት አልተከበረም ብለው በቡድን ተደራጅተው መብታቸውን አስከብረዋል። ችግራቸው በሊብራሊዝም ማዕቀፍ ተፈቷል። ከዚህ አንፃር የቡድን መብቶች የተከበሩት በሊብራሊዝም አመለካከት በሚከተሉ ሀገሮች ውስጥ ነው።

ሰንደቅ፡- ከላይ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የአፈና ስርዓት ነው ብለኸኛል። ይህን አገላለጽህን ከማጣቀሻዎች ጋር አያይዘህ ብታስረዳን?

አቶ አናኒያ፡- አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘመኑ ያለፈበት የእነሌኒን ቤተሙከራ ነው። የስርዓቱ ሰዎችም ቢሆኑ ሊያብራሩት አይችሉም። መጨበጫም ውል የሌለውም አስተሳሰብ ነው። የሶቪየት ዘመን ቅሪት የሆነ የዞረ ድምር ነው። የኮሚኒዝም የዞረ ድምር ነው። እንደቲየሪ የሚቆጠርም አይደለም። እኛ የምናውቀው በእኛ ሀገር ወደተግባር ተቀይሮ ነው። እኛ ላይ ሲተገበር ደግሞ እስርና አፈና ብቻ ነው። እንደሚወራው መልካም አስተዳደር አላሰፈነም። ሙስናን አላስቀረም። ልማትንም አላረጋገጠም።

ሰንደቅ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ እየታዩ ያሉ የልማት ስራዎችና እንቅስቃሴዎች ለአንተ ምን ትርጉም ይሰጥሀል? ወይንስ ልማት አለ የለም የሚለውን መወሰን ያቅትሃል?

አቶ አናኒያ፡- ለእኔ የሚሰጠኝ ትርጉም የቱባ ሙሰኞች ገንዘብ መደበቂያ ናቸው። በሀገሪቱ ልማት አለ የሚባለው ዲስኩር ውሃ አይቋጥርልኝም። የማን ፋብሪካ? የማን ገቢ? ተደምሮ ነው ሲባል የአንድ ሚስኪን ጎዳና ላይ የሚያድር እና የተወሰኑ ባለሃብቶች ገቢ ተደምሮ ነው ሀገሪቷ አደገች የሚባለው። ስርዓቱ የወለዳቸው ባለሃብቶችና ሎሌዎች ሕብረተሰቡን እየዘረፉ፣ እያፈናቀሉ፣ መሬቱን በርካሽ ዋጋ ለሕንድና ለቻይና እየሸጡ በሮኬት አይነት ፍጥነት ተመንድገዋል። ሰፊው ማሕበረሰብ ደግሞ ወደ ድህነት አዘቅዝቋል። ስለዚህም ገበሬ ይሻላል ወይንስ ነጋዴ የሚባል ክርክር አይነት ማድረግ አይጠበቅብንም።

ሰንደቅ፡- ይህን በግለሰቦች ላይ ተንጠልጥሏል ያልከውን ልማት፣ ከእርሶ ፓርቲ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር እንዴት ትፈቱታላችሁ?

አቶ አናኒያ፡- እኛ እንዴት እንደምንፈታው እየተነጋገርንም እያረቀቅንም ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ሕብረተሰቡን አሳምነን ስልጣን ላይ ስንወጣ ደግሞ በተግባር የምን ፈታው ነው የሚሆነው።

ሰንደቅ፡- ምርጫው ወራቶች ነው የቀሩት፣ እያረቀቅን ነው ስትል ምን እያልከን ነው?

አቶ አናኒያ፡- እያረቀቅን ያለነው ማንፌስቶና በራሪ ወረቀት ነው። እንጂ የሊብራሊዝም ፍልስፍናውማ ከሁለት መቶ አመታት በላይ የቆየ ነው።

ሰንደቅ፡- ከዚህ በፊት ኢንጅነር ግዛቸው፣ አቶ ስዬ አብርሃ እና ዶክተር ነጋሶን ከምክርቤት ፈቃድ ውጪ በቀጥታ ስራ አስፈፃሚ ማድረጋቸውን ተከትሎ ‘መርህ ይከበር’ ብለው የወጡ ወገኖች መኖራቸው ይታወቃል። አሁንም የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ተጥሷል ‘መርህ ይከበር’ ብለው ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ ያቀረቡ የፓርቲው አመራሮች አሉ። የእነዚህን አመራሮች ልዩነቶች የተስተናገደበትን መንገድ እንዴት ገመገምከው?

አቶ አናኒያ፡- እነዚህ ሰዎች በፓርቲው ማዕቀፍ ውስጥ እንዲስተናገዱ ሰፊ የሆነ ቦታ ተሰጥቷቸው ሃሳባቸውን እንዲያሰሙ ተፈቅዶላቸዋል። ግን ከተፈቀደላቸው አግባብ ውጪ የፓርቲውን ሕገ ደንብ በጣሰ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ነው እየተስተዋለ ያለው። ስለዚህ እነዚህ ሃይሎች አንድም ከጊዜ በኋላ ለገገርው ፓርቲ በመሸጦነት የገቡ ናቸው፣ አልያም ደግሞ ከመጀመሪያው ተልዕኮ ነበራቸው ማለት ነው። ምክንያቱም ፓርቲው የመነጋገሪያ መድረክ ፈጥሯላቸው ለመነጋገር ፈቃደኛ አለመሆናቸው ለእኔ አውዳሚ መንገድ አድርጌ ነው የምወስደው። እነዚህ ሰዎች ወደ አቅላቸው ተመልሰው ሊቋም ከማይችለው የህዝብ ማዕበል ተሰልፈው ወደፊት ቢገሰግሱ ይሻላል። እየወደቀ ያለውን ስርዓት እየደገፉ አብረው ባይወድቁ ይሻላል።

ሰንደቅ፡- ከዚህ በፊትም ጋዜጠኛ ሆነ ሳለህ ሳለህ “የሕዝብ ማዕበል እየመጣነው” ብለህ መጻፍህን አስታውሳለሁ። የጽሁፍን ግልባጭ ለጠ/ ሚሩ እና ለፀጥታና ደህንነት ሃላፊውም እንዲደርስ ሀገርም ለቀው እንዲሄዱ ምክር ሃሳብ አቅርበህ ነበር። አንተ የምትለው “የሕዝብ ማዕበል” እየመጣ መሆኑን ማሳያዎቹ ምንድን ናቸው?

አቶ አናኒያ፡- የህዝብ ማዕበሉ ኢሕአዴግ የፈጠረው የብሶት ማዕበል ነው። ሌላ አይደለም። ይሄንን ማየት ካልተሳናቸው በስተቀር እየመጣ ያለው ነገር የሞት ሽረት ጉዳይ ነው። ሁለት ሺ ሰባትን በምን መንገድ ለአምባገነኖች አሳልፈን አንሰጥም። ስለዚህም ከወዲሁ ነቅተው በታሪክ የሚታወሱበትን ስራዎች መስራት አለባቸው። አልያ ግን ህዝቡ በራሱ መንገድ በሰላማዊ መንገድ ከዙፋናቸው ያወርዳቸዋል።

ሰንደቅ፡- አንድነት ፓርቲ በቀጣይ ምርጫ አሸንፎ ለመውጣት ያደረገው ዝግጅት ምን ይመስላል?

አቶ አናኒያ፡- በጣም በበቂ ሁኔታና በሚያስገርም የመዋቅር ጥንካሬ ሁሉም ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁ። ሰሞኑም ጠቅላላ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር በሀገሪቱ በአራቱም አቅጣጫ በቂ የሆነ ተወዳዳሪዎችን ቀርበዋል። ፓርቲው ከያዘውም ክቡር ዓላማ አንፃር ከሌሎች ፓርቲዎች በላይ አሸናፊ ያደርገዋል።

ሰንደቅ፡- ፓርቲውን ከተቀላቀልክ የወራቶች እድሜ መሆኑ ይታወቃል። ከላይ ከሰነዘርካቸው ትልልቅ መደምደሚያዎች አንፃር የሰጠኸው አስተያየት እንዴት የሚታይ ይመስልሃል?

አቶ አናኒያ፡- ፖለቲካ ለሚከታተል ሰው ይህ ጥያቄ በጣም ቀላል ነው። የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚከታተል አንድ ጋዜጠኛ ህዝቡ ከየትኛው ወገን ጋር እንደተሰለፈ ማወቅ አያቅተውም፣ አውቆ ማየት ካልፈለገ በስተቀር።■

# 5ኛው ኢትዮጵያን በጎንደር የባህል ፌስቲቫል



ጎንደር የአፍሪካ ካሚሎት በሚል ከሚገለጹ የኢትዮጵያ ወርቃማ ዘመን አሻራዎች አንዷ ናት። ይህች ከተማ የቅርስ ብቻ ሳይሆን የባህል እና የመንፈሳዊ ፌስቲቫል ማዕከልም ናት። በአፍሪካ ድንቅ ከሚባሉት ግንባር ቀደም ኩነቶች አንዱ የጎንደር ጥምቀት ነው። የጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማዋ ያላትን ይህንን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ወደ ኢኮኖሚ ለመቀየር በከተማዋ በተለየ መልኩ የሚከበረውንና በሀገሪቱ ቱሪዝም ልማት ቁልፍ ሚና እየተጫወተ እና ሰፊ የገበያ አቅም እየሆነ የመጣውን የጥምቀት በዓል መሰረት በማድረግ ከአካባቢያዊ ራዕይ ሰፋ ባለ መልኩ ሀገራዊ ይዘት ያለውና የጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜ ሊያራዝም የሚችል እንዲሁም የከተማው ነዋሪ አልፎም ሀገራችን የተሻለ ገቢ ልታገኝ የምትችልበትን አቅም ለመፍጠር አስቦ ኢትዮጵያን በጎንደር በሚል የባህል ፌስቲቫል ይዘት ያለው ባህላዊ ትእይንት በ2003 ዓ.ም ማዘጋጀት ጀመረ።

ይህ በዓል የጎንደርን የፌስቲቫል ማእከልነት ሀገራዊና አህጉራዊ ሚና ሊጫወት የሚችል አቅም ያለው ነው በሚል ከስያሜው ጀምሮ ሀገራዊ ሆኖ የተወጠነ ነው። በውጥኑ ወቅት እንደ መነሻ የሚቆጠር መሰል ሀገራዊ የባህል ኩነት ባይኖርም የሀገር ውስጥና የውጭ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመቀመር እቅዱን ለማውጣት ተችሏል። ባለፉት ሶስት ዓመታትም የሀገራችንን ሌሎች ከተሞች ባሳተፈ መልኩ እንደ ኢትዮጵያ ቡና መንደር የመሳሰሉ ሀገራዊ ኩነቶችን ጨምሮ ከጎንደር ዩንቨርስቲ ጋር በመቀናጀት የዩንቨርስቲ ተማሪዎች የየመጡበት አካባቢን የሚያስተዋውቅ ስልት በመቀየስ ጎንደር ላይ ኢትዮጵያን ለመፍጠርና ለመሳል ተሞክሯል።

## ሁለተኛው ኢትዮጵያን በጎንደርና ዞናዊ ተሳትፎው

ጎንደር በ2003 ዓ.ም ያዘጋጀችው ፌስቲቫል ደማቅና ትኩረትን የሳበ ቢሆንም በከተማው ህዝብ የተዘጋጀ ፌስቲቫል ነበር። የ2004 ዓ.ም ኢትዮጵያን በጎንደር ፌስቲቫል ከመጀመሪያው በተሻለ የጎንደርና አካባቢዋን ወረዳዎች በስፋት ያሳተፈና የሰሜን ጎንደር ዞንን ጭምር ባለቤት ያደረገ ሆኖ ተዘጋጀ። ይህ በዓል ከራስ ደጀን እስከ አርማጭሆ ከመተማ እስከ ቋራ ከበለሳ እስከ አዳአርቃይ ድረስ የጎንደርና አካባቢዋ ባህል የታየበት ሲሆን እንደመጀመሪያው ሁሉ የጎንደር ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ኢትዮጵያን ጎንደር ላይ ለማሳየት ያደረጉት ጥረትም ይበልጥ ደምቆበታል።

## ሦስተኛው ኢትዮጵያን በጎንደርና ክልላዊ ትኩረቱ

ሶስተኛው ኢትዮጵያን በጎንደር ከሁለቱ ዓመታት ዝግጅት ልምድን በመቀመር የተዘጋጀ ሲሆን የአማራ ክልል ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረትን የቸረውና አጋርነቱን ያሳየበት ነበር። በመገናኛ ብዙሃን ሽፋን ረገድም ከአየር ላይ ጭምር በዘመናዊ ካሜራ በመታገዝ ቀረጻ የተከናወነበትና የውጭ ሚዲያዎችን ያሳተፈ በመሆኑ ለሀገሪቱ ገጽታ ግንባታ አበርክቶ ያለፈው ሚና ከፍተኛ ነበር።

## ኢትዮጵያን በጎንደር ሀገር አቀፍ የባህል ሳምንት ፌስቲቫልን አስተናጋጅ ሆኖ መከናወኑ

ከመነሻው ኢትዮጵያን የወከለ አንድ የተደራጀ ሀገራዊ ኩነትን በጎንደር ከተማ ለመተግበር የወጠነው የጎንደር ፌስቲቫል ሀገሪቱ ለ2ኛ ጊዜ የምታዘጋጀውን ሀገር አቀፍ የባህል ሳምንት ፌስቲቫል ለማስተናገድ በቃ። ይህ ፌስቲቫል በዋናነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እና ተጠሪ ተቋሙ በሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማእከል የሚዘጋጅ ሀገራዊ ፌስቲቫል ነው። ፌስቲቫሉ የባህል እሴቶች እንዲለሙ፣ እንዲተዋወቁ፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲኖራቸው ለማስቻል በዘርፍ ሀገራዊ ንቅናቄ ለመፍጠር የእደ ጥበብ ኢንዱስትሪው እንዲለማ፣ የባህል ልማቱ በየደረጃው ትኩረት እንዲያገኝ ንቅናቄ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ተቀይሶ የሚከበር ሀገር አቀፋዊ ባአል ነው። ይህንን ዝግጅት ጎንደር በ2006 ዓ.ም በተሳካ ሁኔታ አስተናግዳዋለች።

## 5ኛው ኢትዮጵያን በጎንደር የባህል ፌስቲቫል

ዘንድሮ ከጥር 7-9 2007 ዓ.ም ለ5ኛ ጊዜ የሚከበረው ኢትዮጵያን በጎንደር የባህል ፌስቲቫል ባህላዊ ጨዋታዎች፣ ሙዚቃዎች፣ የጎዳና ላይ ትዕይንቶች እና በዘርፍ ልማት ላይ የሚያተኩሩ የፓናል ውይይቶች አካቷል።

## የጎዳና ላይ ትዕይንት

ይህ የባህል ፌስቲቫል ከሚያካትታቸው ዝግጅቶች አንዱ የጎዳና ላይ የባህል ትዕይንቶች ናቸው። ይህ ትዕይንት ከጎንደር ከተማ 13 ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ 1300 ገደማ ትዕይንት አቅራቢዎች፣ ከሁሉም የገጠር ቀበሌዎች የተውጣጡ ባህላዊ ቱባ ባህል አቅራቢዎች፣ ከ35 ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ከ2000 ባላይ የጎዳና ላይ ትዕይንት አቅራቢዎች፣ ከ22 በላይ በከተማዋ የሚገኙ አማተር ክበባትና ማህበራት፣ 26 በሚደርሱ የውጪ ዜጎች የጎንደርኛ ጭፈራዎች፣ ያላነሱ አወቃቀሮች ያሉት የአዘጋጇ የጎንደር ከተማ ትዕይንት አቅራቢዎች ያደምቁታል።

## አውደ ርዕይ

የዝግጅቱ አካል የሚሆነው አውደ ርዕይ ታዋቂዋ ፎቶግራፍ አይዳ ሙሉነህ 39 አፍሪካ ሀገራት ፎቶ ግራፎች ለዕይታ ይበቃሉ። ሉሲና አርዲ ቅሪተ አካሎችም እንዲሁ ለእይታ ይበቃሉ። ከዚህ በተጨማሪ የባህል እሴቶች፣ የእደ ጥበብ ምርቶች፣ ከባህል ጋር የተቆራኙ የአነስተኛና ጥቃቅን አምራቾች ይሳፉበታል። አውደ ርዕዩ በመንደሮች የተከፋፈለ ሲሆን መንደሮቹም እንደሚይዙት የርዕይ ዓይነት ለተለያዩ አካባቢዎች መታሰቢያ ይሆኑ ዘንድ ተሰይመዋል።

## አውደ ጥናት

ሌላው የዝግጅቱ አካል አውደ ጥናት ሲሆን እደ ጥበብ ኢንዱስትሪ፣ ኪነ ጥበብና ኢንቨስትመንት ላይ ያተኮሩ የመነሻ ጥናት ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል።

በመሆኑም የከተማው ነዋሪ እንደወትሮው ሁሉ ለበዓሉ ዝግጅት እንዲያደርግ ጥሪ እያቀረብን። በዓሉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታችንን የምናረጋግጥበት፣ ለመልካም ገጽታ ግንባታችን የራሱን ድርሻ የሚወጣበት እንዲሆን ጥሪ እናቀርባለን።

በጎንደር ከተማ አስተዳደር
ባህልና ቱሪዝም መምሪያ
የሀገር አቀፍ የባህል ሳምንት
ፌስቲቫልን ምክንያት በማድረግ የተሳከ■

# ዕጹብ የገና ስጦታ. . .

ቀንድና በአጠቃላይ በአፍሪካና በመላው ዓለም ሰላማዊ የሆነ ግንኙነት እንዲሰፍን ያላቸው ሚና ምንድን ነው በሚል የተደረገ ኮንፈረንስ ትዝ አለኝ። እነዚሁ ከኢጋድ አባላተ አገራት የተውጣጡ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች "IGAD Countries Religions Leaders Consultation on the Welfare of the Region" በሚል መሪ ቃል የተካኼደ አኅጉራዊ ኮንፈረንስ ነበር።

በዚህ በኬንያ ናይሮቢ በተደረገውጉባዔ ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ን የመላው አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ የኾኑት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ፣ "Peace and the Human Race" በሚል ርእስ ለጉባኤው ያቀረቡትን የጥናት ወረቀት ለማንበብ ዕድሉን አግኝቼ ነበር።

ብፁዕነታቸው በዚሁ የጥናት ወረቀታቸው፡- "… ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ ዋንኛ ተልዕኮዋ የሠላም አለቃ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መስበክ፣ በሰላም ማጣት፣ በግጭት፣ በጦርነት በምትታመሰው ምድር፣ በኹከትና በሽብር ሥጋት ለሚናጠው ዓለማችን ሰላምና ፍቅር የሞላበትን ቅዱስ ወንጌል፣ የምስራቹን ቃል ለሰው ልጆች ኹሉ ማዳረስ…።" እንደሆነ ይኸው የጥናት ወረቀታቸው ያትታል።

በተጨማሪም "…የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቀደመው ታሪኳ በሰው ልጆች ኹሉ መካከል ሰላምና ፍቅር የተሞላ ግንኙነት እንዲኖር ያስተማረችና፣ ሌላው ቀርቶ በሃይማኖት የማይመስሏትን ከመካከለኛው ምሥራቅ በሃይማኖት ጠብ ምክንያት የተሰደዱ የነቢዩ መሐመድ ተከታዮችን ያለ ምንም ልዩነት በሰላም ተቀብላ ያስተናገደች፣ የወንጌልን እውነት የሆነውን ሰላምን፣ ፍቅርን በቃልም በተግባርም የሰበከች ቤተ ክርስቲያን መሆኗን።" ይኸው የብፁዕነታቸው የጥናት ወረቀት ይጠቁማል።

ምንም እንኳን ይህ የደመቀና ግዙፍ ታሪክ ያላት፣ በሰው ልጆች ኹሉ መካከል ሰላምን የሰበከች ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ያለችበት እውነታው አሳዛኝና ተገላቢጦሽ ቢሆንም። "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስ አንድነትን ለመጠበቅ ትጉ።" ተብሎ በወንጌል ቅዱስ ቃል የተጻፈላቸው አባቶቻችን እርስ በርሳቸው ተከፋፍለውና ተለያይተው እንኳን ለዓለም ቀርቶ ለራሳቸው የሚሆን ሠላም ጠፍቷቸው የመንግሥታትንና የፖለቲከኞችን ደጅ የሚጠኑ ወደመሆን የመሸጋገራቸው ነገር ልብን የሚሰብር መሆኑ ሳይዘነጋ።

በሰው ልጆች መካከል ሠላም እንዲሰፍን ታላቅ ሚና ያላቸው ሃይማኖቶች፣ ስለ ሰላም፣ ዕርቅና ፍቅር ማስተማር ኃላፊነት ያለባቸው የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች በተቃራኒው የጠብ፣ የግጭትና የጦርነት መንሥኤ ሲሆኑ በታሪክ ደጋግመን አይተናል፣ በቁጭትም ታዝበናል። በመሠረቱ ግን የክርስትና የሃይማኖት ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጻሕፍት እንደተጻፈው፡- "ድንቅ፣ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አምላክ፣ አባትና የሰላም አለቃ ነው።"

ስለሆነም የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ኹሉ የሠላም አብሳሪዎችና የምስራች ቃል ሰባኪዎች ናቸው። የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሌሊት መላእክትና የሰማይ ሰራዊት ከእረኞች ጋር በአንድነት ሆነው፡ - "ሰላም በምድር ይሁን ለሰው ልጆችም በጎ ፈቃድ!" የሚለውን የምስራች በዜማ እንዳወጁ ኹሉ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ልደት በዓልም በክርስቲያኖች ኹሉ ዘንድ ይኸው በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ያገኘነው ታላቅ፣ ፍጹምና ዘላለማዊ ሰላም ነው ሊነገር፣ ሊወራ፣ ሊዜም የሚገባው። ለክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ ሰላምና ፍቅር የተሞላ የልደት በዓል እንዲሆን በመመኘት ልሰናበት።

ሠላም! ሻሎም!■

ሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ
MIDROC Ethiopia Technology Group

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ
ኩባንያዎች አመራር አባላትና ሠራተኞች
ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የክርስትና
እምነት ተከታዮች
እንኳን ለልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ
በማለት መልካም ምኞታችንን
እንገልጻለን፡፡


መልካም የገና በዓል!
፳፻፯ ዓ.ም.

MIDROC CEO
ELFORA
KOSPI
MBI
TRUST
HOME DEPOT
TNA
gp
ዋንዛ
WANZA
DAYLIGHT
ሴፖኮ
SEPCo
Rainbow
ADAGO Trading
Queen's
SUMMIT Partners

www.midroc-ethiotechgroup.com

# ጌዲዮን ዘላለም በአሜሪካን እግር ኳስ አብዮት ውስጥ

በቆንጂት ተሾመ



ተሰጥኦ አዳኙ አርሴን ቬንገር የወደፊቱ የኢመሬትስ ንጉስ እንደሚሆን የመሰከሩለት ጌዲዮን ዘላለም ለሶስት ሀገሮች ብሔራዊ ቡድን የመጫወት ምርጫዎች ነበሩት። ተወልዶ እስከ ዘጠኝ አመቱ ላደገባት ለጀርመን ወይም ለወላጆቹ ሀገር ለኢትዮጵያ፣ አሊያም ደግሞ ከዘጠኝ አመቱ እስከ 16 አመቱ ድረስ ለኖረባት አሜሪካ የመጫወት እድሎች ነበሩት። የተጫዋቹን የእግር ኳስ ተሰጥኦ በማለዳ የተረዱት አሜሪካና ጀርመን ግን በተለየ ሁኔታ የግላቸው ለማድረግ እርስ በእርስ ሲፎካከሩ ቆይተዋል።

ኢትዮጵያ ግን ለ2013 የአፍሪካ ዋንጫ ካለፈች በኂላና ለ2014 አለም ዋንጫ ማጣሪያ የመጨረሻው ምዕራፍ ስትደርስ ነበር ጌዲዮንን ያወቀችው። እርሱም ኢትዮጵያ ከናይጄሪያ ስትጫወት በኢትዮጵያ ቡድንን ሙሉ ጨዋታ መከታተሉንና መልካም እድል መመኘቱን በፌስ ቡክ ገጹ መግለጹ ለዋልያዎቹ የመጫወት ፍላጎቱን የጠቆመ መሰለ። እናም ብዙ ኢትዮጵያውያን ለዋልያዎቹ እንዲጫወት መመኘትና መማጸናቸውን ቀጠሉ። ከስፖርት አፍቃሪው ህዝብ በተጨማሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ቴዎድሮስ አድኻኖም ሳይቀሩ ጌዲዮን ለኢትዮጵያ እንዲጫወት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚሰጡ በመግለጽ በይፋ ጠይቀውታል።

የወቅቱ የዋልያዎቹ አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻውም "ዘላለምን ለምን ለኢትዮጵያ እንዲጫወት አይጠራም?" ተብለው በጋዜጠኞች ተጠየቁ። እርሳቸውም እንዲህ ሲሉ ነበር የመለሱት። "አሁን ለጊዜው ቡድኔ ውስጥ ከእርሱ የሚያንስ ተጫዋች የለም። ነገር ግን እርሱ ጥያቄ ካቀረበና ለቡድኑ የሚመጥን አቋም ካሳየ አይተነው ልንመርጠው እንችላለን"

አርሴን ቬንገር 'የሴስክ ፋብሪጋስ ምትክ' ሲሉ ያወደሱትን ባለተሰጥኦ ታዳጊ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መለያ ለማየት ለፈለገ የስፖርት አፍቃሪ የዋልያዎቹ አሰልጣኝ ምላሽ አስገራሚ ነበር። በዋልያዎቹ ቡድን ውስጥ ለጠፋው ፈጣሪ (Creative) ተጫዋች ጌዲዮን ትክክለኛ መፍትሔ እንደሚሆን ያሰቡ ደጋፊዎችንም ያሳዘነ ነበር። ወላጅ አባቱ ኢትዮጵያ ሲመጡ "እኔ ለኢትዮጵያ ቢጫወት ነው ደስ የሚለኝ። ምርጫው ግን የእርሱ ነው" ሲሉ የሰጡት አስተያየት ግን ለዋልያዎቹ ደጋፊዎች ተስፋ የሚሰጥ ነበር።

ጌዲዮን ለኢትዮጵያ እንዲጫወት በይፋ የጠየቀውም ሆነ የወተወተው አካል አልነበረም። እርሱም የሚሻለውን እየፈተሸ ቆይቶ በመጨረሻ ላይ ወሰነ፤ አሜሪካንንም መረጠ። በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይም ያቀረበው የአሜሪካን ዜግነት ጥያቄ ጉዳይ ዜና በስፋት ተሰራጭቷል። ይህን ተከትሎም ጌዲዮን የአሜሪካን እግር ኳስ አብዮት አቀጣጣይ መሆኑ እየተወራለት ነው። በርካታ አሜሪካውያንም ደስታቸውን በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ ገልጸዋል።

ከኢትዮጵያውያን ወላጆቹ ጀርመን የተወለደው ጌዲዮን ለአሜሪካን ለመጫወት መወሰኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ያደረገው የዋሺንግተን ፖስት ጋዜጣ ስፖርት ጸሐፊ ስቴቨን ጎፍ በትዊተር ገጹ ላይ በ15 ሰዓታት ውስጥ ብቻ 816 ምላሾች ከአሜሪካውያን የደረሱት ሲሆን፣ 518 የሚሆኑት ደግሞ ደስተኛ መሆናቸውን የሚገልጹ ነበሩ።

ይህ ፈጣን የሆነ ምላሽ ከብዙ አሜሪካውያን የሚጠበቅ እንደነበር የጎል ስፖርት ጸሀፊው ማይክ ደከርሲ ገልጿል። ይሁንና አሜሪካን እንደ እርሱ ላለ ባለተሰጥኦ ተጨዋችን የማሳደግ ባህል እንደሌላት በመጥቀስ የአርሴናሉ አማካይ እንደ ከዚህ በፊቶቹ ፍሬዲ አዱ እና ጁሊያን ግሪን በአጭሩ ሊጠፋ ይችላል ሲል ስጋቱን ገልጿል።

ጌዲዮን በዘጠኝ አመቱ ከጀርመን ወደ ሜሪላንድ በመምጣት በኦልኔይ ሬንጀርስ የእግር ኳስ ማሰልጠኛ ውስጥ ያሰለጠኑት ማት ፒልኪንግተን ግን ጌዲዮን አሜሪካንን መምረጡ እንዳላስገረማቸውና ትክክል እንደሆነ ተናግረዋል።

"እርሱ በእኛ በአሜሪካውያን ስልጠና ነው ያደገው። በአሜሪካን የወጣቶች እግር ኳስ ስልጠና ነው ጎልቶ መውጣት የቻለው። በአሜሪካን ለእድገቱ መሰረት የሆኑ አመታትን አሳልፏል። ገና ከ9 አመቱ ጀምሮ እስከ 16 አመቱ ድረስ በመኖር በአሜሪካውያን ባህል አድጓል። ጥሩ ግንኙነትንም ፈጥሯል። ወደ እንግሊዝ ከሄደ በኂላም ተመላልሶ በመምጣት ጓደኞቹንና የክለብ አጋሮቹን ይጠይቃል" በማለት ተጫዋቹ ትክክለኛ ምርጫ መምረጡን ተናግረዋል።

ወደ ማሰልጠኛ ማዕከላቸው ሲመጣ ጌዲዮን ከሌሎች የእድሜ እኩዮቹ በተለየ ሁኔታ ሰውነቱ በጣም ቀጫጫና ትንሽ እንደነበረ የሚያስታውሱት የቀድሞ አሰልጣኙ ፒልኪንግተን፤ ኳስን የመረዳት ግንዛቤውና ተሰጥኦው ግን በተክለሰውነት ከሚበልጡት ተጫዋቾች የበለጠ እንደነበር መስክረዋል። "የእርሱ እግር ኳስን የመረዳት ልዩ ጥበብ፣ እይታውና ፈጣሪነቱ ጎልቶ እንዲታይ አድርጎታል" ብለዋል።

"ገና ከልጅነት እድሜው ጀምሮም ቢሆን ጌዲዮን ከኳስ ጋር ጥሩ እንቅስቃሴ ነው የሚያደርገው። ኳስ ፈጽሞ የሚነጠቅ አይመስልም። ሲያቀብልም ፍጹም አስቦና እንዳይበላሽበት ተጠንቅቆ ነው። እርሱ ላይ ያየሁት ተሰጥኦ ብዙዎች ዘንድ የሌለና ከስንት አንድ ተጫዋቾ የሚታደሉት ነው" ሲሉም አሞካሽተውታል።

ከአራት ወራት በፊት ስለጌዲዮን ዘላለም አስተያየታቸውን የሰጡት የአርሴናሉ አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር አሁን 17 ዓመት የሆነው ታዳጊ ተጫዋቻቸው በጥቂት አመታት ውስጥ ታላቅ የእግር ኳስ ደረጃ ላይ እንደሚደርስ እምነታቸውን ገልጸው ነበር።

***በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ጌዲዮን እስከአሁን ተሰልፎ ባያውቅም በቅርቡ ግን አርሴናል በቻምፒየንስ ሊጉ ጋላታሳራይን 4ለ1 በአሸነፈበት ጨዋታ ተቀይሮ ገብቶ በመጫወት ያሳየው ብቃት አድናቆትን አስገኝቶለታል***

"ጌዲዮን ታላቅ ተጫዋች የሚያደርገው የእግር ኳስ ተሰጥኦ እንዳለው በፍጹም ልቤ አምናለሁ። ይህ ደግሞ በቀጣዮቹ ሁለትና ሶስት አመታት የሚወሰን ነው። ምክንያቱም በታላቅ ደረጃ የሚፎካከር ተጫዋች ለመሆን የሚያስችለው የአእምሮ ብስለት ደረጃን ማሳየት ይኖርበታል" ሲሉ ቬንገር አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

ፈረንሳዊው አሰልጣኝ ስለጌዲዮን ልዩ ተሰጥኦ ጨምረው ሲያስረዱ "እርሱ ኳስን አመቻችቶ ከማቀበል ጀምሮ፣ ጥሩ እይታ ያለውና ፈጣሪ (Creative) የሆነ ተጫዋች ነው። ይህንን ክህሎቱን ማሰደግና የአካል ብቃቱን ማሳደግ ከቻለ እጅግ በጣም አስፈላጊ ተጫዋች መሆን ይችላል"

ጌዲዮን በኦልኔይ ሬንጀርስ እግር ኳስን ሲጀምር አማካይ ተጫዋች በመሆን እንደነበር የሚያስታውሱት አሰልጣኝ ፒልኪንግተን ወደ ማጥቃቱ ያመዘነ አማካይ እንደነበር ሰሞኑን ለሶከር አሜሪካ በሰጡት ማብራሪያ አስረድተዋል።

"ቡድናችን በሶስት አማካዮች ነበር የምንጫወተው። እርሱም ሁልጊዜ ወደ ፊት ጠልቆ የሚጫወት አማካይ መሆንን ነበር የሚመርጠው። በማጥቃት ላይ ያመዘነ አማካይ ነበር። ነገር ግን አንዳንዴም ወደ ኂላ በመመለስ ኳስን መስርቶ መጫወትን ይችልበታል። ለቡድን ጨዋታ እርሱ በጣም አስገራሚ የሆነ ችሎታን የታደለ ነው" ብለዋል።

"አሜሪካን በብራዚሉ የ2014 የአለም ዋንጫ ላይ የተመለከተ እግር ኳስ አፍቃሪ ጌዲዮን ዘላለምን የመሰለ ተጫዋች እንደሌላት ይረዳል" የሚለው ሌላው የሶከር አሜሪካ ጸሀፊ ማይክ ዎይታላ፣ የአሜሪካን ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ጀርመናዊው የርገን ክሊንስማን ቡድኑን የተሟላ ለማድረግ የሚችልበት ጊዜ ላይ መድረሱን ይገልጻል። "አሜሪካን እንደ ጌዲዮን ያለ የላቀ የእግር ኳስ ክህሎት ያለው ተጫዋች ካገኘች የጀመረችውን የለውጥ አብዮት ማቀጣጠል እንደምትችል ከወዲሁ መናገር ይቻላል" በማለትም ሀሳቡን ገልጿል።

በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ጌዲዮን እስከአሁን ተሰልፎ ባያውቅም በቅርቡ ግን አርሴናል በቻምፒየንስ ሊጉ ጋላታሳራይን 4ለ1 በአሸነፈበት ጨዋታ ተቀይሮ ገብቶ በመጫወት ያሳየው ብቃት አድናቆትን አስገኝቶለታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ለአርሴናል ዋናው ቡድን የተሰለፈው ክለቡ በኤፍ ኤ ዋንጫ ከኮቬንተሪ ጋር በነበረው ጨዋታ እንደነበር ይታወሳል። በወቅቱ የ16 አመት ታዳጊ የነበረው ጌዲዮን አርሴን ቬንገር አርሴናልን ማሰልጠን ከጀመሩ በኂላ የተወለደና ለክለቡ የተሰለፈ የመጀመሪያው ተጫዋች ሆኖ ተመዝግቧል።

በኢምሬትሱ ክለብ የስፔናዊውን ሴስክ ፋብሪጋስን 4 ቁጥር የመለያ ልብስ የተሰጠው ጌዲዮን ዘላለም፣ በአሜሪካን ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ተስፋ ከሚጣልባቸው ወጣት ተጫዋቾች አንደኛው ሆኑ እየተወደሰ ነው። ከኢትዮጵያውያን ወላጆቹ ጀርመን ተወልዶ እስከ 9 አመቱ ያደገ ሲሆን፣ ለአሜሪካን ዋናው ብሔራዊ ቡድን ተሰልፎ ካልተጫወተ አሁንም ለኢትዮጵያም ሆነ ለጀርመን ብሔራዊ ቡድን የመጫወት ምርጫ አለው። ይሁንና አስቀድሞ የዜግነት ጥያቄ ላቀረበባት አሜሪካን መጫወቱ አይቀሬ መሆኑን መናገር ይቻላል።■





## ማሬ ዲባባ በቻይና ዚያሜን ማራቶን

# ክብረወሰን በመስበር አሸነፈች




*የዘንድሮውን የማራቶን ፉክክር ርቀቱን ያጠናቀቀችበት 2 ሰአት ከ19 ደቂቃ ከ52 ሰከንድ የውድድሩ አዲስ ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል*

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ማሬ ዲባባ በቻይና በተካሄደው የዢያሜን ኢንተርናሽናል የማራቶን ውድድር አዲስ ክብረወሰን በማስመዝገብ ጭምር አሸንፋለች። በወንዶች ጥላሁን ረጋሳ ኬንያዊውም ሞሰስ ተከትሎ በመግባት ሁለተኛ ሆኗል።

የዢያሜን ኢንተርናሽናል የማራቶን ውድድር ቅዳሜ እለት የተካሄደ ሲሆን፣ በሴቶች የአምናዋ አሸናፊ ማሬ ዲባባ የውድድሩን አዲስ ክብረወሰን በመስበር አሸንፋለች። ባለፈው አመት ውድድሩን 2 ሰአት ከ21 ደቂቃ ከ36 ሰከንዶች በመግባት ለአምስት አመት የቆየውን የውድድሩን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር አሸንፋ የነበረችው ማሬ፣ ዘንድሮም ተመሳሳይ ድልን መድገም ችላለች። የዘንድሮውን የማራቶን ፉክክር ርቀቱን ያጠናቀቀችበት 2 ሰአት ከ19 ደቂቃ ከ52 ሰከንድ የውድድሩ አዲስ ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የግሏ የማራቶን ምርጥ ሰአት ሆኖላታል። ማሬ ዲባባን በመከተል ሁለተኛ ሆና ውድድሩን ያጠናቀቀችው ሌላዋ ኢትዮጵያዊት አሹ ቃሲም ናት።


በወንዶች መካከል በተካሄደው ፉክክር ደግሞ አትሌት ጥላሁን ረጋሳ ከኬንያዊው ሞሰስ ሞሶፕ ጋር ጠንካራ ፉክክር በማድረግ እስከመጨረሻው ሜትር ድረስ ለማሸነፍ ትግል አድርጓል። ይሁንና በመጨረሻዎቹ ሜትሮች በሞሰስ ተቀድሞ ሁለተኛ ሆኖ መግባቱን ዥንዋ ዘግቧል። ሞሰስ ርቀቱን 2 ሰአት ከ06 ደቂቃ ከ19 ሰከንድ በመግባት ያሸነፈበት ሰአት የውድድሩ አዲስ ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል። ጥላሁን ከኬንያዊው አትሌት 27 ሰከንዶች ብቻ ዘግይቶ ሁለተኛ ደረጃን መያዙ እንዳስቆጨውም ከውድድሩ በኋላ በሰጠው አስተያየት ተናግሯል።■

# የስቴቨን ጄራርድ የሊቨርፑል ስንብት

ስቴቨን ጄራርድ ከሊቨርፑል ውጪ በሌላ መለያ ልብስ የማይታሰብና በአንፊልድ ጫማውን እንደሚሰቅል የታመነበት ነበር። የሊቨርፑል ምልክት ተደርጎ የሚቆጠረው እንግሊዛዊው አማካይ ስቴቨን ጄራርድ አንፊልድ የመልቀቁ ዜና እውነት ሆኗል። ይህም ብዙ የክለቡን ተጫዋቾችና ደጋፊዎች ያስደነገጠ ሆኗል። እርሱም ያልጠበቀውን ውሳኔ ለመወሰን መገደዱን ገልጾ ምክንያቱን አስረድቷል።

የ34 ዓመቱ እንግሊዛዊ አማካይ ጄራርድ ከልጅነት እድሜው ጀምሮ የቆየበትን ክለብ ለመልቀቅ የተገደደበት ዋንኛ ምክንያት በቡድኑ ውስጥ በቃሚነት የመሰለፍ እድል እንደማይኖረው ሲረዳ መሆኑን አስታውቋል። ይህንንም የተገነዘበው ከአሰልጣኙ ብሬንዳን ሮጀርስ ጋር በአደረገው ውይይት መሆኑን ገልጿል።

"አሰልጣኙ ጋር በነበረን ውይይት ለቡድኑ ውጤታማነት ሲል የእኔን በቋሚነት የመጫወት ሁኔታ ውስን እንደሚሆን ነው የነገረኝ። ይህን ቅጽበት በህይወቴ ከማልረሳቸው መካከል አንዱ ሆኖ ተቀርጿል። ነገር ግን የአሰልጣኙ ውሳኔ ለሁሉም ወገን ትክክል እንደሆነ ነው የተገነዘብኩት። ይሁንና ለረጅም አመት በቋሚ አሰላለፍ ውስጥ ለቆየ ተጫዋች እንዲህ ያለ ውሳኔ ላይ የሚያስደርስ ውይይትን ከአሰልጣኝ ጋር ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው"



የዘንድሮው የውድድር አመት እስኪጠናቀቅ ድረስ በሊቨርፑል እንደሚቆይ ያስታወቀው ጄራርድ እስከ መጨረሻው ጨዋታ ድረስ በቋሚ አሰላለፍ ውስጥም ይሁን በተጠባባቂነት ቢመደብ ለክለቡ ውጤታማነት የሚችለውን ሁሉ ከመስጠት እንደማይቆጠብ ተናግሯል።

ሊቨርፑልን መልቀቁን ተከትሎ ከክለቡ ተጫዋቾች፣ አሰልጣኞችና ደጋፊዎች እየደረሰው ያለው የአድናቆትና የማበረታቻ መልዕክቶች እጅግ ስሜቱን እንደነኩት የገለጸው የቀድሞ የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን አምበል ጄራርድ "በጣም ጠንካራ መሆንና ቀሪዎቹን ወራት በጥሩ ብቃት ለመጫወት መጣር ይኖርብኛል" ብሏል።

የስቴቨን ጄራርድ ቀጣይ ማረፊያው ወደ አሜሪካን ሜጀር ሶከር ሊግ እንደሚሆን የእንግሊዝና አሜሪካን ጋዜጦች በስፋት ዘግበዋል። በተለይም ደግሞ ሎስ አንጀለስ ጋላክሲ ተጫዋቹን ለማስፈረም ስምምነት ላይ መድረሱን ነው የጠቆሙት።■

# የዝውውር ወሬዎች

• ፍራንክ ላምፓርድ በማንቸስተር ሲቲ ለሌላ ተጨማሪ ዓመት የሚያቆየውን አዲስ ስምምነት ተቀብሏል። ተጫዋቹ በኢትሀድ ስታዲየም ለአንድ አመት በውሰት ለመጫወት ፈርሞ የነበረ ቢሆንም አሰልጣኝ ማኑኤል ፔሊግሬኒ እንግሊዛዊው አማካይ የላቀ ብቃት በማሳየቱ ተጨማሪ አንድ አመት እንዲቆይ ፈልገዋል።

• በማንቸስተር ዩናይትድና ሊቨርፑል የሚፈለገው የስዋንሲ ሲቲው ዊልፍሬድ ቦኒ በአሰልጣኝ ጆዜ ሞውሪንሆ አይን ውስጥ ገብቷል። ሞውሪንሆ ለአጥቂው የተጠየቁትን 30 ሚሊዮን ፓውንድ በመክፈል ወደ ቼልሲ ለማምጣት መወሰናቸውን ስታር ስፖርት ዘግቧል።

• አሪየን ሮበን ከማንቸስተር ዩናይትድ የቀረበለትን የዝውውር ጥያቄ ውድቅ እንዲያደርግ ክለቡ ባየርሙኒክ አዲስ የውል ስምምነት አቅርቦለታል። የቀድሞ የቼልሲ ኮከብ ተጫዋች ሆላንዳዊው ሮበን ወደ ኦልትራፎርድ እንዳይጓዝ በሳምንት ከሚያገኘው 180ሺ ፓውንድ ሳምንታዊ ደሞዙ በተጨማሪ ዳጎስ ባለ ገንዘብ ውሉን እንዲያራዝም ተጠይቋል።

• የተከላካይ መስመራቸውን ማጠናከር የሚፈልጉት የማንቸስተር ዩናይትዱ አሰልጣኝ ሉዊስ ቫን ኻል ከጀርመኖቹ ቦርሲያ ዶርትሙንድና ሻልክ ተጫዋቾን ለማስፈረም ድርድር ጀምረዋል። ከዶርትሙንድ ማት ሀመልስን፣ ከሻልክ ደግሞ ቤኔዲክት ሀውደስን ለመግዛት መቃረባቸውን ሰንዴይ ኤክስፕረስ ዘግቧል።

• ወደ ኦልድትራፎርድ በውሰት ከመጣ በኋላ ምንም ያልፈየደው ኮሎምቢያዊው አጥቂ ፋልካኦ ወደ ጣያ ጁቬንትስ ሊያቀና እንደሚችል ተገምቷል። ጁቬንቱስ የ28 አመቱ አጥቂ የኦልድትራፎርድ የውሰት ቆይታው ሲጠናቀቅ ለማስፈረም እንደሚፈልግ ሰንዴይ ሚረር ጽፏል።

• ቶተንሀም ሆትስፐር የፒኤስጂ አማካይ ተጫዋቹን አድሪየን ራቢዮትን በውሰት ለማስፈረም ከጫፍ ደርሷል። በፈረንሳዩ ክለብ በቋሚ አሰላለፍ ውስጥ መግባት እድል ያላገኘው የ19 አመቱ ራቢዮት በቶተንሃም ለስድስት ወራት ብቻ በውሰት የሚጫወት መሆኑንንም የጣሊያኑ ዴሎ ስፖርት አስታውቋል።

• ችሎታ ሳያንሰው በባህሪ አስቸጋሪ የሆነው የኒውካስል ዩናይትድ አጥቂ ሀቴም ቤናርፋ ከክለቡ ጋር ያለው ኮንትራት ተጠናቋል። በቀጣይም ወደ ፈረንሳይ ተመልሶ ሊሄድ እንደሚችል የተገመተ ሲሆን፣ ለኒሴ ክለብ ለመጫወት መስማማቱን ሰንዴይ ኤክስፕረስ ጽፏል።■

በኢትዮጵያ እድገትና ለህዝቦችዋ ብልጽግና ታላቅ ራዕይ ያላቸው ሼክ መሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ የአለም አቀፉ ድርጅታቸው አካል በሆነው በሚድሮክ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቡድን አማካኝነት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የአገራችንን ልማት ለማፋጠን በስፋት የሚንቀሳቀሱ የወገን አለኝታ ናቸው።

ለኢንቨስተራችን ሼክ መሐመድ በአገራችን በዘርፈ ብዙ የልማት ፕሮግራሞችን በመቀየስ የበኩላቸውን ድርሻ ለማበርከትና ተጨባጭም የሆነ ለውጥ ለማምጣት በሚያደርጉት ከፍተኛና ሁለገብ ጥረትም የላቀ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ለሚገኙ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎቻችን የስራ ዕድልም ፈጥረዋል።

በመሆኑም ድርጅታችን ሚድሮክ ኢትዮጵያና እህት ድርጅቶቹ ይህንን የኢንቨስተራችንን ራዕይ ለማስፈፀምና የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንደወትሮው ሁሉ ጠንክረው ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

ሚድሮክ ኢትዮጵያና እህት ድርጅቶቹ
ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች
መልካም የገና በዓል እንዲሆንላችሁ ይመኛሉ!

ጥረታችን ለልማት ነው!
ተባብረን ራዕዮቻችንን እውን እናድርግ!